የተቀጠፉ አበቦች

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ



በሳንዲ ዊልኮክስ

ከአሪና ሾርት ጋር

ተጨማሪ ማስታወሻ
በተሾመ ነጋሽ

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ - ደሐራ 1
የቃላት አጠቃቀም 1
የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊት ታሪካዊ አመጣጥ. 3
የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊት ስፋት መጠን 4
የአቆራረጥ ዓይነቶች..... 6
ምዕራፍ ሁለት - የጉዳይ ጥናቶች 8
የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ በኢትዮጵያ 10
ሴራሌዮን 24
ኬንያ 26
ግብፅ 30
ምዕራፍ ሦስት
መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር እና አካላችን 32
ወሲባዊነታችን፣ ፍጥረት እና ውድቀት 35
ግርዘት በብሉይ ኪዳን 45
ግርዘት በአዲስ ኪዳን.....58
መጽሐፍ ቅዱስ እና ሴቶችን መቁረጥ.....50
ምዕራፍ አራት
መጽሐፍ ቅዱስ፣ ባህል እና ለውጥ 52
ቅኝት 53
የሴትን ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ምክንያቶችን
በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሾች 56
ማጠቃለያ 62
ምዕራፍ አምስት
የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ
የሕክምና ምላሽ.....63
የሴት መራቢያ ብልቶች ተግባር 64
ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮች 70
ከአእምሮ ጤና ጋር የተያያዙ ችግሮች 73
ለአንዳንድ የተለመዱ እምነቶች የሚሰጡ ምላሾች.....76

ምዕራፍ ስድስት - ለውጥ እና የለውጥ ተቃውሞ 78
በአፍሪካ ድርጊቱን ለመቀየር የተደረገ ሙከራ 78
ባህልን ለመቀየር የሚደረገው ጥረት ከሥነ ምግባር
አንጻር ትክክል ነውን? 80
ቅርጽ እና ትርጉም 87
ጥቅም ያላቸውን ልዋጮች መጠቀም 90
ሌሎች የለውጥ ወኪሎች 92
ምዕራፍ ሰባት - ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ 95
ለጥቃቱ ሰለባዎች የሚሆን እርዳታ 97
የቅጣት አቅጣጫዎች 97
የእርዳታ ምንጮች 101
መፍትሔ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች 106
ማጠቃለያ 118
ተጨማሪ ማስታወሻ ለወንዶች፡-
ባሎች ሆይ፣ ሚስቶቻችሁን ውደዱ (በተሸመ ነጋሽ) 118
ተቀጥላ 125
የቃላት መፍቻ 128
ዋቢ መጻሕፍት 130

የተቀጠፉ አበቦች

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ
እና
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ

በሳንዲ ዊልኮክስ

እና

አሪና ሾርት

ተጨማሪ ማስታወሻ
በተሾመ ነጋሽ

BIBLE BASED BOOKS
BIM PUBLISHING

© A M Willcox 2005
የአማርኛው እትም 1998 (2006)
Published by: SIM Publishing, Ethiopia
PO Box 127
Addis Ababa Ethiopia

Printed by SIM Press

Permissions:
The Hesperian foundation for the use of the diagram and information about deinfubulation from *Where Women Have No Doctor* by Burns, Lovich, Maxwell and Shapiro.

Exerpts from:

Female Circumcision by Ephihenia Gachiri © Paulines Publications Africa. P.O. Box 49026, Nairobi, Kenya.

«መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲሱ መደበኛ ትርጉም © 1993 ዓ.ም በኢንተርናሽናል መጽ ሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታተመ::»

Cover design: (የሽፋን ሥዕል) Arina Short (አሪና ሾርት)
ትርጉም:- ዮዲት ኃይሉ
አርማት:- በኃይሉ ሽብሩ
ዋና አርታኢ:- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ዓለምፀሐይ እውነቱ

Dewey catalogue information

261.835
WIL Willcox, Sandy.
Cut flowers: female genital mutilation and a biblical response / Sandy Willcox.
1. Female Genital Mutilation. 2. Female Genital Mutilation—Biblical view.
3. Female Genital Mutilation—Medical view. I. Title.

ምስጋና

ኤስ ኣይ ኤም (SIM) እና ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ (ETC) ይህንን ሥራ ለማጠናቀቅ ጊዜዬን ልጠቀምበት እንድችል ረድተውኛል።

ስለ ጤና የሚናገረውን ክፍል ሐኪሞች (GP 's)፣ የቀዶ ጥገና ባለሙያዎች (Surgeons)፣ የማኅፀን ሐኪሞች (Gynaecologists) እና ነርሶች አንብበውታል። ከእነርሱም ውስጥ አብዛኛዎቹ አፍሪካውያንን ሴቶች በማክም ልምድ ያላቸው ናቸው። ብዙ ሰዎች የቀረውን የመጽሐፉን ክፍል ወይም ከፊሉን አንብበው ጠቃሚ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። አግባብነት ያለውን የመጽሐፉን ክፍል በማንበብና እውነተኛ አስተያየታቸውን በመስጠት «ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ» በሚል ርእስ ሥር የቀረበውን ጽሑፍ እንደ ገና እንድንሠራው ያደረጉንን የኢቲሲ ሴት ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ ለማመስገን እፈልጋለሁ።

ወንዶች እና ሴቶች ተማሪዎች እንዲሁም ባልደረቦቻችን ጽሑፉን ከማንበባቸው በተጨማሪ ለጉዳይ ጥናቶች (Case Studies) የሚሆኑ መረጃዎችን ሰጥተውናል። ሥራዎቻቸው ጥቅም ላይ የዋሉት በፈቃድ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ከየት እንደ ተወሰዱ ተጠቅሷል። አንዳንድ ቦታ ግን፣ በጥያቄያቸው መሠረት የሰዎቹ ስም እና ማንነት እንዳይጠቀስ ተደርጓል።

ብዙ ሰዎች የዚህ መጽሐፍ ሥራ እንዲጠናቀቅ ገንዘብ ሰጥተዋል። ሌሎች ብዙዎች ደግሞ ይህ መጽሐፍ ፍሬ እንዲኖረው ጸልየዋል፣ ይህ ሥራቸው ከጌታ በስተቀር ለሌላ የማይታይ እና የማይታወቅ ነው። እግዚአብሔርም ጸሎታችንን ሰምቶ ይህንን መጽሐፍ የኢትዮጵያን ሴቶችን ወደ ራሱ አሳብ የማምጫ መንገድ ያድርገው።

የመረጃ ምንጮችን ለመጥቀስ እና መረጃዎችን ለመጠቀም የባለቤቶቹን ፈቃድ ለማግኘት የተቻለው ሙከራ ተደርጓል። ነገር ግን፣ የተዘለለ ተገኝቶ ቢነገረን በደስታ እናስተካክላለን።

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ - ደሐራ 1
የቃላት አጠቃቀም 1
የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊት ታሪካዊ አመጣጥ. 3
የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊት ስፋት መጠን 4
የአቆራረጥ ዓይነቶች..... 6
ምዕራፍ ሁለት - የጉዳይ ጥናቶች 8
የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ በኢትዮጵያ 10
ሴራሌዮን 24
ኬንያ 26
ግብፅ 30
ምዕራፍ ሦስት
መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር እና አካላችን 32
ወሲባዊነታችን፣ ፍጥረት እና ውድቀት 35
ግርዘት በብሉይ ኪዳን 45
ግርዘት በአዲስ ኪዳን.....58
መጽሐፍ ቅዱስ እና ሴቶችን መቁረጥ.....50
ምዕራፍ አራት
መጽሐፍ ቅዱስ፣ ባህል እና ለውጥ 52
ቅኝት 53
የሴትን ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ምክንያቶችን
በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሾች 56
ማጠቃለያ 62
ምዕራፍ አምስት
የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ
የሕክምና ምላሽ.....63
የሴት መራቢያ ብልቶች ተግባር 64
ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮች 70
ከአእምሮ ጤና ጋር የተያያዙ ችግሮች 73
ለአንዳንድ የተለመዱ እምነቶች የሚሰጡ ምላሾች.....76

ምዕራፍ ስድስት - ለውጥ እና የለውጥ ተቃውሞ 78
በአፍሪካ ድርጊቱን ለመቀየር የተደረገ ሙከራ 78
ባህልን ለመቀየር የሚደረገው ጥረት ከሥነ ምግባር
አንጻር ትክክል ነውን? 80
ቅርጽ እና ትርጉም 87
ጥቅም ያላቸውን ልዋጮች መጠቀም 90
ሌሎች የለውጥ ወኪሎች 92
ምዕራፍ ሰባት - ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ 95
ለጥቃቱ ሰለባዎች የሚሆን እርዳታ 97
የቅጣት አቅጣጫዎች 97
የእርዳታ ምንጮች 101
መፍትሔ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች 106
ማጠቃለያ 118
ተጨማሪ ማስታወሻ ለወንዶች፡-
ባሎች ሆይ፣ ሚስቶቻችሁን ውደዱ (በተሸመ ነጋሽ) 118
ተቀጥላ 125
የቃላት መፍቻ 128
ዋቢ መጻሕፍት 130

ምዕራፍ አንድ፡፡ ደሐራ

አበቦች እና ሰዎች በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን፣ ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁሉ የመጨረሻና በጣም ድንቅ ነበሩ፡፡ ምክንያቱም፣ እነርሱ ብቻ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋልና ነው፡፡ አበባን መቁረጥ እግዚአብሔር እንድንደሰትበት የሰጠንን አንድን ነገር ማጥፋት ነው፡፡ ሰውን መቁረጥ ግን የእግዚአብሔር የራሱ ነጸብራቅ የሆነን ነገር ማበላሸት ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ልምድ ምንድን ነው? ለምን በአፍሪካ ውስጥ በብዛት ይደረጋል? ድርጊቱ ለምን አልለወጥ አለ? ስለ ጉዳዩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ነገር ይኖር ይሆን? ይህንን ሥር የሰደደ ባህላዊ ልማድ ለመቀየር መሞከር ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል ነውን? ይህ መጽሐፍ መልስ ሊሰጥባቸው ከሚሞክራቸው ጥያቄዎች መካከል እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን፣ ወደ እነዚህ ጉዳዮች በቀጥታ ከመግባታችን በፊት፣ ስለ ምን እና ስለ እነማን እንደምናወራ ልንግባባ ያስፈልጋል፡፡ አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት እንዲያስችል፣ በመጽሐፉ ጀርባ ላይ የቃላት መፍቻ በተቀጥላ መልክ አብሮ ቀርቧል፡፡

የቃላት አጠቃቀም

በአሁኑ ጊዜ ባሉ ጽሑፎች ውስጥ፣ *የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ* የሚለውን ሐሳብ ጥሩ አድርጎ የሚገልጸን ቃል የመጠቀም ጉዳይ ከፍተኛ ክርክር አስነሥቷል፡፡ በድሮዎቹ ጽሑፎች ውስጥ፣ በብዛት ጥቅም ላይ ይውል የነበው አገላለጽ፣ *የሴት ግርዘት* የሚለው ነበር፡፡ ይህ አባባል ግን ሐሳቡን በትክክል የመግለጹ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ በብዙ ባህሎች ውስጥ ሴቶችንም ሆነ ወንዶችን የመቁረጥ ድርጊት የሚገለጸው በአንድ ቃል ስለ ሆነ፣ ሴቶችን የመቁረጡ አሠራር ከወንዶቹ ግርዘት ጋር ተመጣጣኝ እንደ ሆነ ያስመስለዋል፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት ምዕራፍ አምስትን ማንበብ ይቻላል፡፡ «ግርዘት» የሚለውን ቃል መጠቀም፣ መቆረጡ ለሴቶች ጥሩ እንደ ሆነ ከማስመሰሉም በተጨማሪ፣ አንዳንድ ሰዎች

መጽሐፍ ቅዱስ በሴቶችም ላይ ይፈጸም የሚል እንዲመስላቸው ያደርጋል። እንደዚህ መታሰቡ ግን ያሳዝናል። ምክንያቱም ከአካል አፈጣጠር አንጻር ሲታይ፣ የአንዳንድ ሴቶችን የቂንጥር ሽፋን (ቂንጥርን የሚሸፍን ቁራጭ ቆዳ) መቁረጥ ብቻውን ጉዳቱ ከወንዶች ግርዘት ጋር እኩል ይሆናል። ሌሎቹን የሴት የብልት ክፍሎች መቁረጥ ደግሞ የወንድን ብልት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እንደ ማስወገድ ያህል ነው። በዚህ ምክንያት የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፣ የልጃገረዶችንና የአዋቂ ሴቶችን መቆረጥ ለመግለጽ «ግርዘት» የሚለውን ቃል መጠቀም አልፈለገችም።

በጣም የተለመደው፣ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውና ከሕክምናም አንጻር ትክክል የሆነው አገላለጽ፣ የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ (Female Genital Mutilation) የሚለው ስለ ሆነ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ይህንኑ አገላለጽ ለመጠቀም ተመርጧል። የዓለም የጤና ድርጅት (World Health Organization) የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ (Female Genital Mutilation) ለሚለው አገላለጽ ፍች ሲሰጥ፡- «*ባሕላዊ ወይም የሕክምና ባልሆኑ ምክንያቶች የሴትን ውጫዊ ብልት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ፣ ወይም በሴት የብልት ክፍሎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ አሠራርን ሁሉ ያጠቃልላል።*» ብሏል።

ይሁን እንጂ፣ ከሴት ጋር በሚደረግ የግል ጭውውት ውስጥ «የተቆረጠ» የሚለውን ቃል መጠቀም ለሴቶቹ ስሜት ያለመጠንቀቅ እና ጭካኔ ነው። በተለይ ደግሞ የችግሩ ሰለባ የሆነችን ሴት «የተቆረጠች» ብሎ መጥቀስ ደግሞ አስቀድሞ በደረሰው ጉዳት ላይ ሌላ ጉዳት መጨመር ነው። ይህ ደግሞ አላስፈላጊና ጎጂ ነው። «መቁረጥ» የሚለው ቃል «መግረዝ» ከሚለው ቃል የተለየ ትርጉም ስላለው፣ መግረዝ በሚለው ቃል ፈንታ መጠቀሙ ሁልጊዜ ጥሩ ነው። «የሴት ግርዘት» የሚለውን አባባል ዐውዱ ሲጋብዝ ብቻ ተጠቅመንበታል።

የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት ታሪካዊ አመጣጥ

ብዙ ሰዎች የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን ከእስልምና ጋር ያያይዙታል። ይሁን እንጂ፣ ድርጊቱ የእስልምና መሥራች ከሆነው መሐመድ ሺህ ዓመታት ቀድሞ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2500 በግብፅ አገር ይፈጸም እንደ ነበር መረጃ ያመለክታል። በመሆኑም፣ ድርጊቱ ከእስልምና እምነት መመሥረትም ይቀድማል። መሐመድ ልጁን እንዳስቀረጠ የሚጠቁም መረጃ የለም። ሙስሊሞች በድርጊቱ ትክክለኝነት ላይ ቢከራከሩም፣ አሳቡ ግን የቁርአን መሠረት ያለው አይመስልም። ስለ ባህላዊ ልምዶች (ጎጂ ባህሎች) ለመነጋገር በታንዛኒያ ውስጥ ነሐሴ 1992 ዓ.ም ለተሰበሰበው የኢንተር አፍሪካ ኮሚቴ፣ ዶክተር ኬርማኒ ስለ እስላማዊ ወይም ሸሪያ ሕግ እና የሴትን ውጫዊ ብልት መቆረጥ አስመልክቶ የሚከተለውን ተናግረዋል፦

> *የሴቶች ግርዘት የእስልምና ወግ ወይም ሃይማኖታዊ ግዴታ እንዳልሆነ እንረዳለን። በተጨማሪም፣ በዘፋ መልኩ የሚፈጸመው ግርዘት ሞራሹንም ከእስልምና እምነት ጋር የሚጻረር ነው። የመደረጉ እና ያለመደረጉ ነገር መወሰን ያለበት ለሕክምና ካለው አስፈላጊነት ወይም ከሰዎቹ ፍላጎት አንጻር እንጂ እንደ ባህላዊ ልምድ ተቆጥሮ ሁሉም ሰዎች ሊፈጽሙት አይገባም። ስለዚህ፣ ድርጊቱ በእስልምና እምነት የሚከለከለም ሆነ የሚበረታታ ሳይሆን፣ እንደ ሁኔታው እና እንደ ድርጊቱ አስፈላጊነት እንዲወሰን ተተቷል (ገጽ 82)።*

በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶችን ብልት የሚቆርጡት አብዛኞቹ ባህላዊ እምነት የነበራቸው ወይም ክርስቲያኖች ናቸው። ሁሉቱም ክርስቲያኖችና መስሊሞች አሁን ያላቸውን እምነት ከመያዛቸው በፊት የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ልምድ ያለው ባህላዊ እምነት የነበራቸው ይመስላል። የእስልምና እምነት የወንዶች ግርዘት እንዲፈጸም ስለሚያዝ፣ ሴቶችንም የመቁረጡ አሠራር በዚሁ የእምነት ጥላ ሥር እንደ ቀጠለ ይገመታል።

ክርስቲያን ለሆኑቱ ደግሞ፣ ግርዘት አከራካሪ የሚሆነው ከባህላዊ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነገር ካለው ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ አንድ ብሔረሰብ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክርስቲያን ወንዶች እንዳይገረዙ ወስነዋል። በዚያም የሴቶች ግርዘት ቆሟል። ክርስቲያኖች በሆኑ በሌሎች ቡድኖች ዘንድ ደግሞ፣ የወንዶች ግርዘት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተያይዞ ሳይሆን እንደ ባህል ወይም የጤና ልምድ ተቆጥሮ መፈጸም ቀጥሏል። እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ኖሯቸው ወንዶችን የሚገርዙቱ አብዛኞቹ መሪዎቻቸው ወንዶች ስለ ሆኑ ሴቶችን የመቁረጡ ልምድ ያለ ተቃውሞ ቀጥሏል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ግርዘት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደ ሆነ ብቻ አውቆ፣ ከክርስቶስ ጋር የመጣው አዲስ ኪዳን የወንዶችን ግርዘት እንደማያዝ፣ ለሴቶች ደግሞ መቼም እንዳልታዘዘ ያለመረዳት፣ ሰዎች ክርስቲያኖች ከሆኑም በኋላም እንኳን ድርጊቱ በሴቶች እና በወንዶች ላይ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲፈጸም አስተዋጽኦ አድርጓል።

የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊት ስፋት መጠን

የዓለም የጤና ድርጅት እንዳመለከተው፣ 132 ሚሊዮን ያህል ሴቶች ለሴት ውጫዊ ብልት የመቆረጥ ድርጊት ተዳርገዋል። በተጨማሪም፣ ድርጅቱ በሰጠው ግምት መሠረት በየዓመቱ 2 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴት ልጆችና አዋቂዎች በዚህ ባለው ቁጥር ላይ ይጨመራሉ። ይህ ቁጥር ውሱን በሆነ ጥናት ላይ ተመርኩዞ የተሰጠ በመሆኑ፣ በጣም ግምታዊ ሊሆን ይችላል። ኢትዮጵያን በምሳሌነት ብንወስድ፣ የወሊድ ቁጥር በዓመት በግምት አራት ሚሊዮን ይደርሳል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ሲሆኑ፣ ከእነርሱም ውስጥ ደግሞ 80 በመቶ የሚሆኑት ይቆረጣሉ። ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ቁጥር ብቻ፣ ለጋብቻ በደረሱ ጊዜ የሚቆረጡትን ሴቶች ሳይጨምር፣ በአንድ ዓመት ብቻ የሕፃናት ተቆራጮቹን ቁጥር ወደ 2 ሚሊዮን ያስጠጋዋል።

በዓለም የጤና ድርጅት ቆጠራ (ጥናት) ውስጥ የተካተቱት

አብዛኞቹ ሴቶች በ28 የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። ከዚህ ውስጥ ድርጊቱ በከፍተኛ ሁኔታ የሚከናወነው በሶማሊያ እና በጅቡቲ ሲሆን፣ ድርጊቱ የሚፈጸምባቸው ሴቶች ቁጥር ወደ 98 በመቶ ያህል ነው። በግብፅ 97 በመቶ፣ በማሊ 94 በመቶ፣ በሴራሊዮን 90 በመቶ፣ በሱዳን 89 በመቶ፣ በኢትዮጵያ 85 በመቶ፣ በጋምቢያ 80 በመቶ ይደርሳል (ኪማኒ)።

ባርከር- ቤንፊልድ የተባሉ ሰው በመጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት፣ የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት በአውሮፓና በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ይደረግ ነበር። በተለይም፣ በአሜሪካ ድርጊቱ እስከ (እ.ኤ.አ) 1937 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ ነበር። በወቅቱ ድርጊቱ ይፈጸም የነበረው እንደ ሕክምና ተቆጥሮ ሲሆን፣ ይኸውም ለወሲብ ልቅነት፣ ለሚጥል በሽታ፣ ለብርክ፣ ለሴጋ እና ለእብደት ችግሮች መፍትሔ ይሆናል ተብሎ ነበር (ገጽ 285-286)። አሁን ግን ስደተኞች እና በጥገኝነት የሚኖሩ እንደገና እያስተዋወቁት ይገኛሉ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንዳስታወቀው፦

> ድርጊቱ አሁንም በአውስትራሊያ፣ በካናዳ፣ በዴንማርክ፣ በፈረንሣይ፣ በጣሊያን፣ በኔዘርላንድስ፣ በስዊድን፣ በእንግሊዝ እና በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ይፈጸማል። አንዳንድ ጊዜ በኢንዱስትሪ በበለጸጉ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ልጃገረዶች ወይም ሴት ሕፃናት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በዚያው ማኅበረሰብ ውስጥ ነዋሪ በሆኑ ሐኪሞች አማካይነት ይቆረጣሉ። ብዙውን ጊዜ፣ የልምድ ቆራጮች እዚያው አገሮቹ ድረስ እንዲመጡ ይደረጋል፣ ወይም ሴቶቹ ለመቆረጥ ወደ ሌላ አገር ይላካሉ። ነገር ግን ድርጊቱ በእነዚህ በበለጸጉ አገሮች ውስጥ በሚኖሩ ሕዝቦች ምን ያህል የተለመደ እንደ ሆነ የሚገልጽ መረጃ የለም (የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ድረ ገጽ)።

እንግሊዝ፣ ስዊድን፣ ቤልጅዬም፣ ቡርኪናፋሶ፣ ጋና፣ ጊኒ ሪፐብሊክ፣ ጋምቢያ፣ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ፈረንሳይ እና ጅቡቲ ድርጊቱን የሚያወግዝ ሕግ አላቸው። ነገር ግን፣ በብዙ አገሮች ውስጥ ሕፃናትን ያለአግባብ መጠቀም እንዲሁም የተለያዩ የሀኪት

ድርጊቶችን አስመልክቶ የወጡ ሕግጋት የሴት ውጫዊ ብልት ቆራጮችን በመቃወም ሕግ ፊት ለማቅረብ በቂ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድርጊቱን ለይቶ በመቃወም ደንግጓል። (ተቀጥላውን ይመልከቱ።)

ሴቶችን የመቁረጥ ልምድ ያላቸው ማኅበረሰቦች በአብዛኛው ወንዶችንም ይገርዛሉ። ይህ ግን ሁል ጊዜ የሚሆን ነገር አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የኤርቦሬና የቁጫ ብሔረሰቦችን በምሳሌነት ብንወስድ፣ እነርሱ ሴቶችን ይቆርጣሉ፣ ወንዶችን ግን አይገርዙም።

የሴት ውጫዊ ብልት የአቆራረጥ ዓይነቶች

የዓለም የጤና ድርጅት፣ የሴትን ውጫዊ ብልት አቆራረጥን በዓይነቱ በአራት መድቦታል። እኔ ደግሞ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ የመጀመሪያውን ዓይነት አቆራረጥ ለሦስት ከፍዬዋለሁ። የተለያዩ የአቆራረጥ ዓይነቶች ስለሚፈጸምባቸው አገሮች እና ሕዝቦችም ጥቂት ምሳሌዎች ቀርበዋል። በአንድ አገር ውስጥ በሚኖሩ ወይም በአንድ ክልል በሚኖሩ ማኅበረሰቦች ውስጥ የተለያየ ዓይነት አደራረግ ሊኖር እንደሚችል ማሰቡ አስፈላጊ ነው። አንድ ሕዝብ ሆነው ሰፊ ማኅበረሰብ ያላቸው እንደ ኦሮሞ እና አማራ ባሉ ሕዝቦች መካከል እንኳ የአቆራረጥ ልማዳቸውን በተመለከተ መለያየት ሊኖር ይችላል።

ዓይነት አንድ

የቂንጥርን ሽፋን ከቂንጥር ከፊል ክፍል ወይም ሙሉ ለሙሉ ጋር አብሮ መቁረጥ።

- የቂንጥርን ሽፋን ማስወገድ። ይህ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የሚደረግ ሲሆን፣ ድርጊቱም «ሱና» ተብሎ ይጠራል።
- ቂንጥርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስወገድ። በኢትዮጵያ ውስጥ የትግሬ እና ጀበርቲ ማኅበረሰቦች ያደርጉታል።
- ቂንጥርን ሳይነኩ፣ የብልትን ንዑስ ከንፈር በከፊል

ማስወገድ። በኢትዮጵያ ውስጥ የአማራና የአገው ሕዝቦች ያደርጉታል።

ዓይነት ሁለት

ቂንጥርን እስከ ሽፋኑ እና ንዑስ ከንፈርን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አብሮ መቁረጥ።

- በኢትዮጵያ ውስጥ የጉራጌ፣ የስዋንላይክ፣ የትግራይ ትግሬዎች፣ የጎንደር አማሮችና የኦሮሞ ሕዝቦች ያደርጉታል።

ዓይነት ሦስት

ውጫዊ ብልትን ሙሉ በሙሉ መቁረጥና የብልትን አፍ መስፋት ወይም ማጥበብ። እንደዚህ ዓይነቱ አቆራረጥ «መቁረጥና መስፋት» ወይም በእንግሊዝኛ 'infibulation' ይባላል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በቆቱ፣ በአፋር፣ በብሌን፣ በትግሬ፣ በራሻይዳ፣ በሳሆ፣ በቤንጃ እና በኤርቦሬ ሕዝቦች መካከል ይደረጋል።

ዓይነት አራት

ምድብ ውስጥ ያልገቡ።

- <ኢንትሮሲሽን> (Introcision)። ይህ ከልክ ያለፈ አቆራረጥ ሲሆን፣ እንዲህ ዓይነት አቆራረጥ ሲፈጸም የውጭውና የውስጡ የብልት ክፍሎች ይቆረጣሉ። ይህ የሚደረገው በአውስትራሊያ፣ ፒት-ፓታ በሚባል ማኅበረሰብ ውስጥ ነው።

- ቂንጥርንና የብልትን ከንፈር መውጋት፣ መብሳት፣ መቁረጥና መተልተል።

- ቂንጥርንና የብልትን ከንፈር መወጠር፤ ለምሳሌ፣ በሩዋንዳ ይደረጋል።

- በማቃጠል መተኮስ። የሚወጋ ነገር በብልት ክፍተት ውስጥ በመስደድ እንዲደማ እና እንዲጠብ ማድረግ ነው።

ምዕራፍ ሁለት:: የጉዳይ ጥናቶች

በአንድ የከተማ ሆስፒታል ውስጥ የምትሠራ አንዲት ነርስ፣ ሁለት ልጃገረዶች ለመቆረጥ እርሷ ወደምትሠራበት ክፍል መምጣታቸውን ተገነዘበች:: የቆረጣው ዓይነት፣ ቂንጥርን ማስወገድ እና የብልትን አፍ ማጥበብ ነበር:: በወቅቱ ድርጊቱን የሚከለክል ሕግ የወጣ ቢሆንም፣ በተገቢው መልኩ በሥራ ላይ መዋል ግን አልጀመረም ነበር:: ታዲያ ይህች ነርስ ልጃገረዶቹን ባሉበት ትታ፣ ድርጊቱን ሊያስቆም የሚችል የሆስፒታል ኃላፊ መፈለግ ጀመረች:: ነገር ግን፣ ያሰበችውን ከማድረጓ በፊት ቆረጣው ተጠናቀቀ:: ወደ ክፍሏ በተመለሰች ጊዜ፣ ሁሉም ነገር አልቋል፤ ቂንጥሮቹ ተቆርጠው በሳህን ላይ ተቀምጠዋል፣ የልጆቹም ብልቶች ግጥም ተደርገው ተሰፍተዋል:: ስሜት እንዳይናራቸው በሚቆረጠው አካባቢ ማደንዘዣ ስለ ተደረገላቸው የጤና ባለሙያው ሥራውን ማከናወን ችሏል:: ይህ ባይሆን ኖሮ ግን፣ ልጆቹ ከሕመማቸው ሥቃይ የተነሣ እያለቀሱ እና እየተወራጩ አላሠራም ሊሉ ይችሉ ነበር:: እነዚህ ልጆች በወቅቱ ፈገግ ሊሉ ይሞክሩ ነበር፣ ሥቃዩ ግን ከጥቂት ቆይታ በኋላ ይመጣል:: መጀመሪያ፣ ማደንዘዣው የሚሠራበት ጊዜ ሲያበቃ ያማቸዋል:: በኋላ ደግሞ፣ የሠርጋቸው ቀን ማታ፣ ቀጥሎ ደግሞ በወሊድ ጊዜ ሌላ ሥቃይ ይሆናል:: ለእነዚህ ሴቶች ግን ባለመቆረጥ ምክንያት ከማኅበረሰባቸው በመገለል ከሚደርስባቸው ሥቃይ የሚበረታ ሌላ ሥቃይ የለም::

ግርዘት፣ መቁረጥ፣ ማስወገድና ቆርጦ ማውጣት የሚሉት ቃላት፣ የአቆራረጡ ዓይነቶች፣ ድርጊቱን ስለሚፈጽሙ አገሮች እና ሕዝቦች የተሰጡ የቁጥር መረጃዎች፣ እንዲሁም የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚያስከትላቸውን አደጋዎች በሚያስረዱ የሕክምና ገለጻዎችን የተሞሉ ብዙ ጽሑፎች፣ «ችግሩን» ለማስወገድ ወደ መሞከር እና ወደ ተግባር በቀላሉ ይመሩናል:: ይህንን ስናደርግ ግን፣ የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት የሰዎች፣ የባህላቸው እና የእሴቶቻቸው ጉዳይ መሆኑን

እንዘነጋለን። የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት የሕክምናውን እውነታዎች ካለማወቅ በልጃገረዶችና በሴቶች ላይ የሚፈጸም ወይም ደግሞ እነርሱን ለመጉዳት ታስቦ የሚደረግ ነገር አይደለም። ይልቁንም፣ መቁረጡ ለሰዎቹ የማንነት መገለጫ እና የማኅበረሰቡ አካል የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ጠቃሚ ድርጊት ነው።

የሴትን ውጫዊ ብልትን መቁረጥ፣ ሰዎችንና ባህላቸውን የሚመለከት ድርጊት ነው። ቢሆንም ግን፣ የሴቶችን ጤና የሚጐዳ የባህል ክፍል ነው። ስለዚህም፣ ከድርጊቱ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የሕክምና ችግሮችን መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን፣ ድርጊቱን የሕክምና ችግር ብቻ እንደ ሆነ አድርገን ከተረዳነው፣ የሕክምና መፍትሔዎችን ብቻ እንፈልጋለን። በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች፣ ችግሩን ከሕክምና አንጻር መፍትሔ ለመስጠት ተሞክሮ ነበር። ይህን ማድረጉ ግን መቆረጡ በንጽሕና እና ሥቃዩ በቀነሰ መልኩ እንዲፈጸም አደረገው እንጂ ድርጊቱን አልቀየረውም። ሰዎቹ ድርጊቱን የሚፈጽሙበትን ምክንያቶች በመረዳት፣ ዘላቂ ለውጥን ለማምጣት ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ ካለ በዛ አቅጣጫ መንቀሳቀስ አለብን። የዓለም የጤና ድርጅት ዋና ጸሐፊ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን አስመልክቶ ለድርጅቱ የጤና ኮሚሽን ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፦

> *. . . ሁልጊዜ መሥራት ያለብን የሰውን ባሕርያት እና ባህላዊ እሴቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ያለበለዚያ ግን ድርጊቱን በሚፈጽሙት እንዲሁም መፈጸማቸውም ትርጉም እና ጥቅም በሚሰጣቸው ዘንድ ሥራችን ትርጉመ ቢስ ይሆናል።*

ጉዳዩ ስለ ሰዎች እንደ መሆኑ መጠን፣ በዚህ መጽሐፍም ቅድሚያ በመስጠት የምንነጋገረው ስለ ሰዎች እና ባህሎቻቸው ነው። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ከፈጻሚዎቹ ባህል አንጻር ለመግለጽ እንዲያስችል በባህሉ ውስጥ እንዲሁም ውጪ ያሉ ሰዎች ስለ ድርጊቱ የሚሉትን ለማየት እንሞክራለን። ብዙ

ልማዶች፣ የአቆራረጥ ዓይነቶች እና ድርጊቱን ለመፈጸም አነሣሽ የሆኑ ምክንያቶች አሉ። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊዎች የሚኖሩት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ መሆኑ መጠን፣ ወደዚህ አገር የማድላት ነገር ይኖራል። ቢሆንም ግን፣ በኢትዮጵያ የሚደረገው በሌላ የአፍሪካ ክፍሎች የሚደረገውን የሚወክል ይመስላል። ይህንን መጽሐፍ እያነበብን ስንሄድ፣ ድርጊቱን ለመፈጸም የሚሰጡት ምክንያቶች ጥሩ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መጥፎ ወይም ደግሞ ትክክለኛ ባልሆነ መረጃ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን እንረዳለን። በተጨማሪም፣ ድርጊቱ ለመቀየር ሰምን አስቸጋሪ እንደ ሆነ እና የድርጊቱ ተቀባይነት አድጎ በዓለም ዙሪያ እንዴት ሚሊዮኖችን ሊነካ እንደ ቻለ ጥልቅ ግንዛቤ ይኖረናል ብለን እናስባለን።

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ በኢትዮጵያ

ቅኝት

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ከ80 - 100 ከሚደርሱት ብሔረሰቦች ውስጥ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የማይፈጽሙት 28ቱ ብቻ ናቸው። እነዚህ ብሔረሰቦች በአብዛኛው በደቡብ የአገሪቱ ክፍል የሚገኙ ሲሆን፣ ይኸውም የሐመር፣ በና፣ ሙርሲ እና የመኤን ብሔረሰቦችን ያጠቃልላል። አምስት ብሔረሰቦች ውጫዊውን የብልት ክፍል ሙሉ ለሙሉ ቆርጠው እንደሚሰፉ (Infibulation) ይታወቃል። አብዛኞቹ ግን የሚያደርጉት ቂንጥርን ማስወገድ (ሱና) ወይም ቂንጥርን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ማስወገድን (Clitorectomy) ነው (የአቆራረጡን ዓይነት በምዕራፍ 1 ውስጥ ይመልከቱ)። ድርጊቱን በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈጽሙት ሁለት ብሔረሰቦች አማራና ኦሮሞ ሲሆኑ፣ ቆረጣው የሚፈጸመው በልጅቱ ወይም በገራገጮቹ ቤት ውስጥ ነው። ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ የልጅቱ ወላጅ እናት ወይም የዓይን እናት ልጅቱን ያቅፉና ዓይኗን ይሸፍኗታል። በዳሰነች እና በጉራጌዎች ዘንድ ደግሞ መቁረጡን የሚፈጽሙት ከማኅበረሰቡ እንደ መቀላቀያ ሥርዓት አድርገው ነው። እንደ ሐዲያ ባሉ ብሔረሰቦች ዘንድ ደግሞ ለአቅመ- ሔዋን መድረሻ ዕድሜ የሚከበርበት የገርምስና ሥርዓት ነው። ብዙውን ጊዜ ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ግብዣ ይዘጋጃል። ይህም የቤተሰቡ

የሀብት መገለጫ እንደ ሆነ ይቆጠራል። ድግስ ካልተዘጋጀ ግን፣ ቆራጫ(ጩቤ) ምግብና ቡና ይሰጣታል (ጠዋል)። ብዙውን ጊዜ ቆራጮቹ ለሚሰጡት አገልግሎት በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ይከፈላቸዋል። የክፍያው መጠን የተለያየ ሲሆን፣ ከ5 እስከ 20 ብር ሊደርስ ይችላል።

ቢላዋ፣ ምላጭ፣ ሹል ድንጋይ ወይም የጣት ጥፍር ለመቁረጫነት ያገለግላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ሱና (የቂንጥርን ሽፋን መቁረጥ) በሚፈጸምበት ጊዜ፣ ሽፋኑ በተፈጥሮ ሳይኖር ከተገኘ ልጅቱ አትቆረጥም (የአቆራረጥ ዓይነቶችን በምዕራፍ 1 ውስጥ ይመልከቱ)። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ልጅቱ «በማርያም ተገርዛለች» ይባላል። ከቆረጣው በኋላ ቁስሉን ለማዳን ፈጣ፣ የእምቧጮ ቅጠል፣ የቀበቴ ቅጠል፣ እንቁላል፣ አመድ፣ ከሰል፣ ቅቤ፣ አልኮልና እና የመሳሰሉት ነገሮች በቁስሉ ላይ ይደረጋሉ። የልጅቱ እግሮች በአንድ ላይ ሊታሠሩም ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መዳኑን ለማፋጠን ልጅቱ የሚጨስ እሳት ከሥሯ ተቀምጦ እንድትታጠን ይደረጋል።

መቁረጥና መስፋት (Infibulation) ወይም ዓይነት ሦስት በሚደረግበት ጊዜ፣ የሽንት መውጫ ቀዳዳ እና የብልቱ አፍ አብሮ ያለመሰፋቱን ለማረጋገጥ ስንጥር ይጠቀማሉ። ይህ ስፌት የሚፈታው ልጅቱ ልታገባ ስትል ወይም ካገባች በኋላ ባልየው ብልቱን ታግሶ በሚያስገባበት ጊዜ ነው። ይህንን ሲያደርግ አዲሷ ሙሽራ እየተወራጨች እንዳታስቸግረው አብዛኛውን ጊዜ ይመታታል። ለእንደዚህ ዓይነት ሴት ግንኙነት ማድረጉ በራሱ የሚያም ሲሆን፣ ሥቃዩ የበለጠ የሚበረታው ግን ብልትን በጉልበት (በኃይል) ለማስገባት በሚሞክርበት ጊዜ በሚፈጠረው መላላጥ ነው። ባልየው ለተወሰነ ጊዜ ከሚስቱ ጋር በማይኖርበት ወቅት፣ ሚስቱ ታማኝ ሆና እንድትቆይ በሚል ሰበብ ድጋሚ መስፋት የሚደረግበትም ጊዜ አለ (የኢትዮጵያ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ፣ 52፣56)።

የኢትዮጵያ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ፣ (እ.ኤ.አ) በ1998 ዓ.ም የመነሻ ጥናት (Baseline Survey) አድርጐ ነበር። ይህ ጥናት

የቡድን ውይይትን አካቶ ነበር። ጥልቅ ውይይት ከተደረገባቸው ውስጥ 23 ብሔረሰቦች ድርጊቱን በተጠናከረ ሁኔታ የሚፈጽሙ ሲሆኑ፣ 24ቱ ግን ፈጽሞ አያደርጉትም። ውጫዊውን ብልት ሙሉ ለሙሉ የማስወገድ ልምድ ያላቸው ኤርቦሬዎች፣ 98 በመቶ ያህሉን ሴቶች የሚቆርጡት ወላይታዎች እንዲሁም የሙርሲ፣ የመኤን እና የበና ብሔረሰቦች በቡድን ውይይቱ አማካይነት ከተጠኑት ውስጥ የሉበትም (የኢትዮጵያ ጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ፤ 100-102)።

ደገኛ አማሮች

ወንዶች የሚገረዙት በስምንተኛ ቀናቸው ሲሆን፣ ሴቶችም እንዲሁ ሁልጊዜ ባይሆንም በአብዛኛው ግን የሚቆረጡት በሰባተኛ ቀናቸው ነው። ረዳቶች (የዓይን አባቶች /እናቶች/) ሕፃኑን/ኗን አቅፈው ሲይዙ፣ ቆራጩ/ጯ ደግሞ የመቁረጡን ተግባር ያከናውናሉ። ፌጦ ሞቅ ባለ ቂቤ ተደባልቆ ይቀባና ቁስሉ ይታሰራል። ከዚያም በወሊዱ ጊዜና ከዚያም በኋላ የረዱ ሁሉ ገንፎ ይጋበዛሉ። ቀደም ባሉት የ24 ሰዓታት የጊዜ ክልል ውስጥ ወሲብ የፈጸሙ ሁሉ ጥላ ናቸው ይባላል። ጥላ የሚለው ቃል ሌላ ፍቺ ቢኖረውም፣ በዚህ ዐውድ ግን ርኩስ ወይም የሚጐዳ የሚል ትርጉምን የያዘ ነው። እነዚህ ሰዎች ቁስሉ እስከሚድን ድረስ ሕፃኑ/ኗ ወዳሉበት ቤት እንዳይገቡ ይከለከላሉ። የተወለደውን ልጅ/ልጂት ከጥላ ለመጠበቅ የእንቧይ ፍሬና ሣሪቲ በበሩ ላይ ይሰቀላል፣ ይህም የተወለደውን ልጅ ከጥላ ለመታደግ ተጨማሪ መከላከያ ነው (ተረፈ፤ 44-45)

ቤተሰቡም በግ ወይም ዶሮ ያርድና ደሙ ይረጫል። በተጨማሪም፣ አረቄ በቤቱ ማዕዘናት እንዲሁም በበር እና በመስኮት ይፈነጠቃል። ይህ ሁሉ የሚደረገው፣ አድባሯን ደስ ለማሰኘት ነው። መቆረጡ የሚሰጠው ምክንያት ሴቲቱ ጭምት እንድትሆን እና ትዳርን አሻፈረኝ እንዳትል እንዲሁም የማትጣላ እና የበለጠ ታዛዥ እንድትሆን ያደርጋታል የሚል ነው። በተጨማሪም፣ በወሲብ ለመርካት የሚወስድባትን ጊዜ ይቀንሳል ይባላል።

የጂማ ኦሮሞዎች

አልዋል አደም የተባሉ ሰው እንደ ጸፉት፣ በጅማ ኦሮሞዎች ዘንድ ወንዶች የሚገረዙት በተወለዱ በ40 ወይም በ41ኛ ቀናቸው ሲሆን፣ የሴቶች መቆረጥ የሚፈጸመው ደግሞ ሰባት ዓመት ሲሆናቸው ነው። ሥርዓቱ በሚፈጸምበት ቀን ሁለት የቅርብ ሰዎች (ጃላ) ይገኛሉ። እነዚህ ጃላ የሚሆኑት ከልጆቹ ወላጆች መካከል ለአንዱ የቅርብ ጓደኞች የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ፣ ግርዘቱ በሚፈጸምበት ቀን ገንዘብ ወይም ስጦታን ለወላጆች ያመጣሉ። ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ አንዱ/ዷ ጃላ ሕፃኑን/ኗን ሲያቅፍ/ስታቅፍ ሌላኛ ው/ዋ ደግሞ የሕፃኑን/ኗን ዓይን ይይዛል/ትይዛለች። ቆረጣው በሚፈጸምበት ስፍራ በግ ወይም ዶሮ ይታረድና ደሙ በመሬት ላይ እንዲፈስ ይደረጋል (ገጽ 54)። ሕፃኗ/ኑ ካደጉ በኋላ ሴቷ የእርሷን ጃላ እናትያ ወይም እናት በማለት ስትጠራ፣ ወንዱ ደግሞ የራሱን ጃላ አባትያ ወይም አባቴ ይላል።

በቅርቡ ማለትም በ1994 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ ባደረግንበት ጊዜ እንደ ተነገረን፣ ሴቶች የሚቆረጡት ከ10 - 12 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ እያሉ ነው። በዕድሜ ተቀራራቢ የሆኑ እኅትማማቾች በአንድ ወቅት አብረው ሊቆረጡ ይችላሉ። በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ያሉ ሌሎች ሴት ልጆችም በአካባቢው ካሉ በአንድ ላይ ይቆረጣሉ። በወቅቱ ለወዳጆች እና ለዘመዶች የሚሆን ግብዣ ይዘጋጃል፣ የተቆረጡት ልጆች የቅርብ ጓደኞችም በግብዣው ላይ ይገኛሉ። ከዚያም የተቆረጠችው ልጅ በራሷ ክፍል ውስጥ ታገግማለች።

ሴቶች የሚቆረጡት ዝሙትን እንዳይፈጽሙ፣ ታማኝ ለማድረግ ነው። ረጋ ያሉም ይሆናሉ ይባላል። ካልተቆረጡ ግን ባደጉ ጊዜ ተቀባይነት ወይም የአዋቂነት ክብር አይኖራቸውም። «ከተገረዙት» ሴቶች ጋር እንዲቀመጡ አይፈቀድላቸውም።

«ገራዡ» በማየት የተማረ፣ ሴት ወይም ወንድ ሰው ሊሆን ይችላል። ለመቁረጥም የሚጠቀሙት ምላጭ ወይም የተሳለ ቢላዋ ነው። ቆራጮች በማኅበረሰቡ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ይከበራሉ፤

ለሴቶች የሚጠቅም አገልግሎት የሚሰጡ ተብለውም ይሞካሻሉ።

በአካባቢው ከሚኖሩት ውስጥ አምስት በመቶው ያህሉ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ድርጊቱን በተመለከተ ጥቂት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ይሰጣል። አንዳንድ ሰዎች፣ በተለይም በከተማ የሚኖሩት፣ ድርጊቱን ለመቀየር የሚፈልጉ ቢሆንም፣ ልጆቹ ለአቅመ-ሔዋን በሚደርሱ ጊዜ ከማኅበረሰቡ የሚደረግባቸው ግፊት፣ ልማዱን መከተልን እንዳይቃወሙት ያደርጋቸዋል።

ከምባታዎች

የሚከተለውን መረጃ የሰጠችን ሴት ወላጅ እናት ክርስቲያን ሆኑና ልጃቸውን ላለማስቆረጥ ወሰኑ። ልጃቸው ግን ክፉኛ ስለ ተሸፈባት አንድ ቀን በምስጢር ከጓደኞቿ ጋር ወደ ቆራጭ ዘንድ ለመሄድ ወሰነች። እናትየውም ይህንን ዕቅዷን ስላወቁ፣ ከልጃቸው ጋር ረጅም ውይይት በማድረግ ድርጊቱን በመፈጸማቸው ምክንያት በጋብቻ ውስጥና በወሊድ ጊዜ ስላጋጠማቸው ችግር አስረዷት። እርሷም በጉዳዩ አመነችበት። በአሁን ጊዜ እርሷ አግብታ በከተማ ውስጥ ትኖራለች፣ የእናቷንም አቋም ታመሰግናለች።

የከምባታ ሴቶች የሚቆረጡት ለአቅመ-ሔዋን ሲደርሱ ሲሆን፣ ጊዜውም ትምህርት ቤት የሚዘጋበት የክረምት ወቅት ነው። በአካባቢው የሚደረገው የዓይነት ሁለት አቆራረጥ (ቂንጥርን እና የብልትን ንዑስ ከንፈር መቁረጥ) ነው። ድርጊቱ የሚፈጸመው ሴቶች የሰከነ ስሜት እንዲኖራቸው፣ ሰውን የሚያከብሩ፣ ዝምተኞች፣ ገራምና ረጋ ያሉ እንዲሆኑ ነው ይባላል። ይህ የሚደረገው በዋነኛነት፣ በቀላሉ የወሲብ ስሜታቸው እንዳይነቃቃ ነው። ስለዚህም ከጋብቻ በፊት ድንግል ሆነው እንዲቆዩ፣ በትዳር ታማኝ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ያልተገረዘች ሴት፣ በማንኛውም ላም ላይ ጉብ እንደሚል ኮርማ ትሆናለች ይባላል።

ሴትን የሚቆርጠው ሴት ወይም ወንድ ሊሆን ይችላል፣ ወንዶችን የሚገርዘው ግን ወንድ ብቻ ነው። መቆረጡ ከሚፈጸምበት ቀን በፊት ባለው ምሽት ሴቶች ጓደኞቿ ልጅቷን ለማበረታታት ይሰበሰቡና ሌሊቱን በሙሉ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ

ያድራሉ። በክርስቲያኖች ቤት ዘፈንና ጭፈራ አይደረግም፤ ምክንያቱም እንደ ኃጢአት ስለሚቆጠር ነው። ፀሐይ ስትወጣ፣ ልጅቱ እንድትታጠብ ወደ ወንዝ ትወሰዳለች። ከዚያም የምትቆረጠው ሴት፣ የቅርብ ጓደኛዋ እና ቆራጯ/ጩቤ በአካባቢው ወደሚገኘው የእንስት ማሳ ውስጥ ይገባሉ። የምትቆረጠዋ ልጅ ጓደኛ የሆነች ሴት ዓይኗን ትሸፍናታለች። በወቅቱ መጮህና ማልቀስ አሳፋሪ ነው። የተቆረጠችው ሴት በምታገባበት ጊዜ፣ ይህች ዓይኗን የሸፈነቻት ልጅ ዋነኛ ሚዜ ትሆናለች። የእንስቱ አንጓ የውስጠኛው ክፍል ደሙን ለመምጠጥ ያገለግላል። መቆረጡ ከተፈጸመ ከሦስት ቀናት በኋላ፣ ቁስሉን በላባ የምታጸዳ አሮጊት ሴት ትመጣለች።

የልጅቱ ቤተሰቦችም የቀርከሃ ጎጆን ይቀልሳሉ። ይህ ጎጆ ትንሽ በር እንዲሁም ልጅቱ የምትተኛበት መደብ በውስጡ ይኖረዋል። የመቆረጡ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ የተቆረጠችው ልጅ በጠባቡ በር አልፋ ወደ ጎጆው ትገባለች፣ እስክትድንም ጉጆው የእርሷ ይሆናል። በዚህ ጎጆ ሆና በምታገግምበት ጊዜ አንድ ሰው ሁል ጊዜ አብሯት ይሆናል። ከሥቃዩ የተነሣ የምግብ ፍላጎት ባይኖራትም እንኳ፣ አብሯት የሚኖረው ሰው ድርሻ፣ የተቆረጠችውን ሴት መመገብ ነው። ሥጋ፣ ወተትና ቅቤ ይቀርብላታል። ለመጠየቅ የሚመጡ ጓደኞች ደግሞ ሎሚና ጣፋጮችን ያመጣሉ። በሁለተኛው ወር ማብቂያ ላይ ልጅቱ ወፍራ እና ለትዳር ዝግጁ ሆና ከማገገሚያዋ ትወጣለች።

ልጃገረዶቹ መቆረጥ ባይፈልጉም እንኳ፣ ያደርጉት ዘንድ ከአቻዎቻቸው ግፊት ይደረግባቸዋል። ወጣት ልጃገረዶች ይሸፍባቸዋል፣ ደግሞም ባል እንደማያገኙ ይነገራቸዋል። በተጨማሪም፣ ቂንጥራቸው እስከ ጉልበታችው ድረስ እንደሚያድግ እና እንደ አውራ ዶሮ እንደሚያስካኩ ይገለጽላቸዋል። ክርስቲያኖች ደግሞ፣ «የሚሲዮናዊ ሴት ልጅ ከነቂንጥሯ ትመጣለች» ተብሎ ይቀለድባቸዋል። ይህም ሁኔታ ለመቆረጥ ወደ ክሊኒክ መሄድ የመለመድ አዝማሚያ እንዲታይ አድርጓል። ከባህላዊ ቆራጮች ይልቅ የጤና ረዳቶች የበለጠ ይከፈላቸዋል። ምክንያቱም እነዚህ

ሰዎች ድርጊቱን የሚፈጽሙት የመያዝ እና ለፍርድ የመቅረብ አደጋን ተጋፍጠው ስለ ሆነ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን፣ እነዚህ የጤና ረዳቶች የትኛውንም የብልት ክፍል ሳያስወግዱ፣ ደም ፈስሶ እንዲቆም አድርገው ይቆርጧቸዋል። ልጃገረዶቹም ይህንን ካደረጉ በኋላ፣ ለጓደኞቻቸው «ተገርዣለሁ» ይሏቸዋል፣ ሹፈቱም ይቆማል።

በአካባቢው ያሉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በመቃወም ማስተማር ጀምረዋል። ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ የሚጠቀሙበት አቀራረብ፣ ሰዎች እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር ማበላሸት እንደሌለባቸው፣ ድርጊቱ ለሴቶች ጤና ጎጂ መሆኑንና ወንዶችን መግረዝ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደ ሆነ ማስተማር ነው። ሴት ልጆችን እና እናቶችን አብረው ያስተምራሉ።

አንድ የከምባታ ሰው የሚከተለውን ገልጿል፦

> «እኔ ከክርስቲያን ቤተሰብ የመጣሁ ነኝ። አንድ ቀን ሚሲዮናውያን የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ትክክል አይደለም ብለው አስተማሩ፣ አባቴም በአሳባቸው ተስማማ። ድርጊቱ በልጆቹ ላይ እንዳይፈጸም ወሰነ፣ እናቴም ተስማማች። አንድ ቀን ግን፣ አባቴ ለአገልግሎት (ለሥራ) ሲወጣ፣ እናቴ ሴት ልጇቿን አስቀረጠቻቸው። አባቴ ከሄደበት ሲመለስ፣ ስለ ሆነው ነገር ማንም አልነገረውም። እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስም ምሥጢር አድርገው ጠበቁት።

መጠይቅ የተደረገላት ወይዘሮም ግብረ ሥጋ ለእርሷ ሥቃይ መሆኑን ገልጻለች። ከባድም ሥራ ስለ ሆነባት ብታቆመው ፈቃዷ ነው። በመቆረጧ ምክንያት የተፈጠረው ጠባሳ ስለማይለጠጥ በወሊድ ጊዜ ችግርን እንደሚፈጥር ተናግራለች።

ሲዳሞዎች

ነጋ በሲዳሞ ከካባቢ ከመጡ በርካታ ሰዎች ጋር ቃለ ምልልስ አድርጓል። ከዚህ በታች ያለው፣ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው

ሴቶች መካከል የአንዳንዶቹ ታሪክ ነው። ስለ ድርጊቱ ያላቸው ምላሽ አዎንታዊም፣ አሉታዊም ነው። አዎንታዊዎቹ ምላሾች፣ ለክብራችንና ለማንነታችን ያለን አመለካከት በትክክለኛ መረጃ ላይ የመመሥረቱን አስፈላጊነት ያሳያል። ይህም «ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ» በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የሚታይ ይሆናል።

አንዲት ሴት ታሪኳን እንደሚከተለው ትናገራለች፦

> አውቀዋለሁ! አውቀዋለሁ! ግን በጣም ዘግይቷል። ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ በግልጽ ይታወሰኛል፤ በቦታው ብዙ ሰዎች ነበሩ። አጐቴ እና ሌሎቹ የቤተሰቤ አባላት በዶቃ እና በአዲስ ልብስ ያስጌጡኝ ጀመር። ከዚያም ውበቴንና ጥንካሬዬን ያደንቁ ጀመር። በወቅቱ ለአቅመ - ሔዋን ደርሼ ነበር። ገራኺ ሴት በድንገት ከተሰበሰበው ሕዝብ መሐል ወጣች። በዚህ ጊዜ ታዲያ ወኔዬ ሁሉ ከድቶኝ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ። ለመሮጥ ታገልኩ፤ አለቀስኩ፤ ሽንቴን እንኳ መቆጣጠር አልቻልኩም ነበር። ልብሴ ከላዬ ላይ መውለቁን ከማወቄ በፊት ብልቴ ተገልጧል። ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ቢላዋ የያዙትን የገራኺን ረዳት ነበር። ዓይኔንና አፌን ከደኑኝ። የቻሉትን ያህል ደበደቡኝ። እንዳልነቃነቅ ወደ ታች ጥብቅ አድርገው ያዙኝ። አንዳንዶቹ እግሮቼን በርግደው ሲይዙ፣ ሌሎቹ ደግሞ በእግሮቼ ላይ ቆሙብኝ። በዚያኑ ጊዜ፣ ገራኺ ተብዬዋ እስከምትረካ ድረስ ያለምሕረት መቁረጥ የምትፈልገውን ሁሉ መቁረጥ ጀመረች። በኋላም ቁስሉ መርቅዞ (ኢንፌክሽን ይዞ) ባህላዊ ሕክምና ተደርጐልኛል። ለጥቂት ወራት ያህል ሽንቴን በምሸናበት ጊዜ ያመኝ ነበር። ግንኙነት ማድረግ በጀመርኩበት ጊዜም ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ያህልም የሕመም ስሜት ነበረኝ። ከእነዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በኋላ፣ ስለ ድርጊቱ የተደበላለቀ ስሜት አለኝ። ይህ መደረጉ በኋላው ሕይወቴ በራስ የመተማመን ስሜቴን ጨምሮታል፤ የሕይወት ዓላማንም ሰጥቶኛል። በባሕሉ ውስጥ የኅሳው ሙሉ አባል አድርጎኛል። ከዚያ በኋላ እንዳፍር የሚያደርገኝ ከመሰሎቼ

የሚሰነዘር ግፊት የለብኝም። «ያልተገረዘች» ወይም «ያልተቆረጠች» የሚሉትን ቃላት በሰማሁ ጊዜ ፊቴን እንድሸፍን የሚያስገድደኝ ኀፍረት የለም።

ሌላዋ ሴት ደግሞ ስትናገር፦

ያገባሁት ሰው ክርስቲያን ነበር። በኋላ ግን ባሌ ያለመገረዜን አወቀ። ያደግኩት ሰዎች ስለ መገረዝ ብዙም በማይጨነቁበት በአዲስ አበባ ከተማ መሆኑን ነገርኩት። ባሌም ያለመገረዜን ላለመውደዱ ብዙ ምክንያቶችን አቀረበልኝ። የሚያሳዝነው ግን፣ ካሉን ሦስት ልጆች መካከል ብቸኛ ሴት የሆነችውን ልጃችንን ትገረዝ ብሎ ድርቅ አለ፤ እኔም እርሷን ለማስገረዝ ተገደድኩ።

የሴት ልጄ የመገረዣ ወቅት በደረሰ ጊዜ፣ የሕክምና ባለሙያ ወዳለበት የግል ሐኪም ቤት ወሰድናት። የቤተሰባችን አባላት ቁጥር ትንሽ ነው፣ በእነዚህም ውስጥ ደግሞ አንዳንዶቹ ክርስቲያን ስለ ነበሩ የግርዛቱ ሥርዓት ከተለመደው በጣም የተለየ ነበር። በግርዛት ወቅት የሚዘፈኑት የወሲብ ዘፈኖችና ሌሎች ሥርዓቶች አልነበሩም፣ ወይም በባህላዊው ሥርዓት እንደሚደረገው ድርጊቱ የተፈጸመው ብልቷ ለሰው ሁሉ በተጋለጠበት ሁኔታ አልነበረም። የልጄም ቁስል አላመረቀዘም። ልጃችንን ስለማስገረዛችን እስከ አሁን ድረስ አዝናለሁ። ግን ምን ማድረግ እችል ነበር? ባሌ እና ሌሎች ክርስቲያኖች ድርጊቱ እንዲፈጸም ይጨቀጭቁኝ ነበር። በተጨማሪም፣ ከቤተሰቦቻችን እና ከሌሎችም ግፊት ይደረግ ነበር።

ከተጠለፉና ከተገረዙ በኋላ ያገቡ አንዲት ባልቴት ሲናገሩ፦

በጠለፋ ማግባት ምንም ችግር የለውም። ምክንያቱም ድርጊቱ የጠለፈውን ሰው ጥንካሬና ጀግንነት የሚያሳይ ነው። ከጠለፋው በኋላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ በራሱ የሚያም ቢሆንም፣ ከሥቃዩ ጋር ግን መኖር ነበረብኝ። ይህ ባህላችን ነው። በኋላ ግን ከሕመሙና ከብርቱው የጠለፋ ጉዳት

ድኛለሁ። ጉዳቱ መመታትን፣ ማንገላታትን እና በኃይል የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ያጠቃልላል። ከእነዚህ ነገሮች የተነሣ ኢንፌክሽን ይዞኝ በባህላዊ ሕክምና ድኛለሁ። ሁሉም ነገር ባያስደስተኝም፣ ባህሌን ግን እወደዋለሁ። በደፈናው የእኛ ባህል በአካባቢያችን ካሉት በጣም ይሻላል። በአሁኑ ጊዜ በትዳር ውስጥ ከሚደረጉት ነገሮች እና ሆስፒታል ውስጥ በባለሙያ ገራገሮች አማካይነት ከሚደረገው ግርዘት አንጻር ብዙ መሻሻሎችን ባይም፣ ባህልን ወደ ማክበር ስንመጣ ግን፣ በተለይም ለትዳር እና ለግርዘት ሥርዓት ክብር መስጠትን አስመልክቶ፣ የቀደሙትን መልካሞቹን ቀናት እወዳቸዋለሁ።

ለመቆረጡ ሥርዓት የሚደረገው ዝግጅት የሚካሄደው ከምትቆረጠው ሴት እውቅና ውጭ ነው። ድርጊቱ የሚፈጸመው ልክ ከጋብቻ በፊት ወይም በኋላ ነው። የሚዘጋጀው ትልቅ ድግሥ የቅርብና የሩቅ ዘመዶችን ሁሉ ያሳትፋል። መቆረጡ ወላድነትን እንደሚጨምር እና ሴቲቱ መልካም ባሕርይ እንዲኖራት እንደሚያደርግ ይታመናል። የደሙ መፍሰስ ሴቲቱ ንጹሕ እንድትሆን ያደርጋታልም ይባላል። ካልተቆረጠች በስተቀር፣ ወንዱ የግብረ ሥጋ ፍላጐቷን ሊያረካ በፍጹም አይችልም ተብሎ ይታመናል። በተጨማሪም፣ ቂንጥሩ ይረዝምና «ቂንጥራቸውን በአንገታቸው ዙሪያ መጠምጠም እንደሚችሉት» የጎጂ ሴቶች ይሆናሉ ይባላል (ካልታተመ ጽሑፍ የተወሰደ)።

ሐዲያዎች

ግርማ እንዳለው መቆረጥ ሴቶች ተገዢዎች እንዲሆኑ ማስተማሪያ መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል። መቆረጡ ከልጅነት ወደ አዋቂነትና አቅመ - ሔዋን መሸጋገሪያ እንዲሁም ልጅቱን ለጋብቻ ብቁ የማድረጊያ ሥርዓት አካል ነው። መቆረጡ የሚያስተላልፈው መልእክት ሴቲቱ ለጋብቻ ዝግጁ መሆኗን ነው። መቆረጡ የሚፈጸመው ልጃገረዶቹ ከ12-17 ዕድሜ ሲሆናቸው ነው። ሥርዓቱ ክብርን ከማጎናጸፉም በላይ ልጅቱ በጋብቻዋ ምሽት

ድንግል መሆኗን ያረጋግጣል። ልጅቷም የቤተሰቧን ክብር እና የእርሷን ተፈላጊነት የሚያሳዩ ስጦታዎች ይሰጧታል። የተከበረ ቤተሰብ ደግሞ ክብርን ለመላው ጎሣ ይጨምራል። የሴቷን የግብረ ሥጋ ፍላጐት ለመግታት ሥርዓቱ አስፈላጊ ነው ይባላል። ይህ ከሆነ ወንድየው ከአንድ በላይ ሚስቶችን ለማርካት አቅም ይኖረዋል። ሴቷ ካልተቆረጠች በባሏ ብቻ ልትረካ ስለማትችል፣ ከጋብቻ ውጭ ሌላ ግንኙነት ትፈልጋለች ተብሎ ይታሰባል። ሴቲቱ ሰቢላ የምታስቸግር ከሆነ፣ ብዙ ሚስቶች ይዞ የራሱን ፍላጐት ለማርካት ለባልየው ጥሩ ምክንያት ይሆንለታል። ገራገሮቹ ክፍያን የሚቀበሉትና በማኅበረሰቡም ውስጥ ቦታ ያላቸው ሰዎች ናቸው (ካልታተመ የጥናት ጽሑፍ የተወሰደ)።

ኃይሌ እንደ ጻፈው፣ ለመቆረጥ ዝግጁ የመሆኛ ዕድሜ ባጃሜ በመባል ይታወቃል። ከመቆረጡ ሥርዓት በመቀጠል ወጣት ሴቶች የሚጋብዙበት ድግስ ይደገሳል። እናቲቱ አዋቂ ሴቶችን ትጠራለች፣ አባትየው ደግሞ በበኩሉ አዋቂ ወንዶች ይጋብዛል። ሌሊቱን በሙሉ፣ ትላልቆቹ ሰዎች ይዘፍናሉ፣ ወጣቶቹ ደግሞ ይዘፍናሉ፣ ይጨፍሩማል። በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ወጣት ወንዶች ከቤቱ ፊት ለፊት የሣር መደብ ይሠራሉ። የምትቆረጠውም ልጅ በዚህ መደብ ላይ እንድትሆን ይደረግና ወንዶች ጋቢ ይዘው በዙሪያዋ ይቆማሉ። ከዚያም ልጅቱ ዓይኗ ይሸፈንና ትቆረጣለች። አብዛኛውን ጊዜ ገራዥ የምትሆነው ሴት ናት። መቆረጡ በሚፈጸምበት ጊዜ ልጅቷ ሕመሙን እንድትቋቋመው ለማበረታታት በሥርዓቱ ላይ ለመገኘት የመጡት እንግዶች ይዘፍኑላታል። ሂደቱ ሲጠናቀቅ ደግሞ የተሰባሰበው ሰው እልል ይላል። ልጅቱ ደግሞ ትጠቀለልና ደም መፍሰሱ እስኪቆም ድረስ ከእሳት አጠገብ ባለ መደብ ላይ ትደረጋለች። ከጥቂት ቀናት በኋላ ለማገገም ወደ ተከለለ ቦታ (ዱማ) ትገባለች። በዛ ስፍራ በቀን አምስት ወይም ስድስት ጊዜ፣ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ ምግብ ይሰጣታል። በዚያ ሆና ጥፍሮቿን መቆረጥ ትጀምራለች። ይህም አዋቂ መሆኗን ያሳያል። ሦስት ወራት ከሚፈጀው ከዚህ የማገገም ሂደት በኋላ በመንደሩ ውስጥ

በቅርብ የተቆረጡ ሴቶች በሰልፉ ሆነው፣ በወጣቶች እየተመሩ በመንደሩ እና በገበያው ስፍራ እንዲያልፉ ይደረጋል። ይህ የተገረዙ ወንድ ልጆች ስጦታን በመስጠትና (እርስ በርሳቸው) በመታገል (ጋሚላ በመጫወት) የሴቶችን ትኩረት ሊያገኙ የሚችሉበት ጊዜ ነው። ሴቶች ወደ ቤት ይመለሳሉ፣ ከዚህ በኋላ ለመታጨትና ለማግባት ብቁ ናቸው። የፀጉር አሠራራቸውም ይቀየራል። ቀሚሳቸውም ረጅም እና በጨሌና በዛጐል ያጌጠ ይሆናል። በተጨማሪም፣ የአንገት ጌጥ፣ ቀለበትና አልቦ ያደርጋሉ። በሕዝብ መካከል ስትሆን ከዘንባባ ቅጠል የተሠራ ጃንጥላ ትይዛለች (ገጽ 137-139)።

ወንዶች ካልተቆረጠች ሴት ጋር ግንኙነት ስለማያደርጉ፣ ከመቆረጥ በዓል በፊት ማንኛዋም ሴት አትያዝም ወይም አትደፈርም። አንዴ ከተቆረጠች በኋላ ግን እነዚህ ነገሮች ሊያጋጥሟት ስለሚችሉ በሕዝብ በዓላት ላይ የምትገኘው ከአጃቢ ጋር በመሆን ነው። ይህም ሰው ከፈላጊዎቿ ጋር የሚኖራትን ንክኪ ሁሉ በጥንቃቄ ይቆጣጠራል። ከተቆረጠች በኋላ በቶሎ መታጨቷን ወላጆቿ ይፈልጉታል።

ጉራጌዎች

በጉራጌዎች ዘንድ ግርዘት እና መቆረጥ፣ የልጃገረዶችና የወጣት ወንዶች የጉልምስና ሥርዓት ዋነኛው አካል ነው። በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶችና ሴቶች በአንድነት ተሰብስበው ቂንጥር በመቁረጥና በመግረዝ በአንድ ላይ የሚፈጸመው ሥርዓት ቴባር ይባላል። የሚደረገው በበጋ ወቅት ነው። ሥርዓቱ ከልጅነት ወደ አዋቂነት የመሸጋገር ምልክት ነው። ከመቆረጡ ሥርዓቱ በኋላ በቤት ውስጥ ወይም ለዚህ ዓላማ ተብሎ በተዘጋጀው ጎጆ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች በተለያየ ስፍራ እንዲሆኑ ይደረጋል። በዚህ ወቅት የተቆረጡት ልጃገረዶችና የተገረዙት ወንድ ልጆች ለጸታቸው የተለየን ሥራ መሥራት ይማራሉ። የሚያስተምሯቸው ለሴቶች ሴቶች ለወንዶችም ደግሞ ወንዶች ናቸው። ይህ የቆይታ ጊዜያቸው ሲያበቃ፣ ወንዶቹ የተለየ የመውጣት ሥርዓት አላቸው። ሴቶቹ ደግሞ ሚዌት በሚባል ሌላ ሥርዓት ውስጥ ያልፋሉ። ይህ

ሥርዓት ከወላጆቻቸው አስተዳደር በመለየት የ«ፋጋ» አለቃ በተባለ ሥልጣን ሥር ወደ አንድ ዕድሜ ቡድን ይቀላቀላቸዋል። ይህ ከልጅነት ወደ ትዳር መሸጋገሪያ ሲሆን፣ ሴቶቹ ሲያገቡ በባላቸው ሥልጣን ሥር ይሆናሉ (ሻክ፣ ገጽ 131-133)።

ፋጋ ተገልለው ካሉት ብሔረሰቦች መካከል ሲሆኑ፣ በመላው ኢትዮጵያ ይገኛሉ። በቡድን ስማቸው ዋታ በመባል ይታወቃሉ። በሙያቸውም የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች እና አዳኞች ሲሆኑ፣ ፋጋዎች የሥርዓቱም አዋቂዎች ናቸው (ሻክ፣ 8-12)። ዋታዎች በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ ጎሳዎች ጋር የደንበኝነት ግንኙነት መሥርተዋል። በሚጋበዙበት ጎሳ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትንና ሥራን ያከናውናሉ። ለእነዚህ የተገለሉ ማኅበረሰቦች የሚሰጧቸው ስሞች የተለያዩ ናቸው። ለምሳሌ፣ ፋጋ የሚለው ስም ከጉራጌ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተሰጣቸው ነው። ፋጋ አደን ያድናል፣ የእንጨት፣ የቆዳና የብረት ሥራዎችን ይሠራል። እነዚህ ሥራዎች ከርኩሳን መናፍስት ጋር የተገናኙ እንደ ሆነ ስለሚታሰብ፣ ፋጋ ኃይለኛ አስማተኛና ቡዳ ነው ይባላል። ፋጋ ጉራጊኛ ይናገራል። ነገር ግን «ፊድዋት» የሚባል በሥርዓቱ ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ አለው። ይህን ቋንቋ በሥርዓቱ ወቅት መነጋገሪያ ከመሆኑ በተጨማሪ የጉራጌ ሴቶችም ይጠቀሙበታል። ፋጋ ለሚሰጡት አገልግሎት በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ይከፈላቸዋል (ሻክ፣ ገጽ 8-12)።

ፓንክረስት እንደ ጻፉት፣ እነዚህ ፋጋ የተባሉት አናሳ ብሔረሰቦች ከወረራው እና ሰዎች ከሌላ አካባቢ ከመፍለሳቸው በፊት፣ በምሥራቅ አፍሪካ ይኖሩ ከነበሩ ማኅበረሰቦች የቀሩ እንደ ሆኑ ይታሰባል። ፓንክረስት ይህንን በተመለከተ፣ ማንነታቸውን እና መነሻቸውን አስመልክቶ በተሰጡት ግምቶች ላይ ጠንከር ያለ ጥያቄን አንሥተዋል (ፍሪማን፣ ገጽ 8-12)። እዚህ ላይ ክርክሩ የተነሣበት ምክንያት ከትልቁ ማኅበረሰብ ውስጥ የተገለሉትን የእነዚህን ጎሳዎች ማንነትና ተግባር መረዳት፣ ግርዘት እና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ሥርዓቶችን ለመለወጥ በሚታሰብበት ጊዜ ስለ እነርሱም አብሮ ማሰብ አስፈላጊ ጉዳይ ስለ ሆነ ነው።

ወላይታዎች

የወላይታ ሴቶች የሚቆረጡት ልክ ከሠርጋቸው በፊት ወይም በኋላ ነው። ሂደቱን የሚያቀናጀው እና የገንዘቡን ወጪ የሚሸፍነው ሙሽራው ወይም ባልየው ሲሆን፣ ድርጊቱ የሚከናወነውም በቤተሰቦቹ ቤት ውስጥ ነው። ሥርዓቱን አስመልክቶ በሚዘጋጀው ድግሥ ላይ ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች ይጋበዛሉ። የእርሱ ቤተሰቦች ሥርዓቱን ለማከናወን አቅሙ ከሌላቸው፣ የሴቷ ቤተሰቦች ድምፃቸውን አጥፍተው ድርጊቱን ያከናውኑታል። በዚህ አካባቢ የሚፈጸመው አቆራረጥ በጣም ትንሽ ስለ ሆነ፣ የጤና ባለሙያ እንኳ አይቶ መቆረጡን ላያውቅ ይችላል። የሥጋ ዘመድ ያልሆነች ሴት የምትቆረጠውን ልጅ ዓይን ትሸፍናለች። ይህንን የምታደርግ ሴት «ጃላ» ወይም ባልንጀራ ትባላለች። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሴቶች የተለየ ቁርኝት ይኖራቸዋል። ጎዘናቸውንና ደስታቸውን አብረው ይካፈላሉ። ግርዘት ለሴቶች በማኅበረሰብ ውስጥ እንደ ሰው ለመቆጠርና ተቀባይነት ለማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል። ከግርዘቱ በኋላ፣ ልጅቱ የተለየ ምግብ እየተመገበች በቤት ውስጥ ታገግማለች። በዚህም ወቅት የዕድሜ እኩዮች ጓደኞቿ እየመጡ ይጎበኟታል፤ ያወራሉ፣ ይጫወታሉ እንዲሁም አብረው ይጨፍራሉ።

የሶማሊያ ሶማሌዎች እና የኢትዮጵያ ሶማሌዎች

ሶማሌዎች የሚፈጽሙት ቆርጦ መስፋት (infibulation) በከፍተኛ ሁኔታ ይታወቃል። የፋሽን ሞዴሊስት የሆነችው ሶማሊያዊት ዋሪስ ዲሬ ያደረገችው ዘመቻ ለድርጊቱ መታወቅ ከፊል ምክንያት ሆኗል። በሶማሌዎች ዘንድ የመቆረጡ ልማድ የአቅመ-ሔዋን መድረሻ ሥርዓት መሆኑ ተለውጦ ለኮረዳነት ያልደረሱ ሕፃናት እንደሚፈጸምባቸው ዋሪስ አስፍራለች። እነዚህ የሚቆረጡቱ ስለሚፈጸምባቸው ነገር በዝርዝር አይነገራቸውም። የሚነግሯቸው ይህ ለእነርሱ የተለየ እና ጥሩ ጊዜ እንደ ሆነ ብቻ ነው። ድርጊቱ የሚፈጸምበት ወቅት እየቀረበ ሲሄድ፣ ልጅቱ የተለየ እንክብካቤ ይደረግላታል፣ በንጥረ ነገር ክምችቱ የዳበረ ምግብም

ይሰጣታል። ቤተሰቦች እንድትቆረጥ ለጂፕሲ ሴት ይከፍሏታል። ይህ ለእርሷ የሚከፈላትን ክፍያ ቤተሰቡ ትልቅ መዋለ ንዋይ እንዳፈሰሰ አድርጎ ይቆጥረዋል። የዋሪስ ግርዘት የተከናወነው በማለዳ በቁጥቋጦ ውስጥ ነበር። በዚህ ወቅት እናቷ አቅፈዋት እና ዓይኖቿን ሸፍነዋት ነበር። ድርጊቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ዋሪስ በትንሽ ጎጆ ውስጥ ተተወች። እስክታገግምም ድረስም እናቷ ምግብ ያመጡላት ነበር (ዲሬ 1999)።

ሌዊስ እንዳሰፈሩት ደግሞ፣ የሶማሌ ልጃገረዶች የሚቆረጡት ዕድሜያቸው ሰባት ዓመት አካባቢ ሲሆናቸው ነው። ድርጊቱ የሚፈጸመው ጥቂት ሴት ዘመዶች ባሉበት በግል ጎጆ ውስጥ ነው። አንድ ልጅ ወይም እኅትማማቾች በአንድ ላይ ሊቆረጡ ይችላሉ። ድርጊቱ መቁረጥን እንዲሁም ለሽንት እና ለወር አበባ መውጫ የሚሆን ትንሽ ክፍተትን በመተው የውጪውን ብልት መስፋትን ያጠቃልላል። ባሏ በጋብቻው ዕለት ምሽት ስፌቱን መተርተር አለበት። በምትወልድበትም ጊዜ ደግሞ ተጨማሪ መክፈት አስፈላጊ ነው (ገጽ 135)።

ሴራሊዮን

ቅኝት

በሴራሊዮን ድርጊቱ 90 በመቶ የሚሆኑትን ሴቶች ነክቷል። ከጠቅላላው ሕዝብ 3 በመቶ የሚሆኑት የቂርዮ ሙስሊሞች ዓይነት አንድን (ቂንጥርን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መቁረጥ) ይፈጽማሉ። የቀሩት ሁሉ ግን ከዚህ የከፋውን መቆረጥ ያደርጋሉ። በአብዛኛዎቹ የሴራሊዮን ማኅበረሰቦች ዘንድ መቆረጡ ከልጅነት ወደ ኮረዳነት የሚተላለፉበት ዘመን ምልክት እንደ ማድረጊያ ሥርዓት ነው። ልጅቷ ሴት የምትሆንበት፣ ግብረ ሥጋ ግንኙነትንና ጋብቻን ለመፈጸም መብት የሚሰጣት ጊዜ ነው።

በሴራሊዮን ይህ ሥርዓት የሚፈጸመው በድብቅ ማኅበረሰብ አማካይነት ሲሆን፤ ድርጊቱን መፈጸም የሚችሉትም እነርሱው ናቸው። እነዚህ ማኅበረሰቦች ሳንዴ ወይም ቡንጆ ይባላሉ። የቡንጆ ጎጆ የሚቀለሰው በቁጥቋጦ ውስጥ ነው። የምትቆረጠው ልጅ

የመቆረጫዋ ጊዜ መድረሱ ሊነገራት ቢችልም፣ ወደ ቁጥቋጦው የምትወሰደው ግን ተታልላ ነው። በዚያም ትጠለፍና ወደ ጎጆው ትወሰዳለች። ብዙ ሴቶች በአንድ ላይ ይቆረጣሉ። ከታሪክ አንጻር ይህ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ለትዳር እና ለአዋቂነት መዘጋጀት የሚጀመርበት ወቅት ነው። ቀደም ሲል ይህ የልምምድ ጊዜ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ይቆይ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ከሁለት ሳምንት ወደ አነሰ ጊዜ ተቀንሷል። ይህም ቁስሉ ለመዳን የሚወስድበት ጊዜ ነው።

ሜንዴዎች

ሜንዴ ከሚዛመዱት የማንዴ ስምንት ጎሳዎች መካከል አንዱ ነው። ማንዴዎች ቁጥራቸው ከአጠቃላዩ የሴራሊዮን ሕዝብ ውስጥ 44 በመቶ ያህል ይሆናል። ከእነርሱ ውስጥ 75 በመቶው የሮማ ካቶሊክ፣ 15 በመቶ ሙስሊሞች፣ እንዲሁም 10 በመቶው ደግሞ የባህላዊ እምነት ተከታዮች እንደ ሆኑ ኮሶ ቶማስ ገልጸታል።

ኩዋርኮፖሜ የተባሉ ጸሐፊ ደግሞ ስለ ሜንዴዎች የጉልምስና ሥርዓት ገልጸዋል። ይህ የመቆረጥ ሥርዓት ወንዶችንና ሴቶችን ወደ ጉልምስና የሚያሻግራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ወደ ድብቅ ማኅበረሰብ የሚገቡበት ነው። ወንዶቹ ወደ ፖሮ፣ ሴቶቹ ደግሞ ወደ ሳንዴ ድብቅ ማኅበረሰቦች ይገባሉ። ትልልቆቹ ወንዶች ወንዶቹን ልጆች ሲመርቁ፣ ትልልቆቹ ሴቶችም እንዲሁ ሴቶቹን ልጆች ይመርቋቸዋል። የፖሮ ሥርዓት ከመፈጸሙ በፊት መሥዋዕት ይቀርብ እና የአለቃው ፈቃድ ይጠየቃል። ጸሐፊው ስለ ሳንዴ (ሴቶች) መሥዋዕት ምንም አላነሣም። ነገር ግን፣ የሴቶች እና የወንዶች ሥርዓት በአንድ ላይ የሚፈጸሙ ከሆነና በማኅበረሰቡ ውስጥ እነርሱም ተመሳሳይ ተግባር የሚያናውኑ ከሆነ፣ በሴቶቹም በኩል መሥዋዕት ሳይደረግ አይቀርም።

በቁጥቋጦው ውስጥ ወዳለው ጎጆ የተወሰዱት ልጃገረዶች በዚያ የሳንዴ ማኅበረሰብ አባላት በሆኑ ሽማግሌዎች ሥልጣን ሥር ይሆናል። ሳንዴዎች ስለ ሰጡት አገልግሎት የልጆቹ ወላጆች ይከፍሏቸዋል። ክፍያው የሚፈጸመው በጥሬ ገንዘብ ወይም

በዓይነት ነው። ሴቶቹ በዚህ ወቅት የቤት ሥራና ታላላቆችን ማክበር ይማራሉ። ከዚያም የሥርዓቱን ፈጻሚዎች በማገልገል፣ የተማሩትን በተግባር እንዲያሳዩ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ወቅት ለሦስት ወራት ያህል ከሌላው ኅብረተሰብ ተለይተው ይቆያሉ። ቂንጥር ተቆርጦ፣ የተለያዩ ሥርዓቶች ይደረጉና መገለሉ እየቀለለ ይሄዳል። ከዚህ በኋላ የመውጣት ሥርዓት ይሆናል። ይህ ሥርዓት የደስታ ጊዜ ነው። በመጨረሻም ልጅቷ ለጋብቻ እንደ ደረሰች ትልቅ ሴት ተደርጋ ትቆጠራለች።

ወጣቶቹ ሴቶች ወደ መጡበት ማኅበረሰብ የሚመለሱት ጭምብል በለበሱ የሳንዴ ባለሥልጣን እየተመሩ ነው። የሚመለሱበት ማኅበረሰብ አቀባበል ያደርግላቸዋል፣ ጓደኞቻቸውና ሊያገቧቸው የሚፈልጉ ወንዶችም ስጦታን ይሰጧቸዋል። ሴቶች ወደ እናቶቻቸው ቤት ይሄዳሉ፣ በእዚያም ወደ ሙሉ ሴትነት ደረጃ የመግባታቸው ሥርዓት ለጥቂት ጊዜ ይቀጥላል (ገጽ 117፣ 119፣ 120)።

ኬንያ

ቅኝት

በኬንያ 30 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች የሚቆረጡት ዕድሜአቸው 19 ዓመት ሲሞላቸው ነው። 50 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ 35 ዓመት ካለፋቸው በኋላ ይቆረጣሉ። ከተቆረጡት ውስጥ 65 በመቶ በሚሆኑት ሴቶች ላይ ጥናት ተደርጎ፣ ሴቶቹ የገለጹት እነርሱም ልጆቻቸውን እንደሚያስቆርጡ ነው። በአጠቃላይ ይህ ከ20 ዓመት በታች እና ከ35 ዓመት በላይ ያለው ልዩነት የሚያሳየው ድርጊቱ መቀነሱን ነው። ሦስቱም ዓይነቶች አቆራረጦች በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ይፈጸማሉ።

የሴቶች ውጫዊ ብልትን የሚቆረጡት አንዳንድ ብሔረሰቦች፦

ኪሲ - 97 በመቶ

ማሳይ - 89 በመቶ

ካሌንጂን - 62 በመቶ

ታኢታ ታቬታ - 59 በመቶ

ሊኩዩ - 42 በመቶ

ካምባ - 33 በመቶ

ሚጂኬንዳ/ ስዋሂሊ - 12 በመቶ

ሉሉ /ሉሀያ - 3 በመቶ (በብዛት በጋብቻ መካከል)

የኬንያ አካምባዎች (ምቢቲ እንደ ጸፉት)

ወንዶች የሚገረዙትና ሴቶች የሚቆረጡት ዕድሜያቸው ከ4-7 ዓመት መካከል ሆኖ ነው። ይህኛው ከሦስቱ የጉልምስና ሥርዓት ክፍሎች መካከል የመጀመሪያው ነው። ምንም እንኳ በዕድሜ ልጆች ቢሆኑም፣ ድርጊቱ የሚያመለክተው ልጆቹ ከልጅነት ወደ ጉርምስና መሸጋገራቸውን ነው። ሥርዓቱ የሚደረግበት ቀን ይገለጻል። አዋቂ ወንዶች ወንዶቹን፣ አዋቂ ሴቶች ደግሞ ሴቶቹን ይመርቋቸዋል። በዚህ ወቅት ድፍረት ዋጋ ይሰጠዋል፤ ልጆቹም እንዳያለቅሱ ይበረታታሉ። በማገገሚያቸው ወቅት ዘመዶች፣ የገንዘብ፣ የቀንድ ከብትና የጌጣጌጥ ስጦታዎችን በማምጣት ይጎበኟቸዋል (ምቢቲ 1988፣ ገጽ 122)።

ምቢቲ እንደ ገለጹት፣ ይህ ሥርዓት በተምሳሌትነቱ እትብትን ከመቁረጥ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ የሚያመለክተውም ከመሃንነት እና እውቀትን ከማጣት መለየትን ነው። ይህ በአዲስ ሁኔታ እንደ መወለድ ነው። የሚፈሰው ደም የሚቆረጡትን ልጆች በተምሳሌት ከምድር በታች ከሚኖሩት የቀደሙ አያት ቅድመ አያቶቻቸው ጋር ያቆራኛቸዋል ይባላል። ስለዚህም፣ በሞቱት እና በሕያዋኑ መካከል ያለውን ግንኙነት ያድሰዋል ይባላል። ድርጊቱ ሕመምን መቋቋም ለመልመድ የመጀመሪያው ሥልጠና ነው። ይህ ደግሞ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። አዳዲስ አዋቂዎችን በማጎበረሰባቸው ውስጥ ለመቀበል ስጦታ ይሰጣሉ። ስጦታዎቹም የልጆቹ የመጀመሪያ የግል ንብረታቸው ይሆናሉ። ወጣቱ በማጎበረሰቡ ጭፈራ ላይ እንዲሳተፍ ይፈቀድለታል (1988፣ ገጽ 123)። ግርዘት/መቆረጥ ልጆችና አዋቂዎች የሚለዩበት የማጎበረሰቡ ምልክት ነው።

አጂኩዩዎች (በጋቺሪ የተደረገ ጥናት)

የኮረድነት መጀመሪያው ላይ ሴቷ የመቆረጫዋ ጊዜ መድረሱ ምልክት የሆነውን ጆሮዋን የመበሳት ፈቃድ ለማግኘትና ምርቃት ለመቀበል ወደ አሳቷ ዘንድ ትሄዳለች። ምርቃቱን ተከትሎ በእናት በኩል የአማቶች ግብጣ ይከተላል። ጆሮ የመበሳቱና የመለጠጡ ሂደት ሁለት ወራትን ይፈጃል። ይህ አንዴ ተጠናቅቆ ከተፈጸመ በኋላ፣ ለግርዛት መዘጋጀት ይጀመራል። ምግብ እና መጠጥ የያዙ ጓደኞች በሰልፍ ወደ አጎቶቿ ዘንድ ይሄዳሉ። አጎቶችም የመገረዙ ሥርዓት እንዲጀመር ከመፍቀዳቸው በፊት አንድ ኮርማ ለመክፈል ቃል ይገባሉ።

የምትቆረጠውን ሴት የምትንከባከብና የድግሱን ምግብ የምታቀርብላት ሞግዚት ትመረጣለች። ይህች ሞግዚት ሆና የምትመረጠው ሴት ለምትቆረጠው ልጅ በሕይወት ዘመኗ ሁሉ የቅርብ ጓደኛና አማካሪ ትሆናታለች። የምርጫውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ለመድኃኒተኛ ሰውዬ ፍየል ይከፈላቸዋል። የመቆረጫው ቀን ሲነገር፣ ሞግዚቷ የምግብ ስጦታዎች ይሰጣታል። ምግብ፣ መጠጥ፣ ዘፈንና ጭፈራ ያለበት ድግስ ይደገሳል። ይህንን ድግስ መደገስ የሚችሉት ባለጠጎች ብቻ ሲሆኑ፣ ድሃ ቤተሰቦች ደግሞ የሀብታም ልጅ በምትቆረጥበት ጊዜ የሥርዓቱ አካል ለመሆን ይጠይቃሉ። ድግሱን የደገሱት ቤተሰቦች ልጅ ሥርዓቱን ትመራለች፣ ከዕድሜ ጓደኞቿም በኩር ትሆናለች። የቀሩት የዕድሜ ጓደኞቿ በድግሱ ያካተታቸውን ቤተሰብ ማሳ በሚቀጥሉት ዓመታት በማልማትና ምርቱን በመሰብሰብ ውለታውን ይመልሳሉ።

በግርዘቱ (መቆረጡ በሚፈጸመበት ቀን) ቁሳዊ ሽልማት የሚገባቸው ጓደኞች የሚቆረጡት ይታጠቡ ዘንድ ወደ ወንዝ ተሸክመዋቸው ይሄዳሉ። በሚመለሱበት ጊዜ የሌቶቹ ጓደኞች የሆኑ፣ ያልተገረዙ ወንድ ልጆች መንገዱን ይዘጉባቸዋል። ወንዶቹ ልጆች ሌቶቹን ጓደኞቻቸውን ለተገረዙ ሽማግሌዎች ይሰጡና ኪሣራቸውን በገንዘብ ያካክሳሉ። የሚገረዙትም በአጎቶች

የተዘጋጀውን ድግስ ይጋበዛሉ። ቃል የተገባው ኮርማ ይሰጣል። ሴቶቹ በሥርዓቱ መሠረት ተዘጋጅተው ወደሚገረዙበት አደባባይ ይሰበሰባሉ። እያንዳንዷ ሴት በአሳዳጊዋ ትያዝና ቆረጣው ይከናወናል። ይህንን ተከትሎ ልጃገረዶቹ ደማቸውን እያንጠባጠቡ እና እየጨፈሩ የመቆረጫውን ስፍራ እንዲዞሩ ይደረጋል። በቆረጣው ወቅት ድንግል ሳትሆን የተገኘች ሴት ከሌሎቹ ሴቶች በከፋ ሁኔታ ትቆረጣለች።

ከዚህ ቀጥሎ ሴቶቹ ወደ ማገገሚያ ይገባሉ። በዚህ ወቅት፣ የተቆረጠችውን ሴት መንከባከብና በጎሣ ውስጥ የአዋቂነት ስፍራ ለመያዝ እንድትችል የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ ማስተማር የሞግዚቷ ሥራ ነው። ልጅቱ ጥሩ ምግብ እና መጠጥ ትወስዳለች። በተጨማሪም፣ ደስ የሚል ወዳጅነትና «አዋቂ» ከመሆን ጋር አብሮ የሚመጣ ማኅበረሰባዊ ክብር ይኖራታል። ከቁስላቸው መዳን ሲጀምሩ፣ ሴቶቹ እርስ በርሳቸው እና በቅርቡ ከተገረዙት ወንዶች ጋር ጊዜ ማሳለፍን ይጀምራሉ። በዚህ አጋጣሚ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚቆይ ጓደኝነት ይመሠርታሉ፤ የዕድሜ ጓደኞቻቸውን ደካማ እና ብርቱ ጎኖችንም ያውቃሉ።

«የመውጣት ሥርዓቱን» ከፈጸሙ በኋላ ልጆቹ የአዋቂ ማኅበረሰብ ሙሉ አባል ሆነው ተቀባይነትን ያገኛሉ። እነዚህ የአዲሶቹ ዕድሜ ስብስብ የሆኑት ወንድ እና ሴት ልጆች ከሞግዚቶቻቸው ጎጆ ውስጥ ይሰበሰባሉ። ሞግዚቶቻቸው ስጦታዎችን ያገኛሉ። ወንዶችና ሴቶች ጎን ለጎን በመተኛት ስምንት ሌሊቶችን ያሳልፋሉ። በዚህ ወቅት እርስ በርሳቸው እንዳይነካኩ ጥብቅ የሆነ ክልከላ አለ፤ በዓይነ ቁራኛ ይጠበቃሉ። በቀን ጊዜ እርስ በርሳቸው ይተዋወቃሉ፣ ማኅበራዊ ግንኙነቶችንም ያደርጋሉ። ይህ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ልጆቹ ወደ አዋቂነት እንደ ተወለዱ ይቆጠራል። ይህ «እንደገና መወለድ» በመባል ይታወቃል። ለሁሉም የገንፎ ቁርስ ግብዣ ይደረግላቸውና የተቆረጡት ልጆች ወላጆች ወደሚሠሩበት ቦታ ሄደው እስከ እኩለ ቀን ድረስ በዚያ ይሠራሉ። ከዚያ በኋላ ልጆቹ ወደየቤታቸው ይበታተናሉ (ጋቺሪ፣ ገጽ 57-77)።

ኬንያዊያን ገራገሮች

ጋቺሪ እንደ ጻፉት፣ በምርምር ወቅት ቃለ ምልልስ ያደረጉላቸው ገራገሮች ሁሉ ለሥራው «ተሹመዋል»። አንዷ ገራዥ «የውስጥ ጥሪ» አለኝ ብላለች። የጥሪውን ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው የባህል ሐኪም ነው። «ጥሪው» ትክክለኛ ሆኖ ከተገኘ የመግረዥ ቢላዋና ዱቄቶች የያዘ ቦርሳ በገራዥ ወገብ ዙሪያ ይታሰራል። አሠራሩንም ለማየት ልምድ ካላት ገራዥ ጋር አብራ ትሄዳለች። ደም ባየች ቁጥር በድፍረትና በብርቱ ስሜት ትንቀጠቀጣለች። እንደዚህ ስትሆን ከስፍራው ገለል መደረግ አለባት (ገጽ 106)። በልምምዱ መጨረሻ፣ ቢላዋ (መቁረጫ) ተቀብላ ልምድ ባለው ቆራጭ ቁጥጥር ሥር በመሆን መቁረጥ ትጀምራለች። በኋላም ሥርዓቱን ለብቻዋ ለማከናወን ብቁ ትሆናለች። ከዚያም ሥራው ለገራዢ የገቢ ምንጭ ይሆናል።

ግብፅ

ቅኝት

97 በመቶ የሚሆኑ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ሴቶች ከ7-12 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ እያሉ ይቆረጣሉ። መቆረጡ ወደ አዋቂነት እንደ መሸጋገሪያ ተደርጎ ይቆጠራል። ከዚህ በኋላ ልጆቹ መጫወት አቁመው የቤት ውስጥ ሥራ እንዲማሩ ይጠበቅባቸዋል። ለመታጨትና ለጋብቻ ብቁ ይሆናሉ። ድርጊቱን የሚያከናውኑት ሴት አዋላጆች ወይም ወንድ የባህል ሐኪሞች ናቸው። ምናልባት ለልጅቱ አዲስ ልብስ ከመሰጠቱ በስተቀር ከሥርዓቱ ጋር ተያይዞ የሚከበር ነገር የለም። ያልተገረዘች ሴት እንደ ወንድ ነች፤ ቂንጥሯም ሊያድግ ይችላል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም መቆረጥ ሴትነትን ያረጋግጣል ይባላል (ኤል- ሐዲ፣ ገጽ 149-150)።

ወግ፣ ንጽሕና፣ ሃይማኖት፣ ድንግልናን መጠበቅ፣ የትዳርን ሁኔታ ማሻሻል፣ ዝሙትን መከላከል እና ለባል ደስታ መስጠት የሚሉት በግብፅ ውስጥ የሴትን ውጫዊ ብልት ለመቁረጥ

የሚሰጡ ምክንያቶች ተብለው በኤል- ሐዲ ተዘርዝረዋል::

እንደ ኤል- ሐዲ አባባል፣ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የወንዶች የበላይነት የሰፈነበትን ማኅበረሰብ ፍላጐት የሚያሟላ ነው:: የጭካኔ ሥርዓት ብላ የገለጸችው፣ በአባቶች ከመታዘዙ የተነሣና ወደ ንጽሕና ያመራል ስለሚባል፣ ድርጊቱ ክብር የመሰጠቱን ነገር ነው:: ከቁጥጥር ውጪ የሆነን የሴቶችን የወሲብ ፍላጎት በመፍራት፣ የወንዶችን ማኅበራዊ እሴቶች ለማርካት ሲባል የሴቶች አካል እንዲለወጥ ያደርጋሉ ብላለች:: ሴቶቹ የማኅበረሰቡ አካል ለመሆን ለአሠራሩ ይገዛሉ (ገጽ 149)::

ምዕራፍ ሦስት::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር እና አካላችን

ስለ ሴት ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚናገሩ ብዙ ጽሑፎች ትኩረት የሚያደርጉት አሠራሩ በሰውነት ላይ በሚያስከትለው ጉዳት እና አደጋ ላይ ነው:: ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ሰዎች ድርጊቱ ትክክል ያልሆነው የሴቶችን እና የሕፃናትን ሕይወት አደጋ ላይ ስለሚጥል ነው የሚል ስሜት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል:: ይህ እውነት ቢሆንም፣ እኛ ግን ነገሩን አንድ እርምጃ ወደ ኋላ ተመልሰን ልንጠይቅ ይገባናል ብዬ አምናለሁ:: ይህም ጥያቄ፣ «አካላችንን ወይም የሌሎችን ጤንነት መጉዳት ትክክል ያልሆነው ለምንድን ነው?» ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ ካልመለስን፣ ባህልና ጤና እርስ በርሳቸው የሚቃረኑበት ሁኔታ ውስጥ እንገባለን:: ሰዎች ጥልቅ በሆኑ የባህል እሴቶች እና በጤና መካከል መምረጥ የግድ ቢኖርባቸው፣ ያለ ጥርጥር ባህል ያሸንፋል:: ነገር ግን፣ ምርጫው በባህል እና ያንን ባህል በሚተካው አንድ እሴት መካከል ቢሆን ያኔ ጉዳዩ ሌላ ትርጉም ይኖረዋል:: የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ግን የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ትክክል አይደለም ብላ ታምናለች:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትክክል አይደለም ብሎ ስለ ተናገረ ነው:: ይህ እውነት ከሆነ እና ትክክለኛ ግንዛቤ ካገኘ፣ የጤናው ጉዳይ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ይሆናል::

በዚህ ምክንያት፣ ለሴት ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ልምድ ምላሾችን መስጠት የምንጀምረው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት እና የሴትን ውጫዊ ብልት ስለ መቁረጥ ምን እንደሚልና እንደማይል በመመርመር ነው:: አንባቢው ይህንን ምዕራፍ በተከፈተ ልብ እና በተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ ያነበው ዘንድ ይበረታታል::

ዳዊት ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፦

አቤቱ፣ አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤
በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሠራኸኝ።
ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤
ሥራህ ድንቅ ነው፣ ነፍሴም ይህን በውል ተረድታለች።
እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣
ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም፤
በምድር ጥልቀት ውስጥ በጥበብ በተሠራሁ ጊዜ፣
(መዝሙር 139:13-15)።

ይህ መዝሙር እግዚአብሔር እንዴት ባለ ጥንቃቄ ሕጻናትን በማኅፀን ውስጥ እንደሚያበጅ የሚያሳይ ውብ ሥዕል ይሰጣል። «አበጃጅተህ ሠራኸኝ» እና «በተሠራሁ ጊዜ» የሚሉት ሐረጎች በጥንቃቄ የታቀደንና በደንብ የተሠራን ውብ የጥበብ ሥራ ያመለክታሉ። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ፍጥረቱን በጥንቃቄ ፈጥሯል።

ጳውሎስ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፦

እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 3:16-17)

ለመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤ በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። (1ኛ ቆሮንቶስ 6:19-20)

እነዚህ የጳውሎስ ጠንካራ ቃላት ናቸው። በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተናል። ኢየሱስ የኃጢአት

ቅጣታችንን ለመክፈል ሞተ። ይህንን ባደረገ ጊዜ፣ መንፈሳችንንና አካላችንን ዋጀ። በ1ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ፣ ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ በክርስቶስ የሞቱት እንደሚነሡ ተነግሮናል። በዚያን ጊዜ አካላቸው ይታደሳል። ኢየሱስ ራሱ ለተከታዮቹ በአካል ተገልጦ ታይቷል። ያረገው በአካል እንደ ሆነ ሁሉ፣ የሚመለሰውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ሆነ ተነግሮናል። ስለዚህም ጳውሎስ እግዚአብሔርን በአካላቸው ያከብሩት ዘንድ ለአንባቢዎቹ ይናገራል። የራሳችንን ወይም የሌሎችን ሰዎች አካል የሚጐዳ ማንኛውንም ነገር ማድረግ፣ እግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እንደ ማዋረድ ነው። እግዚአብሔር እንወዳለን እያልን፣ አካላችንንና የትዳር ግንኙነትን የምንጐዳ ከሆነ፣ እርሱንም እንጎዳዋለን። አካላችንን የምንቆርጥ ከሆነ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለእኛ የሠራው ሥራ እንዳልገባን እናሳያለን። አማኞች ቤተ ክርስቲያንን ስለ ሠሯት፣ አካላችንን መጉዳት መንፈስ ቅዱስ የሚኖርበትን ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ መቅደስ ማፍረስ እና መደምሰስ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለየ ሁኔታ የምናየው የአካል ክፍል፣ የሰው ልጅ ብቻ የሆነ ነው። የሰው የወሲብ አካላት በጣም የተለየ ሚና አላቸው። ልዩ የሆኑት ለመራቢያነት ስለሚያገለግሉ ብቻ ሳይሆን፣ ለትዳር ግንኙነትም ስለሚጠቅሙ ጭምር ነው። የትዳር ግንኙነት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዲኖረው የሚፈልገውን ግንኙነት የሚያሳይ ምሥል ነው። የትዳር ግንኙነትን የሚጐዳ ማንኛውንም ነገር ስናደርግ፣ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚወደን እና እንዴት ከእኛ ጋር ኅብረት ሊያደርግ እንደሚፈልግ የሚያሳየውን ምሥል ይጐዳል። አሁን ለጌታ እግዚአብሔር ሰዎችን ልዩ አድርጐ የሠራበትን መንገድ በቅርበት እንመረምራለን። እግዚአብሔር የፈጠረው የትኛው መንገድ እንደ ታላቅ እና ተበላሽቶ መቀጠሉ ለሰይጣን ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነ ለውጥ እንመለከታለን። በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት ምን እንደሚል በቅርበት እናያለን።

ወሲባዊነታችን፣ ፍጥረት እና ውድቀት

እግዚአብሔር ፈጠረ

እግዚአብሔር ልናያቸው፣ ልንነካቸውና ልናሽትታቸው የምንችላቸውን ነገሮች ሁሉ ፈጠረ። በዓይናችን ልናያቸው የማንችላቸውን እንደ መላእክት ያሉትን ፍጡራንም ፈጥሯል። ከመላእክቱ መካከል ጠንካራ የነበረው ሉሲፈር ሲሆን፣ እርሱም በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀ። ሉሲፈር እንደ እግዚአብሔር ሥልጣን እንዲኖረው ፈለገ። ይህንን በመፈለጉ ምክንያት፣ ሉሲፈር ከሰማይ ታገደ። ይህንን ያደረገው መልአክ ሰይጣን በመባል ሲታወቅ፣ እርሱን የሚረዱት መላእክት ደግሞ አጋንንት ይባላሉ። እግዚአብሔር መላእክትን ከፈጠረ በኋላ ሰማይን፣ ምድርን፣ ፕላኔቶችን እንዲሁም ወንዶችን እና ሴቶችን ፈጠረ። በመጀመሪያ፣ አዳም የተባለውን ሰው ፈጠረ። እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት አኖረው። በዚያም ደስ እንዲሰኝ አደረገው፣ በተጨማሪም ለእንስሳትን ሁሉ በስም የመሰየም ሥራን ሰጠው። ከዚያም እግዚአብሔር አዳም ብቻውን እንደ ሆነ አየና አብራው የምትሆንና የምትረዳውን ሴት ፈጠረለት። እግዚአብሔር ሰውን ሲሠራ የተፈጠረው ሁሉ መልካም ነው ብሎ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፣ እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ከሠራ በኋላ ግን፣ «እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ።» አለ ይላል (ዘፍጥረት 1:31)። ሴት ከወንድ የተገኘች ደግሞም ለወንድ የተሰጠች ልዩ ስጦታ ነች።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወንድም ሆኑ ሴት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል ይላል። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ፍጥረትን እንዲገዙ ነግሯቸዋል። ዘፍጥረት 2:15፣ «እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት» ይላል። ይህ ገዥነት በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር አምሳል አንድ ገጽታ ነው። በሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር እና ፍጥረትን

በመንከባከብ መካከል ግንኙነት እንዳለ ይናገራል። ምሳሌ 12:10 ሲናገር፣ «ጻድቅ ሰው ለእንስሳቱ ይራራል» ይላል። እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያለመንከባከብ፣ እግዚአብሔርንና አጽናፈ ዓለምን የፈጠረበትን መንገድ እንደ ማጥፋት ነው። ሰዎች ፈጠራን በመፍጠርም የእግዚአብሔርን ምሥል ያንጸባርቃሉ። ሰዎች ኑሯቸውን ለማሻሻል የሚሆኑ አዳዲስ ነገሮችን ለመሥራት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነገር ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ልጆችን በመውለድ ወደ ዓለም ማምጣት፣ የእግዚአብሔርን የፈጣሪነት ክብር ያንጸባርቃል። እርስ በርሳችን እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትና ግንኙነት ማድረግ መቻላችን የእግዚአብሔርን አምሳል የምናንጸባርቅባቸው ሌሎች መንገዶች ናቸው። ሰዎች ለመሥራት እንዲሁም በሥራ ደስ ለመሰኘት ተፈጥረዋል። እነዚህ ሁሉ በውስጣችን ያሉት የእግዚአብሔር አምሳል ገጽታዎች፣ ለወንድም ይሁን ለሴት እኩል ናቸው። ምሳሌ 31:10-31 እንደሚናገር፣ ታታሪ የሆነች፣ ቤተሰቧን፣ ሠራተኞችን እና ድሆችን የምትንከባከብ፣ እግዚአብሔርን የምታከብር ደግሞም ለባሏ ክብር የሆነች ሴት ሁሉም ሰው ሊያወድሳትና ሊያከብራት ይገባል። ሰዎችን ግንኙነት እንዳያደርጉ፣ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዳይጠቀሙ፣ ጤነኛ ልጅ እንዳያሳድጉ፣ አብረው እንዳይሠሩ ወይም ኅብረት እንዳያደርጉ፣ በተለይም በትዳር ውስጥ፣ የሚከለክሉ ነገሮች እግዚአብሔርን ያሳዝናሉ። እግዚአብሔር ፍጥረትን የመግዛት ኃላፊነት ሰጥቶናል። በአምሳሉ የተፈጠረው እና የፍጥረቱ አካል የሆነውን የመንከባከብ የተለየ ኃላፊነት አለብን።

ሰዎች አልታዘዙም

የሴትን የወሲብ ብልት መቁረጥ እግዚአብሔር ለሴቶች፣ ለባሎቻቸው እንዲሁም ልጅ በማግኘቱና አጠቃላዩ የመውለዱ ሂደት አስመልክቶ ያቀደውን ዕቅድ ማበላሸት ነው። ይህ አስደናቂና መልካም ፍጥረት፣ ሴቶችንና ልጆችን በጭካኔና አካላቸውን በሚጎዳ

እንዲሁም እግዚአብሔር በትዳር ውስጥ እንዲኖር የፈጠረውን ደስታ በሚያጎድል ሁኔታ ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ? «ችግሩ ምንድን ነው?» ብለን መጠየቅ አለብን።

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ እና አስደንጋጭ ወደ ሆነው ድርጊት መለስ ብለን ማየት ይኖርብናል። እግዚአብሔር በዔድን ገነት ውስጥ ካስቀመጣቸው ሁለት ልዩ ሰዎች ጋር ሁለት ልዩ ዛፎችንም አብሮ አስቀምጦ ነበር። አንደኛው የሕይወት ዛፍ ነው (ዘፍጥረት 3:24)። ሁለተኛው ደግሞ መልካሙን እና ክፉውን የሚያሳውቅ ዛፍ ነበር። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ «በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። ነገር ግን፤ መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ።» (ዘፍጥረት 2:17)። ይህንን ትእዛዝ የማክበር የመጀመሪያ ኃላፊነት ለአዳም ተሰጥቶት ነበር። ይህ መመሪያ ለአዳም ሲሰጠው ሔዋን ገና አልተፈጠረችም ነበር። ይህ ትእዛዝ እንዲጠብቅ እግዚአብሔር ለአዳም ኃላፊነት ሰጠው።

ሔዋን ከተፈጠረች በኋላ የነበረውን ሁኔታ ለመለል እንድንችል አስቲ ጥቂት ግምቶችን እንጠቀም። ሁለቱም በአንድነት ፍጥረትን ሁሉ የመግዛት ወይም የመንከባከብ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። ይህ የመንከባከብ ኃላፊነት ሥራን ቢጨምርም፣ ሥራው ግን አስደሳች ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም እርስ በርሳቸው ያልተገደበ ግንኙነትን ያደርጉ ነበር። ከዚያም ሰይጣን ሔዋን ከፍሬው መሞከር እንዳለባት አሳመናት። ሔዋን ፍሬውን በተመለከተ ለባሏ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ታውቅ ነበር። እንደምታውቅ የምንረዳው ሰይጣን ሊያሳምናት በሚሞክርበት ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር በተሳሳተ መልኩም ቢሆን በመጥቀሷ ነው (ዘፍጥረት 3:ከ6 ጀምሮ)። ሰይጣን በሔዋን ፊት እንደ እባብ ሆኖ በመቅረብ እግዚአብሔር ከዛፉ እንዳይበሉ የሰጠውን ትእዛዝ ጥያቄ ውስጥ አስገባው። ሰይጣን ሔዋን እግዚአብሔር

የሚያውቀውን ነገር ሁሉ በማወቅ ፍላጐቷ መጣባት። ይህ እንደ እግዚአብሔር የመሆን ፍላጎት ሉሲፈርን ከእግዚአብሔር ሕልውና ያስባረረው ምክንያት መሆኑን ልብ በሉ። ሰይጣን ይህንን የሔዋን ተመሳሳይ የሥልጣን ፍላጎት እርሷ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንድትተላለፍ ለማበረታታት ተጠቀመበት። ሔዋንም አባቡን አዳመጠችና ከተከለከለው ዛፍ በላች።

ይህ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ አዳምም ከሔዋን ጋር አብሮ ነበር። አዳም ሔዋን ስትበላ ተመለከታት። ምናልባትም፣ ምንም ያለመሆኗን ካየ በኋላ፣ እርሱም የግብዣው ተካፋይ ሆነ። ይህ ድርጊት አጽናፈ ዓለም ላይ ሁሉ ተጽዕኖ አደረገ። አዳምና ሔዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእግዚአብሔር ተደበቁ፣ በሁለቱ መካከልም ጠብ ሆነ። ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ኀፍረትና መለያየት በመካከላቸው እንዲሁም በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል ተፈጠረ። አዳም ስለሆነው ነገር ሔዋንን ጥፋተኛ አድርጎ ወቀሳት። ከሆነው ነገርም የተነሣ የእግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ፍጥረት እስከ መጨረሻው ድረስ ተለመጠ። ይህ አሳዛኝ የሆነ የጨለማ ቅጽበት ነበር። በዚህ ነጥብ ላይ፣ ፍርሃት በትዳር እንዲሁም በሰዎች እና በእግዚአብሔር መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ገባ።

እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ

አሁን የደረስነው በጣም አከራካሪ ወደ ሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ማንኛችንም ብንሆን ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር ያለመውደዳችን፣ ክፍሉን በታማኝነትና በቅንነት ለመተርጎም አስቸጋሪ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ቅጣትን፣ መዋጀትንና ተስፋን የተናገረው አስጨናቂ ሁኔታ እያለ ነው። እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ የሚያስከትለው አስከፊ ውጤት በዘመናት ሁሉ የሚታወስ ይሆናል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰይጣንን ረገመው። በኋላም፣ የአዳምና የሔዋን ድርጊት በትዳራቸው እና በሌላው ፍጥረት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳይ ከመንገሩ በፊት፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ የተስፋ ቃል ኪዳንን ሰጣቸው። ሰይጣንን የሚደመስስ አንድ ልጅ ወይም «ፍሬ» ከሴት እንደሚወለድ ቃል

ገባላቸው። ይህም የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ቃል ኪዳን ነበር። ከሔዋን ልጆች መካከል አንዷ ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ወይም የተስፋ ቃል የማስፈጸሚያ መሣሪያ በመሆን በፍጥረት ላይ ያለውን አስጨናቂ ቀን የምትቀለብስ ትሆናለች። ይህንን የሴቷን ዘር በተመለከተ የቃል ኪዳኑ ማጎተም ይሆን ዘንድ ደም አልፈሰሰም። ዘሩ ኢየሱስን የሚያመለክት ነበር። እናም የእርሱ ደም የዚህ ቃል ኪዳን ማጎተም ሆኗል። በዚህ ጊዜ በሁለቱ ሰዎች ውስጥ የተፈጠረውን እፎይታ እና በሰይጣን በኩል የሆነውን የመሸነፍን ጥልቅ ሐዘን ማንም ሊገምት ይችላል።

ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ነገሩን አልጨረሰም ነበር። ልጅ መውለድ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንባት ለሔዋን ነገራት። ይህ አስቀድሞ በእርሷና በባሏ መካከል ከተፈጠረው መካሰስ ጋር ተጨምሮ ስለ ወደ ፊቱ እርግዝናዋ መልካም ነገር አልታያትም። ከአሁን በኋላ ሥራ እና ምግብን ማምረት አስቸጋሪ እንደሚሆንበት ለአዳም ተነገረው። ካለመታዘዛቸው የተነሣ ሁለቱም ሥቃይን በራሳቸው ላይ አመጡ። ከእነዚህ ከሁለቱ ውጤቶች መካከል የትኛውም ሁለት የማይስማሙ ሰዎችን ልጅ ሊወልዱበት ወዳለ ግንኙነት ለማምጣት አመቺ አልነበሩም። ይህም ኃጢአት ግንኙነትን እንደሚያበላሽ የሚያሳይ ግልጽ መልእክት ነው። ይህ ሥቃይ አዳም እና ሔዋን እንዲሁም የእነርሱ ልጆች ሁሉ ከግራ መጋባታቸው የሚያወጣ «ዘር» እንደሚያስፈልጋቸው እንዲያውቁ አደረጋቸው። ይህ የሚወለደው ዘር በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት እንደገና የሚያድስ ተስፋ ሰጠ። ሆኖም ግን፣ ምን ጊዜም ዘሩ ወደ ምድር ቢመጣ የቅድሚያ ትኩረት የሚያስፈልገው ከባድ ግንኙነት በአዳምና በሔዋን መካከል ነበር። አዳም በምግብ ማምረት ሥራ ተጠምዶ ለሚስቱ ጊዜ ባይኖረው ኖሮ ወይም ደግሞ ሔዋን ግጭትንና የልጅ መውለድን ሥቃይ ለመገላገል በምድር ተቃራኒ አቅጣጫ ብትሰደድ ኖሮ ዘሩ አይኖርም (ኢየሱስ አይገኝም) ነበር።

ትዳር በወደቀው ዓለም ውስጥ

በሁለቱ ፍርዶች መካከል ያለው ትንሽ ክፍል በግንኙነት እና ለወደፊት የሰው ዘር ተስፋን የሚሰጥ እንደ ሆነ የጸሐፊዋ እምነት ነው። እግዚአብሔር ሲናገር፣ «ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤ በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በሥቃይም ትወልጃለሽ፤ ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል።» (ዘፍጥረት 3:16)። ይህ፣ በዚህ ምንባብ ላይ ማብራሪያ የሰጡ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ አዳምን እና ሔዋንን የሚለያይ ሳይሆን በእርግጠኝነት ወደ አንድነት የሚያመጣቸው ነው።

ይህንን ማስታወቂያ ከተነገረበት ዐውድ እንዲሁም ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውድ አንጻር መረዳት ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ምንባብ ልንጠይቀው የሚገቡ ሌሎች ጥያቄዎች አሉ። ይህ ማለት ወንዶች በአጠቃላይ፣ ባሎች ደግሞ በተለይ በሴቶች ላይ የወደዱትን ያድርጉ ማለቱ ነውን? የሔዋንስ ፍላጐት አንዳንድ ጊዜ መጥፎና ሊገታ የሚገባው ወይም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጥሩ እና ከአዳም ጋር እንድትቆይ የሚያደርጋት ነውን? ይህ ምናልባትም እንደ አዳምና ሔዋን እንዲሁም እንደ ሁሉም የወደፊት ጥንዶች ሊተገብሩ እንደ መረጡት በረከት ወይም መርገም እነዚህ «ፈቃድሽ/ ፍላጐትሽ» እና «የበላይሽ/ ገዢሽ» የሚሉት ትናንሽ ቃላት ትርጉማቸው ምንድን ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ «ፍላጐት» የሚለውን ቃል ለመረዳት እንሞክር። የአንድን አስቸጋሪ ቃል ትርጉም ለማግኘት ቃሉ በተለያዩ ዐውዶች ውስጥ እንዴት እንደ ተተረጐመ መረዳት ጠቃሚ ነው። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌሎች ሁለት ስፍራዎች ተገልጸአል። በዘፍጥረት 4:7 ላይ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ልጅ ለሆነው ለቃየን ሲናገር፣ «መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፤ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት» ይላል። (የ1954 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ) ቆይቶ ደግሞ፣ ይኸው ቃል በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 7:11 በጋብቻ ግንኙነት ዐውድ ውስጥ ጥቅም

ላይ ውሏል። ቃሉ እንዲህ ይላል፣ «እኔ የውዴ ነኝ፤ የእርሱም ምኞት እኔው ነኝ።»

በሁለቱም ምንባቦች ውስጥ፣ «ፈቃድ/ፍላጐት» የሚለው ቃል አንድን ድርጊት ይፈጽም ዘንድ ሰውን የሚገፋ ጠንካራ ስሜት የሚል ትርጉም አለው። በቃየን ሁኔታ ደግሞ፣ ይህ «ፈቃድ» ምናልባት ሊቆጣጠረው የሚገባ ቅናት እና ቅሬታ ነው። ቃየን ይህንን ያለማድረጉ ግን ወንድሙን አቤልን ወደ መግደል መራው። በፍቅረኛ ሁኔታ፣ «ፈቃድ» ጥሩና ይከታተለውም ዘንድ በአፍቃሪው የሚበረታታ ነገር ነው። የሚያመለክተውም ፍቅረኞች በአካል፣ በስሜት እና በመንፈስ አንድ ለመሆን ያላቸውን ጠንካራ ግፊት ነው።

ከእነዚህ ሁለት ምንባቦች አንጻር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች የሚሉት በዘፍጥረት 3:16 ውስጥ ፍላጐት/ፈቃድ የሚለው ቃል ቀጥለው ከቀረቡት ሁለቱ ዝርዝር አሳቦች መካከል አንዱን ለማመልከት የተጠቀሰ ነው። ሔዋን ባሏን ለመቆጣጠር እና ለማሞኘት ያላትን ፍላጐት ለማመልከት፣ ወይም ደግሞ ከአዳም ጋር አካላዊ ግንኙነት ለማድረግ ያላት ታላቅ መሻት ልጅ የመውለድን ሥቃይ እንድትረሳ አድርጓታል የሚል ትርጉም አለው።

ይህ ምንባብ ሁለቱም ትርጉም ያስፈልገዋል ብዬ አላምንም። ቃሉ የተጠቀሰበት ዐውድ «ፈቃድ» የሚለውን ቃል እንድንረዳ የሚያደርገን ልጅ ከመጸነስና ከመውለድ ሂደት አንጻር ነው። ይህ ቃል ለሔዋን ከተነገረ ከብዙ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ከቃየን ጋር ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ቃሉን ደግሞ ሲጠቅሰው፣ «ፈቃድ» የሚለው ቃል መጥፎ ነገርን እንደሚያመለክት እንድንቆጥር ያደርገናል። «ፈቃድ» የሚለውን ቃል አሉታዊ ወይም አሰጋጋቢ እንድምታ እንዲኖረው የሚያደርገው የምንሻው ነገር እንዲሁም ያሻንን ነገር ለማግኘት የምናደርገው አካሄድ ነው።

ቃየን ክፉ የሆነውን ምኞቱን ሊቆጣጠር ይገባው እንደ ነበረ ሁሉ፣ ሔዋንም እግዚአብሔር የሰጣትን መሻት በባሏ እና

በእግዚአብሔር የፍቅር ቁጥጥር ሥር ማድረግ ነበረባት። ይህንን ስታደርግ፣ ፈቃዷ ትዳሯን የሚያጠናክር አምንታዊ ትርጉም ይኖረው ነበር። ቃየን ፈቃዱ እንዳይቆጣጠረው እና ከወንድሙ ከአቤል ጋር ያለውን ግንኙነት እንዳይገዛ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሔዋንም የትዳር ግንኙነቷን እንድትቆጣጠረውና እንዳሻት እንድታደርገው አልተፈቀደላትም ነበር። ቢሆንም ግን፣ ባሏ አዳም ይረዳት ዘንድ በአጠገቧ ስላለ የነበረችበት ሁኔታ ከቃየን በተሻለ ነበር። ሰይጣን ሊፈትናት በመጣ ጊዜ፣ ሔዋን እግዚአብሔርን አልሰማችም፣ አዳም ደግሞ ለሚስቱ ምሪት የመስጠት ኃላፊነቱን አልተወጣም ነበር። ሊሆን የሚገባው ሔዋንም ባሏን መስማት ነበረባት፣ አዳምም ደግሞ መመሪያ መስጠት ነበረበት።

ይህ በወንድና በሴት ወይም በሚስትና በባል መካከል ያለው የአካል ግንኙነት የመጣው በቀጣዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ብዙ ጊዜ፣ ወንድ ኃጢአትን ለማድረግ ሲፈተን፣ የወሲብ ፍላጎቷን ተጠቅማ በእርሱ ላይ የምትሠለጥን ሴት ትኖራለች። በዮሴፍና በጲጥፋራ ሚስት መካከል የሆነው ነገር እንደዚህ ነበር። ቤርሳቤህም ዳዊት ሊያይ በሚችልበት ስፍራ ላይ ሆና ትታጠብ ነበር። ደሊላም የአገሩን ምሥጢር ከሳምሶን ያገኘችው በዚህ መልኩ ነበር። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ተጠያቂ የሚያደርገው ወንዱን ነው።

አሁን ደግሞ «መግዛት» የሚለውን ቃል እንመልከት። ይህ ገዥነት (የበላይነት) በትዳር ግንኙነት ውስጥ እንዴት ይፈጸማል? እግዚአብሔር አዳም የሔዋን ገዢ (የበላይ) ይሆናል ሲል ምን ማለቱ ነው? ለመገንዘብ እንዲረዳን በተቀረው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ቃሉ እንዴት ጥቅም ላይ እንደ ዋለ አንድ ጊዜ በድጋሚ እንይ። ቃሉ በተለያዩ ዐውዶች ውስጥ ጥቅም ላይ መዋሉን እናያለን። በመጀመሪያ፣ አዳምና ሔዋን ምድርን ግዙዋት ተብለው በታዘዙበት ጊዜ ከተገለጸው ቃል ጋር አንድ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። ይሁን እንጂ ቃሉ፣ በዘፍጥረት 1:16 ላይ

የተጠቀሰው ቃል ነው። እዚህ ጋ ፀሐይና ጨረቃ በቀንና በሌሊት ላይ እንዲሠለጥኑ ተደርገዋል። ይኸውም ሥርዓት የሌለውን ነገር ሥርዓት እንዲኖረው የማድረግ አሳብ አለው። በዘፍጥረት 24:2፣ 45:8 ውስጥ «መግዛት» የሚለው ቃል የንብረት ኃላፊ/ ጌታ ወይም የቤት አዛዥ መሆንን በሚያንጸባርቅ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። በዘፍጥረት 37:8 እና 45:26 ውስጥ ደግሞ መግዛት (የበላይ) የሚለው ቃል ንጉሥ(ገዥ) የሚል ትርጉም ይሰጣል። ይህ ቃል በሌላ ስፍራ በቤተሰብ ወይም በሴት እና በወንድ ግንኙነት ዐውድ ውስጥ አልተጠቀሰም። ስለዚህም፣ በአዳምና ሔዋን መካከል ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ የሚረዳን ጥቂት ፍንጭ ነው ያለው። ስለዚህም በዚህ ጥቅስ ገዥነት አጥፊ ወይም ጉጂ አይደለም ለማለት እንችላለን። ይልቁንም፣ ሥርዓትን የሚያስጠብቅ እና በሥርዓቱ የሚገኘውን ደኅንነት የሚያረጋግጥ ነው። ሁለቱም ማለትም ወንድ እና ሴት አሁንም በተቀሩት ፍጥረታት ላይ የመሠልጠን ኃላፊነት አለባቸው። ወንዶች በሴቶች ሁሉ ላይ የመግዛት ሥልጣን የላቸውም።

እግዚአብሔር በተጋቡ ጥንዶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማድነቅ እና ገዥነት በሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ ለማየት ወደ አዲስ ኪዳን መሄድ አለብን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደደ ሁሉ ባሎችም ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ተነግሯቸዋል (ኤፌሶን 5:25)። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደደው እንዴት ነበር? እርሱ እኛን የወደደን አባቱን ታዞ ወደዚህች ዓለም በመምጣት፣ ለ30 ዓመታት በኃጢአት ቢፈተንም እንኳ፣ ፍጹም የሆነ ሕይወትን በመኖር፣ ከዚያም በኃጢአታችን ምክንያት የሚደርስብንን ቅጣት ለማስወገድ በመሞት ነው። ፍጥረትን ከመግዛቱ በተለየ መልኩ፣ አዳም በሔዋን ላይ ያለው ገዥነት፣ ለእርሷ ለመኖርና ለመሞት መዘጋጀት ይጠበቅበታል። በቆላስይስ 3:19 ውስጥ፣ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ እንጂ መራራ እንዳይሆኑባቸው በድጋሚ ተነግሯቸዋል። በ1ኛ ጴጥሮስ 3:7 ውስጥ ደግሞ ጸሎታቸው እንዳይከለከል ባሎች ለሚስቶቻቸው ዋጋ የሚሰጡ እና የሚያከብሯቸው እንዲሆኑ

ተነግሮናል። ገዢ መሆኑ የወሲብ ፍላጎታቸውን ለመቆጣጠር ሲባል የሴቶችን ብልት ለመቁረጥ ፈቃድ አይሰጥም። በዚህ በመወደድ ዐውድ ውስጥ ሴቶችም እንዲገዙ ተነግሯቸዋል።

እግዚአብሔር የሰዎች ግንኙነት እንደዚህ እንዲሆን ካደረገ በኋላ፣ በሰዎች እና በራሱ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደገና ደነገገ። ከገነት አስወጣቸው። ግን ለምን? በተለየ ሁኔታ የተገለጹ ሁለት ዛፎች እንደ ነበሩ ታስታውሳላችሁ። እነርሱም መልካም እና ክፉውን የሚያሳውቁ እና የሕይወት ዛፍ ናቸው። አዳም እና ሔዋን የዘላለም ሕይወት እንዳላገኙ፣ ከእግዚአብሔር መለየታቸውን ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነበር። «የሴቲቱ ዘር» ፍሬው መጀመሪያ መምጣት እና ሰይጣንን ማሸነፍ እንዲሁም የኃጢአትን የሞት ዋጋ መክፈል ነበረበት። «ከሕይወት ዛፍ» እንድንበላ የተጋበዝነው ኢየሱስ ሞት እና ትንሣኤ በኋላ ነው። ይህ ዛፍ የክርስቶስ የራሱ ምሳሌ ነው። የዘላለም ሕይወት ስጦታን የምንቀበለው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ትክክለኛ ግንኙነት ነው። ይህም ማለት፣ ኢየሱስ የኃጢአት ዕዳችንን መክፈሉን ከተቀበልን በኋላ ነው። ይህንን የዕዳ ክፍያ ካልተቀበልን፣ ከእግዚአብሔር ጎብረት ውጭ እንሆናለን፣ ለዘላለም ይፈረድብናል። አዳምንና ሔዋንን ከዔድን ገነት በማስወጣት፣ እኛ እና እነርሱ (ሁላችንም) ኃጢአታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ተወግዶ፣ ከሕይወት ዛፍ ለመብላት እንድንችል አደረገ።

በቀጣይ የምሕረት ድርጊቱ፣ እግዚአብሔር ሁለት ልጆቹን የእንስሳ ቆዳ አለበሳቸው። ልብስ ለማግኘት የደም መፍሰሱ አስፈላጊነት ኃጢአት በመሠራቱ ደም መፍሰስ እንዳለበት የሚናገር ምሳሌ ነው። በብሉይ፣ ቃል ኪዳን በደም ይገለጥ ነበር፣ እግዚአብሔር ይቅር ማለቱንና ኃጢአትን ማስወገዱን እንደ ምሳሌ ለማሳየትም መሥዋዕት ይቀርባል። በግርዘት ደምን ማፍሰስ ከእነዚህ ምልክቶች መካከል አንዱ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለተነሣው ርእሰ ጉዳይ፣ ግርዘትን እግዚአብሔር ለሴቶች እና ለወንዶች ካለው ዓላማ አንጻር መረዳት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም

ከዚህ ቀጥለን የምናየው ግርዘት በብሉይ እና በአዲስ ኪዳናት ውስጥ ነው።

ግርዘት በብሉይ ኪዳን

አቶ ተሾመ ነጋሽ እንዲህ ጽፈዋል፡-

«ከትንሽ ጊዜ በፊት ሴት ልጅ የወለደች ጓደኛዬን ለመጎብኘት ሄድኩ። ስለ ሰጦታውም እግዚአብሔርን አመሰገንን። እዛም በጨዋታ መሐል የሴቶችን ግርዘት ጉዳይ አነሣን። እኔም በዚያው የወለደችውን ጓደኛዬን ልጇን በተመለከተ ምን እንዳሰበች ጠየቅኳት። እርሷም፣ ከ80 ቀን በኋላ የምታስገርዛት መሆኗን በመግለጽ በፍጥነት መለሰች። በጣም ደነገጥኩ።

ውይይቱ በጣም ተጧጧፈ። በቤቱ ውስጥ ባለን ሰዎች መካከል የአሳብ መለያየት ሆነ። እናቲቷ፣ ልጂቱ ካልተገረዘች ቂንጥሯ አድጎ የብልቷን አፍ እንደሚሸፍነው ተናገረች (ለነገሩ ቂንጥር የአተር ፍሬ ከማክል የበለጠ አያድግም)። እኔም በንግግሯ በመገረም፣ የምትለው ነገር ከምሯ እንደ ሆነ ጠየቅኳት። እርሷም እውነቷን መሆኑን በድጋሚ አረጋገጠችልኝ። በእርግጥ በእነዚህ ሴቶች እምነት ተበሳጨሁ። ቂንጥር የሚያድግ እና የብልትን አፍ የሚሸፍን ከሆነ እግዚአብሔር ለምን ፈጠረው? እግዚአብሔር በእኛ አካል አይቀልድም። በእርግጥ፣ እንዲህ ዓይነት የውሸት መረጃ «ከተማሪች» እናት መሰማት ያሳዝናል። በተጨማሪም እናቲቱ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ የቃል ኪዳን ግንኙነት ግርዘት መፈጸም እንዳለባትም ታስባለች። እግዚአብሔር ግን፣ የሴትን ውጫዊ ብልት ሰለ መቁረጥ (ግርዘት) ምንም ነገር አልተናገረም። የተሳሳተ እምነት ሰለባ ስለሆኑት ምስኪን ሴቶች ሐዘን ተሰማኝ።»

በዘፍጥረት 12:2-3 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ ብሎ ተናግሯል፡-

«ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ ደግሞም እባርክሃለሁ፤ ለሌሎች በረከት ትሆናለህ። የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ በአንተ አማካይነት

ይባረካሉ::»

ከሔዋን ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን በእርሷ ታዛዥነት ላይ የተመሠረተ አልነበረም:: በተመሳሳይ መልኩ፣ ለአብርሃም ቃል ኪዳን የተሰጠው ያለ ምንም ቅድመ- ሁኔታ ነበር:: ለሁለቱም የተሰጡት ተስፋዎች፣ የሰዎችን ከዘላለም ጥፋት መዳን የሚመለከቱ ናቸው:: ከትንሽ ጊዜ በኋላ፣ እግዚአብሔር ይህንን ቃል ኪዳን ከአብርሃም ጋር እንደሚያረጋግጠው ተናገረ:: ለዚህ ቃል ኪዳን እንደ መታሰቢያና ምላሽ አድርጎ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ «አንተና ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠብቁት ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ::» (ዘፍጥረት 17:2፣10)::

ለግርዘቱ የተሰጠው ትእዛዝ በጣም ግልጽ ነበር:: ይኸውም ወንዶች ሁሉ እንዲገረዙ ነው:: የሚገረዙትም በተወለዱ በስምንተኛ ቀናቸው ነበር:: ከስምንት ቀን በላይ የሆናቸው ወንድ ልጆች እና ትልልቅ ሰዎችም መገረዝ ይችሉ ነበር:: ያለመገረዝ ሰውየውን ከቃል ኪዳኑ በረከት ውጭ ያደርገዋል:: ግርዘቱና ተከትሎት የሚመጣው በረከት የአብርሃም ቤተሰቦች አባል ለሆኑት ሁሉ የሚሆን ነበር::

አባቶቻቸው ስለ ተገረዙ ሴቶችም በቃል ኪዳኑ ውስጥ ይጠቃለሉ ነበር:: እግዚአብሔር በግርዘት ተምሳሌትነት የሰውን ዘር ይባርካል:: በመፀነስ ወቅት ባርኩቱ ወደ ልጆች ያልፋል:: ተምሳሌቱ ሴቶች እንዲገረዙ አይጠይቅም:: የሴቲቱ ዘር በውስጧ ስለ ሆነ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ተምሳሌታዊ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም:: እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው እርሱ ላይ ጉዳትን ሳያደርስ ሊቆረጥ ከሚችል ቁራጭ ቆዳ (ሽለፈት) ጋር ይመሰላል:: በሴቶች አካል በየትኛውም ስፍራ እንደዚህ ዓይነት ቁራጭ ቆዳ (ሽለፈት) የለም::

እግዚአብሔር ይህንን እና ቀጣዮቹን ቃል ኪዳኖች ሁሉ ለማረጋገጥ ደም ማፍሰስን ተጠቀመ:: ይሁን እንጂ፣ ይህ ምልክት የሰዎችን ልብ እንደማይቀይር ወዲያውኑ ግልጽ ሆነ:: ከእያንዳንዱ

ቃል ኪዳን ጋር የደም መፍሰሱ በቂ እንዳልሆነና ሕጉን ጠንቅቆ በሚፈጽም አንድ ሰው አማካይነት የተገረዘ ልብ ማስፈለጉን የሚያሳይ ፍንጭ ነበር። በዚሁ ጉዳይ ላይ ሙሴ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፤ «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ እንድትወደው፤ በሕይወትም እንድትኖር፣ አምላክህ እግዚአብሔር የአንተንና የዘርህን ልብ ይገርዛል።» (ዘዳግም 30:6)።

በኤርምያስ ምዕራፍ 4 ውስጥ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ወደ እርሱ እንዲመለስ፣ ጣዖቶቻቸውን እንዲያስወግዱ እና መልካም ሕይወት እንዲኖሩ ጥሪ ያደርጋል። ቃሉም እንዲህ ይላል፤ «አናንተ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች፤ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ፤ አለዚያ ስለ ሠራችሁት ክፋት፣ ቁጣዬ እንደ እሳት ይንበለበላል፤ ሊገታውም የሚችል የለም።» (ኤርምያስ 4:4)። በኤርምያስ 9:25 ላይ ደግሞ በድጋሚ፣ የሥጋ ግርዘት ከእግዚአብሔር ቅጣት ለመዳን በቂ እንዳልሆነ እናያለን። ጌታም እንዲህ አለ፤ «ሥጋቸውን ብቻ የተገረዙትን የምቀጣበት ጊዜ ይመጣል፤. . . እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ በእርግጥ የተገረዙ አይደሉምና፤ የእስራኤልም ቤት ሁሉ ልባቸው አልተገረዘም።» በኋላ ኤርምያስ ሲናገር፦ «ከእስራኤል ቤትና፣ ከይሁዳ ቤት ጋር ይላል እግዚአብሔር፤ አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት፣ ጊዜ ይመጣል . . . ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ኪዳን አይደለም፤» (ኤርምያስ 31:31፣32)። እግዚአብሔር ሲናገር፣ «ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እኔ አምላክ እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።» (ኤርምያስ 31:33)። ኢሳይያስ በበኩሉ አገልጋይ እንደሚወለድ፣ እርሱም የቃል ኪዳን ምልክት ሳይሆን ራሱ ቃል ኪዳን እንደ ሆነ፣ እንዲሁም ለአሕዛብ ብርሃን እንደሚሆን ይናገራል (ኢሳይያስ 42:1፣ 6)። ይህ አገልጋይ፣ ሰዎችን ከጨለማና ከግዞት ነፃ ያወጣቸዋል ተብሎ በኢሳይያስ 49:8፣9 ውስጥ ተጠቅሷል።

ግርዘት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይኖራቸው ዘንድ ንጹሕ ልብ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያመለክት ተምሳሌት ነበር። ይህ አሳብ በሌላ መንገድ ሲገለጽ፣ ሰዎች ቅዱስ ከሆነው

ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ ኃጢአት የሌለባቸው እና ፍጹም የተቀደሱ መሆን ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የነበሩት የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ዓይን ንጹሕና ኃጢአት አልባ የሚሆንበትን መንገድ ያለማቋረጥ መፈለግ ነበረባቸው። ለዚህ መንገዱ ኢየሱስ ነበር። እውነተኛ መገረዝ የልብ መለወጥ ወይም የፍላጐት መቀየር ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን የሚያላይ መንፈሳዊ ለውጥ ነው።

ይህንን እውነት ያለማወቅ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ መወዛገብን እና ክርክርን አስነሥቶ ነበር። ከዚህ ቀጥሎን የምናየው ይህንኑ ነው።

ግርዘት በአዲስ ኪዳን ውስጥ

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ወንጌል ወደ አሕዛብ ወይም ወዳልተገረዙ ሰዎች እንደ ሄደ እናያለን። ጌታ ጴጥሮስን በቂሣርያ ወደሚኖረው ቆርኔሌዎስ ወደሚባል ሰው ዘንድ ልኮታል። ከጴጥሮስ ስብከትም የተነሣ፣ ብዙ ያልተገረዙ ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል። መዳናቸውን ተከትሎ ወዲያውኑ አዳዲሶቹ አማኞች መገረዝ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ክርክር ተነሥቶ ነበር።

ጳውሎስም ለገላትያ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የግርዘትን ጉዳይ አንሥቶ ምላሽን ሰጥቷል፤ በአዳዲሶቹ አማኞች ላይ ሕግን የጫኑባቸውንም ኮንኗቸዋል። አሕዛብ የነበረው ቲቶ መገረዝ እንዳላስፈለገው ነግሯቸዋል። ጽድቅ የሚመጣው በእምነት እንጂ ሕግን በመጠበቅ እንዳልሆነ አስረድቷቸዋል። ከአብርሃም በሚወጣ ዘር አማካይነት ዓለም ሁሉ እንደሚባረክ ለአብርሃም የተገባውን የተስፋ ቃል አስታውሷቸዋል። የክርስቶስ ሕይወትና ሞት ደግሞም ከሙታን መነሣቱ ከሕግ የሚበልጥ ደግሞም ሕግን የሚተካ እንደ ሆነ ግልጽ አድርጓል። የሕግ ውጤት ወደ ሞት የሚያመራ የመርገም ጫና ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ራሱ ስለ እኛ መርገም ሆኖ ከሕግ ነፃ አወጣን። የሕጉ ዓላማ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ

ሌላ ፍጹም መንገድ እንደሚያስፈልጋቸው ለአይሁዳውያን እና ለአሕዛብ ማሳየት ነው። ስለዚህም ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ መጨረሻ ላይ ሲናገር እንዲህ ብሏል፣ «መገረዝ ለሚፈልግ ሁሉ ሕግን በሙሉ የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት እንደገና ለእያንዳንዱ በግልጽ እናገራለሁ። በሕግ ለመጽደቅ የምትጥሩ፣ ከክርስቶስ ተለይታችኋል፣ ከጸጋ ርቃችኋል።» (ገላትያ 5:3-4)።

በሮሜ ውስጥ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የገባውን ቃል ኪዳን ለአንባቢዎቹ እንዲህ እያለ ያስታውሳቸዋል፣ «ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ ነው። ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣ በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር ነው።» (ሮሜ 2:29)። በምዕራፍ 4:9-25 ውስጥ ደግሞ አብርሃም የጸደቀው ከመገረዙ በፊት ባሳየው እምነት መሆኑን ጳውሎስ ይገልጻል። መገረዝ ለአብርሃም እና ለአይሁድ ሕዝብ የእግዚአብሔር ታማኝነትና የቃል ኪዳን ምልክት ነው። መገረዝ የእምነት፣ የመዳን ወይም ጸጋን የማግኛ መንገድ ሆኖ አያውቅም።

እነዚህ ምንባቦች፣ የተገረዘ ሰው ደኅንነቱን ያጣል የሚሉ አይደሉም። ይልቁንም፣ ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት በመገረዝ ላይ እምነቱን ከጣለ፣ ኢየሱስን እያመነ አይደለም ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ደግሞ፣ የኢየሱስ ሞት የኃጢአትን ዕዳ ለመክፈል በቂ ስላይደለ ሞቱን ፍጹም እናደርግ ዘንድ አንድ ነገር መሥራት አለብን እንደ ማለት ነው።

ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በሄደ ጊዜ፣ ካልተገረዙ አሕዛብ ጋር ኅብረትን በማድረጉ ተወቅሶ ነበር። ጴጥሮስም እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል እንዴት እየሠራ እንዳለ በነገራቸው ጊዜ፣ የሕዝቡ ምላሽ፡- «ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቷቸዋል ማለት ነዋ» እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ (ሐሥ. 11:18)። ያልተገረዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ስፍራ አስመልክቶ የተነሣው ክርክር እልባት ያገኘ ቢመስልም፣ ኋላ ግን ከይሁዳ እና ከአንጾኪያ የመጡ ሰዎች

ደኅንነት ማግኘት የሚቻለው ሰዎች ሲገረዙ ብቻ ነው የሚል ትምህርት በማስተማራቸው ችግሩ እንደገና አገርሽቷል።

እነዚህ አስተማሪዎች በፈጠሩት ጥርጥር ምክንያት በኢየሩሳሌም ጉባኤ ተጠራ። ይህም ጉባኤ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሠራ ካለው ሥራ አንጻር ተከራክሮ እና መርምሮ እልባትን የሚሰጥ ነበር። በዚህ ውይይት ላይ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ ባርናባስ እንዲሁም ያዕቆብ አስተዋጽኦ አድርገው ነበር። በመጨረሻም፣ አሕዛብ ለመዳን የሙሴን ሕግጋት መጠበቅ እንደማያስፈልጋቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል። አሕዛብ አማኞች ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ማድረግ ይችሉ ዘንድ የተወሰኑትን የአመጋገብ ሥርዓቶች እንዲጠብቁ ተነግሯቸው ነበር (ሐሥ. 15)።

በቈላስይስ መጽሐፍ የልብ ግርዘት ምልክቱ መጠመቅ እንደ ሆነ ጳውሎስ ይናገራል። «የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና፤ እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል። በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፤ እርሱን ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር ኀይል በማመን ከእርሱ ጋር ደግሞ ተነሣችሁ።» (ቈላስይስ 2:9-12)።

ለማጠቃለልም፣ የወንዶች ግርዘት ከግል ወይም ከንጽሕና ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ይደረግ ይሆናል። አዲስ ኪዳን ግልጽ የሚያደርገው፣ ግርዘት ሰውየው በአንድ የተወሰነ ቡድን ውስጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሲል ሊፈጽመው እንደሚችል ነው። ይሁን እንጂ፣ ለሃይማኖታዊ ዓላማ ተብሎ መፈጸም ግን የለበትም። ክርስቶስ በእኛ ፈንታ ሕግን ስለ ፈጸመ፣ ድርጊቱ አያጸድቀንም፣ አስፈላጊም አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ እና የሴቶች መቆረጥ

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ከወንዶች ግርዘት ጋር ተመጣጣኝ አይደለም፣ እንደ ሆነ ተቆጥሮም አያውቅም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትም የለውም። አሳቡ ዝም በመባሉ (ባለመገለጽ)

አማካይነት የተላለፈው መልእክት ጠንካራ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ትምህርቶች ሁሉ ስለ ወንድ ግርዘት የሚናገሩ ናቸው። የሴቶች መቆረጥ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል እንኳ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው።

በፍጥረት አማካይነት የቀረበው አሳብ እንኳ ጠንካራ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ፣ እነዚህ የሴት አካል ክፍሎችን ጨምሮ፣ መልካም ነው። እነዚህ የአካል ክፍሎች በልጅ መውለድ ሂደት እንዲሁም በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጸም ጤናማ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተስማሚና አስፈላጊ ሆነው የተፈጠሩ ናቸው። በሔዋን ዘር አማካይነት ኢየሱስ የመምጣቱ ተስፋ እግዚአብሔር በልጅ መወለድ ላይ ላለው በረከት ማረጋገጫ ነው። ልጅ የመወለዱን ሂደት የበለጠ አደገኛ የሚያደርገው ማንኛውም ድርጊት ከእግዚአብሔር ያልሆነ እና የእርሱም ባርኮት ያልታከለበት ነው። የጋብቻን ግንኙነት የሚያደናቅፍ ወይም የሚያበላሽ፣ ወይም ደግሞ ከጋብቻ ውጭ ያለን የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚያበረታታ ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ለወሲብ እርካታ የተሰጡ ብልቶች ከመጉዳታቸው የተነሣ በጋብቻ ውስጥ ጥንዶች እግዚአብሔር የሰጣቸውን የግብረ ሥጋ ፍላጐት ማርካት ካልቻሉ፣ ሁልጊዜ ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ ለመሞከር መፈተናቸው አይቀርም። አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ፣ ምንጩ የሰይጣን መሣሪያ ለመሆን ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች ኃጢአተኛ ልብ ነው። ስለዚህ ሴት እንድትቆረጥ ማድረግ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሰይጣን ጋር መተባበር ነው።

ትዳር፣ እኛና ወደ እኛ የሚመለከቱ ሌሎች የሚያዩን ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዲኖረው የሚፈልገውን ግንኙነት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱት የሚያስችል ተጨባጭ ግንኙነት ነው። የቤተሰብ ግንኙነት እግዚአብሔር ለእኛ ለመናገር የሚጠቀምበት መንገድ ነው። በዚያም ሙሽራ ለሙሽሪት፣ ወይም ደግሞ አባትና እናት ለልጆቻቸው እንደሚጠነቀቁ፣ እርሱም ደግሞ ለእኛ እንዴት እንደሚጠነቀቅ ያሳይበታል።

ምዕራፍ አራት::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ባህል እና ለውጥ

በዚህም ምዕራፍ ውስጥ፣ ሰዎች ሴቶች ልጆቻቸውን የሚያስቆርጡበትን ምክንያት እንመረምርና ለድርጊቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን:: በምዕራፍ ሦስት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ አካልን ወይም የትዳርን ግንኙነትን የሚጎዳን ድርጊትን እንደሚኮንን አይተናል:: ይህም የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥን ድርጊት ስሕተት ያደርገዋል:: ሆኖም ግን፣ መቆረጥ ከባህል አንጻር ያለውን ጠቀሜታ በጥልቀት ስንመለከት፣ ሁሉም ባህሎች ድርጊቱን ለመፈጸም የሚሰጧቸው ምክንያቶች አሏቸው:: አንዳንዶቹን ምክንያቶች በጉዳይ ጥናት ውስጥ አይተናቸዋል:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ፣ «የሴትን ውጫዊ ብልት ለመቁረጥ የሚሰጡት እነዚህ ምክንያቶች ትክክል ናቸው ወይስ አይደሉም?» የሚል ጥያቄን እንጠይቃለን:: ድርጊቱን ለመፈጸም የቀረቡት ምክንያቶቶች እውነት ሆነው ከተገኙ፣ የታሰበውን ግብ ለመምታት ድርጊቱን የሚተካ ሌላ ነገር እንፈልጋለን:: ድርጊቱን ለመፈጸም የቀረቡት ምክንያቶች ትክክል ካልሆኑ ደግሞ፣ ክርስቲያን ስንሆን ልምዱን ወደ ኋላችን ለመተው የበለጠ እንደፋፈራለን::

ቅኝት

የሴትን ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ምክንያት ከድርጊቱ ጋር አብሮ ከሚሄደው ሥርዓት አኳያ የተለያየ ነው:: እነዚህን ምክንያቶች ልማዳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የሕክምና እንዲሁም የእምነትና የፖለቲካ ብለን ልንከፋፍላቸው እንችላለን::

ወግ አጥባቂዎች (Traditionalists) እንደሚሉት፣ እነርሱ ሴቶችን የሚቆርጡት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ስላደረጉት ነው:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የልጅ ልጆቻቸው ልማዳቸውን እንደሚከተሉ ወላጆች ቃል ይገባሉ:: ልጆችም ቃል ኪዳናቸውን በመጠበቃቸው ምክንያት

ከቀደሙት ጋር የመተሳሰር ክብር ይሰማቸዋል።

ማኅበራዊና ባህላዊ (Socio-Cultural) ምክንያቶች ደግሞ ብዙውን ጊዜ የመቆጣጠር ፍላጐትና መቆረጡ የሚፈጸመው ድንግልናን ለመጠበቅ እና ሚስቲቱን ታማኝ ለማድረግ ነው የሚል አሳብን ያንጸባርቃሉ። ይህ ልማድ አንዳንድ ጊዜ ባል ወደ ውጭ ሲሄድ የሴቲቱን ብልት መስፋትና ሲመለስ ደግሞ እንደገና መክፈትን (deinfibulation) ያጠቃልላል። ቂንጥር ሴትን በወሲብ በጣም ኃይለኛ እንድትሆን ያደርጋታል ይባላል። ስለዚህም ይህንን የሴት ከፍተኛ ስሜት ወንዶች ላያረኩት ይችላሉ የሚል ፍርሃት አለ። ስለዚህም ቂንጥርን ማስወገድ የወሲብ ፍላጐትን ይቀንሳል ይባላል። ደግሞም እርስ በእርሱ በሚቃረን መልኩ (በአያዎው) ድርጊቱ የመጀመሪያውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሂደት ቀላል እንዲያደርገው ነው ይባላል።

ሁለተኛው የማኅበራዊና ባሕላዊ (Socio-cultural) ምክንያቶች ሰብስብ ደግሞ የባሕርይ ቀረጻን ያካትታል። ድርጊቱ ሴቶቹን የበለጠ ዝግተኛ ከማድረጉም በተጨማሪ፣ አመለ ሸጋ ያደርጋቸዋል ይባላል። በተጨማሪም፣ ለቁጥጥር የሚመቹ እና የታመኑ ያደርጋቸዋል ተብሎ ይታሰባል። በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ ያልተገረዘች ልጃገረድ ገልጃጃ እንደምትሆን፣ እንዲሁም ዕቃዎችን እንደምትጥልና እንደምትሰብር ይታሰባል። ስለዚህም መቆረጡ የተሻለ የቤት እመቤት ያደርጋታል ተብሎ ይታሰባል።

ከዛም የክብርና የደረጃ ምክንያቶችም አሉ። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የቤተሰብን መልካም ስም ያስጠብቃል። ለቤተሰቡ፣ ለጎሳው እንዲሁም ለሴቷ ማኅበራዊ ክብርን ያስገኛል። የመሸጋገሪያው ሥርዓት ለልጆቹ ትልቅነትን ያሰጣቸዋል፣ የአዋቂነት ቡድኖች አባልም ያደርጋቸዋል። ያለበለዚያ ግን ይገለላሉ። ይህ በሴራሊዮን እና በኬንያም የተለመደ ሲሆን፣ በማሊ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ባሉት ኩናማዎችም ዘንድ ያለ ሁኔታ ነው። ገራገጮቹ፣ ብዙውን ጊዜ ባልቴቶች ናቸው፣ በአንዳንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ክብርንና ዝናን ያገኛሉ።

ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ደግሞ ቆራጮቹ ድርጊቱን እንዲያከናውኑ የሚከፈላቸውን ክፍያ ያጠቃልላል። እነዚህ ሰዎች ሴቷ ስታገባ፣ መቆረጡ በሚፈጸምበት ወቅት የተሰፋውን ብልቷን ሲከፍቱ (ስፌቱን ሲያላቅቁ) ይከፈላቸዋል። ይህ አንዳንድ ጊዜ ከመሬት ወይም ከግመል ውርስ ጋር ይገናኛል። በተጨማሪም፣ ዳጎስ ያለ ጥሎሽ ለማግኘት ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። ልጃ በተቆረጠች ጊዜ ለአባት ስጦታዎች ይሰጣሉ።

ፖለቲካዊ ምክንያቶች ደግሞ በሴት ላይ መሠልጠንንና የቤተሰብና የጎሣን ክብርን ያጠቃልላል። ድርጊቱ ልጃገረዶቹ እንዲያገቡና ካልተቆረጡት ወገን የሆኑትን ማግባት እንደማይችሉ ስለሚያረጋግጥ፣ ለቤተሰቡ ክብር ያስገኛል። አንዳንድ ጊዜ ድርጊቱ ወደ ምሥጢራዊው ማኅበረሰብ መግቢያ ነው። የተቆረጡቱ በማኅበረሰቡ ድጋፍ ለማግኘት ምሥጢራዊ ቡድኑን ይቀላቀላሉ። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ማኅበረሰቦች አንድ ክፍል በሆኑበት ባህል ላይ የማይናቅ ተጽዕኖ አላቸው።

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚፈጸምበት የእድሜ ክልል የተለያየ ነው። ለመቆረጥ የሚሰጡት ምክንያቶች የመቆረጫውን እድሜ ይወስናሉ። ቆረጣው የሚከናወንባቸው አራት ዋና ዋና ጊዜያት አሉ። ልጅቷ ከተወለደች በኋላ ባሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ፣ ወደ አቅመ-ሔዋን እንደ መሸጋገሪያ፣ እንደ ጋብቻ ሥርዓት ወይም የመጀመሪያ ልጅን ከወለደች በኋላ ይደረጋል።

ብዙውን ጊዜ፣ ሁልጊዜም ባይሆን፣ አማራጮች የሚገርዙት ልጂቱ ገና ሕፃን እያለች፣ በስምንተኛ ቀኗ ነው። የወሲብ ፍላጐትን መቀነስ፣ ልጅቱ በመልካም ባሕርይ እንድታድግ፣ ሴቲቱ ገልጃጃ ሆና ዕቃዎችን እንዳትሰብር እና ንጽሕና በልጅነት ለሚደረገው መቆረጥ የሚሰጡ ምክንያቶች ናቸው።

በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ ድርጊቱ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ሲሆን፣ የሚፈጸመውም ልክ የወር አበባ ከማየታቸው በፊት ወይም በኋላ ነው። አንዳንድ ጊዜ ድርጊቱ የጉርምስና ሥርዓት አካል ነው። በሂደት ልጂቱ ሴት ሆነች ይባላል። ይህ ካልተፈጸመ እንደ ሙሉ

ሴት አትቆጠርም፤ ጋብቻ መፈጸምም አትችልም። እነዚህ ማኅበረሰቦች፣ መቆረጥን የሚያስቡት የወሲብ ፍላጐትን ስለሚቀንስ ሴቲቱ እስከ ጋብቻዋ ጊዜ ድረስ ድንግል ሆና እንድትቆይ ያደርጋታል ብለው ነው። ሴቲቱን የበለጠ ዝግተኛ እንዲሁም ተገዢ ያደርጋታል ተብሎም ይታሰባል። ልጆቹ የሚያድጉት መቆረጥ ጥሩ እና አስፈላጊ እንደ ሆነ እየሰሙ ነው። ተለቅ ያሉት ልጆች ከእነርሱ ያነሱትን፡- አስቀያሚ፣ ወንድ የሚመስሉ እና በፍጹም የማያገቡ እንደ ሆኑ አድርገው ይቀልዱባቸዋል። በዚህ መንገድ ልጆቹ በሂደቱ ለማለፍ ፈቃደኞች ይሆናሉ። መቆረጥ ለሴቲቱ እና ለቤተሰቧ ማኅበራዊ ክብር ይሰጣቸዋል። መቆረጥ ዳኅስ ያለ ጥሎሽ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ካለው ባል ጋር ያስገኛል። በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ መቆረጥ የጉርምስና ሥርዓቱ አካል እንዲሁም በምሥጢራዊው ማኅበረሰብ ውስጥ መግባትን ያጠቃልላል። ወደ አዋቂነት ዕድሜ ለሚገቡት የአዲሱ ትውልድ ልጃገረዶች ምትሃታዊውን የሴት ምሥጢር የሚማሩበት ጊዜ ነው።

ሦስተኛው ለመቆረጥ የሚቻልበት ጊዜ ደግሞ ልክ ከጋብቻ በፊት ወይም በኋላ ነው፤ ምናልባትም የጋብቻ ሥርዓቱ አንዱ አካል ሊሆን ይችላል። ለዚህ ከሚሰጡት ምክንያቶች በከፊል በመጀመሪያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት የወንዱ ብልት ወደ ሴቷ የማስገባቱን ሂደት ቀላል ለማድረግ፣ ሴቲቱ ወላድ እንድትሆን፣ በግብረ ሥጋ ለመርካት ከወንዱ ብዙ እንዳትጠብቅ፣ ዝግተኛ እና ታዛዥ እንድትሆን የሚሉት ይገኙበታል። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለሴቲቱ ኃይለኛ ሥቃይ እንዳለው ይቆጠራል። ስለዚህም በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ ሴቷ በግንኙነት ወቅት ትገዛለት ዘንድ፣ ባሏ መምታት አለበት ይባላል። አንዳንድ ጊዜ መቆረጡ የሚደረገው የመጀመሪያ ልጅ ሲወለድ ወይም ከተወለደ በኋላ ነው።

ሁሉም ዓይነት እምነቶች እና ተረቶች የሚናገሩት፣ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ለሰውነት፣ ለአእምሮ እንዲሁም ለአጠቃላይ ንጽሕና አስፈላጊ በመሆኑ ዙሪያ ነው። በዚህ ምዕራፍ የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ባህላዊ ምክንያቶችን ካየን በኋላ፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የጤና ጉዳዮችን እናያለን።

የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ምክንያቶችን የሚመለከቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሾች

«ይህ የእኛ ባህልና ልምድ ስለ ሆነ ስንፈጽመው ኖረናል።»

አንዳንድ ጊዜ ይህ ምክንያት አያት ቅድመ-አያቶቻችን እንዲደረግ ስለሚፈልጉት ቢቆም ይበሳጫሉ እንደ ማለት ነው።

«ስለ ሞተውም ሥጋችሁን አትንጩ፤ ገላችሁንም አትንቀሱት፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘሌዋውያን 19:28)።

ማቴዎስ 10:34-39፦ «በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይመስላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። ሰውን ከአባቱ፣ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፣ ምራትንም ከአማትዋ አለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል። ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፣ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።»

ሉቃስ 16:19-31፡ (ቢቻላችሁ ክፍሉን በሙሉ አንብቡት።) ታሪኩ ሞቶ ወደ ሲኦል ስለ ሄደው ሃብታም ሰው እና ሞቶ እነአብርሃም ወዳሉበት ገነት ስለ ሄደው አልዓዛር የሚባል ድሃ ሰው ነው። በመጀመሪያ፣ ባለ ጠጋው ሰው አልዓዛር ወደ እርሱ ዘንድ መጥቶ እንዲረዳው ፈለገ። አብርሃም ግን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ማለፍ እንደማይቻል ገለጸለት። ከዚያም ባለ ጠጋው ሰው ደግሞ አልዓዛር ወደ ምድር ሄዶ የባለ ጠጋውን ሰው ቤተሰቦች ያስጠነቅቅለት ዘንድ ጠየቀ። «አብርሃም ግን፦ . . . ሙሴ ና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። . . .ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፣ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አይምኑም አለው» (ቁ. 30፣31)።

ሮሜ 12:1-2:- «እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን አግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ አለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።»

የዘሌዋውያኑ ጥቅስ የተወሰደው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋዱቱ ምደር ሲገቡ ከተሰጣቸው ዝርዝር ሕጎች መካከል ነው። ሕጉ የተሰጠው ለተወሰኑ ሰዎች፣ በተወሰነ ወቅት እና ለተወሰነ ዓላማ መሆኑን መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ዛሬ በእኛ ላይ ተግባራዊ እናደርገው ዘንድ የትምህርቱን መርሖዎችና ትርጉም በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልገናል። ለዚህ ዝርዝር ሕግ መሪ መርሕ በዘሌዋውያን 19:18 ላይ ያለው ሲሆን፣ የሚለውም:- « . . . ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» ነው። የዘሌዋውያንን መጽሐፍ በአጠቃላይ ለመረዳት መሪ የሆነው መርሕ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅድስና ነው። ስለ ሆነም፣ በዘሌዋውያን መጽሐፍ 19:28 ላይ ያለው አሳብ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ላይ ያለውን አተገባበር ለመረዳት ይህ ክልከላ እንዴት ፍቅርንና ቅድስናን እንደሚያሳይ መመርመር አለብን። ይህ እግዚአብሔር የፍጥረትን ሥርዓት ከሚያስከብርበት ብዙ ሕግጋት መካከል አንዱ ነው። ሕዝቡ ልጆችን እንዳይሠዋ፣ ከእንስሳት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንዳይፈጽም፣ ወይም ወንድ ከወንድ ጋር እንዳይተኛ ተነግሯቸዋል። አካልን መጉዳት፣ እግዚአብሔር እኛን ከፈጠረበት መንገድ በተቃራኒው መሄድ ነው። ይህ ጥቅስ፣ ሕዝቡ በአካባቢያቸው ከሚኖሩ እና ለጎዘን ሥርዓት አካላቸውን ከሚያበላሹ አሕዛብ የተለዩ ይሆኑ ዘንድ የተሰጠ ቁልፍ ማስጠንቀቂያ ነው። በተጨማሪም፣ የሞቱ ሰዎችን ማክበር ወይም መዘከር ወይም ደግሞ ያሉበትን ሁኔታ ለመቀየር የሚደረግ ማንኛ

ውም ድርጊት ስሕተት ነው።

ማቴዎስ እግዚአብሔርን ከምንወደው በላይ ቤተሰቦቻችንን መወደድ እንደሌለብን ነግሮናል። ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ የምንወዳቸውን ሰዎች የማያስደሰት ምርጫ ማድረግ የግድ ነው ማለት ነው። ሰዎች እና መላእክት ፍጡራን መሆናቸውን አስታውሱ። ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍጥረት የመንከባከብ፣ መላእክት ደግሞ እግዚአብሔርን የማገልገል ሥራ ተሰጥቷቸዋል። ሰይጣንና ርኩሳን መላእክቱ ደግሞ እግዚአብሔር የፈጠረውን መልካም ነገር ሁሉ ለማጥፋት ይሞክራሉ። ከፍጡራን መካከል ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይለኛ የለም። ፈጣሪያችን ወይም ፍጡራኑን በማገልገል መካከል መምረጥ አለብን። ይህ ማለት እናትና አባትን ከማገልገል ይልቅ፣ የእርሱን መንገድ ማገልገልን መምረጥ አለብን ማለት ነው። እግዚአብሔር የሠራውን አንድ ነገር በማጥፋት የምናምን ከሆነ፣ ሰይጣንን እየተከተልን ነው። እግዚአብሔር ከሰይጣን የበለጠ ኃይለኛ ነው። ደግሞም ከሞቱትም ይሁን በሕይወት ካሉት አባቶቻችን የበለጠ ኃይለኛ ነው። አእምሮአችንን እና እምነቶቻችንን እግዚአብሔር በሚለው መሠረት ይቀየሩ ዘንድ ልንፈቅድላቸው ያስፈልጋል። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ስንታዘዘው፣ እግዚአብሔር አስተሳሰባችንን ይቀይረዋል፤ አስተሳሰባችን ደግሞ ድርጊታችንን ይቀይረዋል።

አንዳንድ ጊዜ ለወላጆቻችን ቃል ኪዳን እንገባለን። ስለዚህም ወላጆቻችን ሲሞቱ መታሰቢያቸውን ለማክበር ቃል ኪዳናችንን መጠበቅ እንዳለብን ይሰማናል። ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔርን የማያስከብር መሆኑን ስናውቅ ምን ማድረግ አለብን? በሉቃስ የተጻፈው ታሪክ፣ በሕይወት ወዳሉት ቤተሰቦቹ ዘንድ ተመልሶ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ የሚያስከትለውን ጠንቅ ይነግራቸው ዘንድ በጣም ስለ ፈለገ አንድ ሰው ይነግረናል። ከሞቱት አያት ቅድመ - አያቶቻችን መካከል ብዙዎቹ ሊመለሱና የእግዚአብሔርን

ቃል እንድንታዘዝ ሊነግሩን ይፈልጋሉ፤ ግን አይችሉም። በእርግጠኝነት፣ የሞቱ ዘመዶቻችንን መታሰቢያ ለማክበር የሚመረጠው መንገድ፣ ሊነግሩን የሚናፍቁትን ነገር ማድረግ ነው።

በሮሜ ምዕራፍ 12 ውስጥ ያለው ምንባብ ሰውነታችንን በተመለከተ እግዚአብሔር ያለውን ፈቃድ እና እግዚአብሔርን ልናመልክበት ስለሚገባበት መንገድ ከሚናገሩ ብዙ ክፍሎች መካከል አንዱ ነው። እኛ በአካባቢያችን ካሉት የተለየን ልንሆን ይገባናል። ምክንያቱም የምናደርገው ነገር ሁሉ፣ ሰውነታችንን የምንጠብቅበትን መንገድ ጨምሮ፣ እግዚአብሔርን ማምለኪያ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሕዝቡን ተገቢ ስላልሆነ አምልኮ ጠንከር አድርጎ የወቀሰባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ውስጥ አናኒያ እና ሰጲራ የተገደሉት ለጌታ ታማኝነት የጎደለው ስጦታን በማቅረባቸው ነው።

ክብረ ንጽሕናዋን ይጠብቃል፣ እርሷንም ለባሏ ያቆያል።

ዘፍጥረት 2:24፡ «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።»

ዘጸአት 20:15፡ «አትስረቅ።»

ዘሌዋውያን 19:16፡ «በሕዝብህ መካከል በሸንጋይነት አትዙር፤ በባልንጀራህም ደም ላይ አትቁም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።»

ሰዎች አንድ መሆን የሚገባቸው ከሚያገቡት ሰው ጋር ነው። ይህም ሴቶችና ወንዶች በልባቸው ሊያደርጉት የሚገባ ውሳኔ ነው። በግብረ ሥጋ አንድ መሆን ለሴቶችና ለወንዶች በትዳር ውስጥ ብቻ መልካም ይሆን ዘንድ የታሰበ ነው። ድንግል ሆነው ይቆዩ ዘንድ የወንዶችን ብልት አንቆርጥም? እንዲህ ቢደረግ ግን ከጋብቻ ውጭ የሚደረግን ግንኙነት ለመከላከል በጣም ውጤታማ መንገድ ይሆን ነበር። ሴቷ ባልፈጸመችው ነገር ለምን በሕይወቷ ዘመን ሁሉ

ጠንቅ የሚሆን ጭካኔ የሞላበት ቅጣት እንቀጣታለን? ሰውነትን ማስተካከል አስተሳሰባችንን አይቀይርም። እግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች አንዳቸው ስለ ሌላቸው ንጹሕ የሆነ አሳብ እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ባሏና እርሷ ደስ ይሰኙበት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣትን አንድ ነገር መወሰዱ ልዩ የሆነን ስጦታ ከሴቷ እና ከትዳሯ እንደ መስረቅ ነው። ይህ ስጦታ ከተወሰደ ሴቷም ሆነች ወንዱ ይሠቃያሉ።

ድርጊቱ ደስታ የተሞላበትን ግንኙነት ከሴቷ ይሰርቃል። መቆረጡ በሚፈጸምባት ወቅት ወይም ልጅ በምትወልድበት ጊዜ ለመሞቷ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ ድርጊቱ ምናልባትም በምጥ ጊዜ ለልጁ ሞት ምክንያት ሊሆን ወይም በሕይወቱ (በጤንነቱ) ላይ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል (ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ)።

መቆረጡ ልጂቱ «ረጋ» ያለች እንድትሆን ከማድረጉም በተጨማሪ፤ የወሲብ ፍላጎቷንም ይቀንሳል።

መኃልየ 4:9፡ «እኅቴ ሙሽራ ሆይ፣ ልቤን በደስታ አሳበድሽው፤ አንድ ጊዜ በዓይኖችሽ፣ ከአንገትሽስ ድሪ በአንዱ ልቤን በደስታ አሳበድሽው።» ሙሽሪትም በቁጥር 16 ላይ ስትመልስ፦ « . . . ውዴ ወደ ገነቱ ይግባ፣ መልካሙንም ፍሬ ይብላ።» ትላለች።

አንዳንድ ሰዎች የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ የሚናገረው እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ኅብረት ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በሴትና በወንድ መካከል ስላለ ግንኙነት ይናገራል ይላሉ። ነገር ግን፣ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግልጽ እንደ ሆነው፣ በትዳር ውስጥ ያለው ግንኙነት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሊኖረው የሚፈልገውን ግንኙነት ምሳሌ (ሥዕል) ነው። መኃልየ መኃልይ በጋብቻ ውስጥ በሴትና በወንድ መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅርበት በእርሱና በፍቅረኛው መካከል ባለው ፍቅር መስሎ ያቀርበዋል። ትዳር የመንግሥተ ሰማይ ጣዕም በትንሹ ሊኖረው ይገባል። ነገር

ግን፣ የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ ጋብቻን ትንሽ የገዛነም ጣዕም እንዲኖረው ያደርገዋል፣ በተለይም ደግሞ ለሴቷ። አእምሯችን እንዲሁም በሰውነታችን ውስጥ የሚገኙ ንጥረ ነገሮች የወሲብ ፍላጎትን ይፈጥራሉ። ስለሆነም፣ ፈጽሞ ሽባ የሆኑ ሰዎች እንኳ ይህ ፍላጐት አላቸው። የሴትን ብልት ማስወገድ፣ ሴቷ በግብረ ሥጋ ፍላጎት ለመርካት የበለጠ አስቸጋሪ ይሆንባታል።

ሴት መልካም ባሕርይ እንዲኖራትና ባሏን እንድትሰማ እሺ ባይ እንድትሆን መደረግ አለባት።

ምሳሌ 12:19፦ «ከጠበኛና ከቍጡ ሴት ጋር ከመቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል።»

ገላትያ 3:28-29፦ «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።»

የሰውነት ጉዳት ሰውየውን ፈሪ እና ጎዘንተኛ ያደርገዋል። እነዚህ ደግሞ ከራሱ እንዲሁም ከሌሎች ጋር በሰላም የሆነ ሰው ባሕርያት አይደሉም። ብዙውን ጊዜ እንደዚህ የተጎዳች ሴት ሌላ ሰው በድጋሚ ጥቃት እንዳያደርስባት ለመከላከል ስትል ከሰዎች ጋር ልትጣላ ትፈልጋለች። ይህ መቆረጥ በሁለቱም ተጋቢዎች ዘንድ በትዳር ውስጥ ጥልንና የደስታ ማጣትን እንደሚያስከትል የሚያረጋግጥ ነው።

ጳውሎስ በመልእክቱ ውስጥ፣ ማንም ክርስቲያን ሌላውን ሰው ወይም ቡድን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል የማስገደድ መብት እንደሌለው ግልጽ አድርጓል። ሁላችንም በክርስቶስ ሞት ተገዝተናል፣ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፣ እናም ሁላችንም የአንድ ቤተ ክርስቲያን እና የአንድ አካል ብልቶች ነን።

ሴት ካልተገረዘች ጥሩ ጥሎሽ ስለማታገኝ አባቷ በድህነት ይማቅቃል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡9፣ «ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ፣ እንዲሁም ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱነትና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ። ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፣ አንዳንዶች ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤ ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል።»

ዘጸአት 20፡3፣17 «ከእኔ በቀር ሌላ አማልክት አይኑሩህ . . . የባልንጀራህ . . . የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ።»

አማኞች ከሌሎች ጤንነት እና ደኅንነት አስበልጠው ገንዘብን መውደድ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለእኛ የሚነግርበት መንገድ ነው። ነገሮችን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከመታዘዝ የበለጠ ከፈለግናቸው፣ ጣዖት ስላደረግን ኃጢአተኞች ነን። በአዲስ ኪዳን ደግሞ፣ ጣዖትን ማምለክ ዝሙትን የመፈጸም ያህል መጥፎ ተግባር ነው።

ማጠቃለያ

የምናደርገው፣ የምናስበው ወይም የምንናገረው ነገር ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ከሚጠብቅብን ነገር አኳያ መቃኘት አለበት። የማኅበረሰብ አካል መሆን መልካም ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን እንዲህ እንድንሆን ነው። ነገር ግን፣ እግዚአብሔርንም ሆነ ባህላችንን ሳናስከፋ የባህላችን አካል ሆነን ልንቀር እንዴት እንደምንችል መጣር ያስፈልገናል። ይህም አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ለመከተል እና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ድፍረት ከማግኘታቸው በፊት አንድ ሰው ቀደም ብሎ ባህላዊ ድርጊቶችን መቃወም ማለት ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔር መንገድ ሁልጊዜ ምርጥ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ባህላችንን ለመኖርና ልጆችን ለማሳደግ የተመቸ እና የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ባስቀመጠን ባህል ውስጥ ሆነን፣ ብርሃንና ጨው እንሆን ዘንድ ተጠርተናል።

ምዕራፍ አምስት::
የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ የሕክምና ምላሽ

ዕድሜዋ 15 ዓመት የሚሆን አንዲት የኦሮሞ ልጃገረድ ሥቃይ ይዟት ወደ ክሊኒክ መጣች:: የሥቃየዋ ምክንያት፣ ከ24 ሰዓት በላይ ሽንት መሽናት ያለመቻሏ ነው:: የሕክምና ባለሙያዋ የሽንት ፊኛዋ የቋጠረውን እንዲያፈሰ አድርጋላት ልጅቱ ወደ ቤት እንድትሄድ ተደረገ:: ወዲያውኑ ግን ፊኛዋ እንደገና ሞልቶ ተመልሳ መጣች:: በዚህ ጊዜ ነርሷ የልጅቱ የወገብ አጥንት (ኩሌ ገንዳ) ያለበት አካባቢ ማበጡን አስተዋለች:: በሽተኛ ዋ ብልት በመቆረጥ ሂደት ውስጥ እንዳለፈች ጠረጠረች እና፣ የወር አበባ ማየት ጀምራ እንደ ሆነ ጠየቀች:: ያገኘችው ምላሽ «አልጀመርኩም» የሚል ነበር:: ምርመራውም ያሳየው ከተፈጸመባት የቆረጣ ዓይነት የተነሣ የብልቷ ቀዳዳ ሙሉ ለሙሉ መዘጋቱን ነው:: ከዚያም የብልቱ አፍ አንዴ ሲከፈት፣ መጥፎ ጠረን ያለው የደረቀ ደም መፍሰስ ጀመረ:: ሊወጣ ባልቻለው የወር አበባ ደም ምክንያት የተፈጠረው እብጠት፣ የሽንት መውረጃውን በመጫን ሽንት እንዳይወርድ ከልክሎት ነበር::

አሁን የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ከጤና ጋር ወዳለው ግንኙነት መጥተናል:: በመግቢያችን ላይ በአውሮፓ መቆረጡ የሚፈጸምበት ምክንያት ከጤና አንጻር ለሴቶች ይጠቅማል ተብሎ እንደ ሆነ አይተናል:: በአፍሪካም፣ በአንዳንድ የጤና ባለሙያዎች መካከል እንኳን ሳይቀር፣ መቆረጡ ከጤና አንጻር አስፈላጊ እንደ ሆነ ይታመናል:: ከመቆረጥ ጋር በተያያዘ ወዲያውኑ የሚፈጠሩ ችግሮች በመድማት መሞት፣ ድንጋጤ፣ የመንጋጋ ቆልፍ በሽታ (Tetanus) እንዲሁም የሽንት እና የመውለጃ አካላት መመረዝን (infection) ያጠቃልላል:: በተጨማሪም፣ የተሰፉ ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽሙ ሲሉ የተሰፋው በሚከፈትበት ጊዜ ኤች. ኣይ. ቪ ከአንዷ ሴት ወደ ሌላዋ ሊተላለፍ ይችላል:: ከእነዚህ ሁሉ አደጋዎች ባሻገር፣ አሁንም ቂንጥርን ወይም ሌላ የሴት የብልት ክፍልን ማስወገድ፣ የሴቷን፣ ያልተወለደውን ልጅና የባለቤቷን ጤና የተሻለ ከማድረግ አንጻር

ያለው ጠቀሜታ ተረጋግጧል ወይ ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

የሴቶች መራቢያ ብልቶች ተግባር

ከሴት ውጫዊ የብልት ክፍሎች መካከል ማንኛውንም ቢሆን ማስወገድ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመረዳት እንድንችል፣ የተለያዩ የአካል ክፍሎችን ተግባራት ማጤን አለብን።

የብልት አፍ (Vagina)

የብልት አፍ ሦስት ተግባራት አሉት። ወንዱ የዘር ፍሬውን ወደ ሴቷ አካል የሚያሳልፍበት መንገድ ነው። የወር አበባ ደም ከሰውነት አልፎ የሚወጣው በዚሁ ክፍተት አማካይነት ነው። በተጨማሪም፣ ልጅ ለመወለድ የሚያልፈውም በዚሁ መንገድ ነው።

የብልት አፍ በመሰፋት ከተዘጋ፣ ሴቷ የወር አበባ ማየት በምትጀምርበት ጊዜ ችግር ያጋጥማታል። ደሙ በሰውነቷ ውስጥ መቆየቱ በጣም መጥፎ ነገር ነው። ደሙም ሁሉ ወደ ውጭ የማይፈስ ከሆነ ውስጥ ሆኖ ይጠነክራል፤ ጥንካሬውም የድንጋይ ያህል ሊሆን ይችላል። ከመጀመሪያው ደም በኋላ በየወሩ ሌላ ደምም እየተጨመረ ይጠነክራል። ይህ ደግም በጣም ያሠቃያል። ይህ በውስጥ አካላት ላይ መመረዝ ያስከትላል። የብልቱ አፍ በሚከፈትበት ጊዜ፣ የሽንት መውጫን የሚቆጣጠረውን ጡንቻ ሊጐዳው ይችላል።

አንዲት ሴት የሽንት ቱቦዎችን ወይም ፊንጢጣን መዝጋት እንደምትችለው፣ በፈቃደኝነት የብልቷን አፍ ልትዘጋ አትችልም። ይህ ማለት በብልት ውስጥ ያለ ማንኛውም ፈሳሽ ወደ ውጭ ይወጣል። የብልት አፍ የሚገኘው በሽንት ቧንቧ እና በፊንጢጣ መካከል ነው። በአጠቃላይ ንጹሕ መተላለፊያ ነው። ቢሆንም ግን፣ የብልት የውስጥ ግድግዳዎች ከተጐዱ ግን፣ ከሰውነት የሚወጣው ሽንት እና ሰገራ በብልት አልፎ ሊወጣ ይችላል። የብልት ከንፈር ደግሞ ለዚህ ሥራ ስላልተፈጠረ ከሰውነት በሚወገደው ቆሻሻ በቀላሉ ሊመረዝ ይችላል። ከሰውነት የተወገደ ቆሻሻ በብልት ውስጥ

ካለ፣ የወንድ ብልት በብልት አፍ ሲገባ ከዚህ ቆሻሻ ጋር ሊገናኝ ይችላል። ይህ ለወንድ ደስ የማይል ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የመመረዙን ዕድል እንዲጨምር ያደርጋል።

መቆረጡ በዙሪያው ያለውን ቆዳ በማጠንከሩ ምክንያት የብልት አፍ ጠባብ ከሆነና የሚለጠጥ ቆዳ ከሌለው፣ በግንኙነት ጊዜ ወንዱ ብልቱን ለማስገባት ይቸገራል፣ ለሴቲቱም ቢሆን ለረጅም ጊዜ ያሠቃያታል። ይህ እግዚአብሔር በትዳር ውስጥ ያለው ዕቅድ አይደለም። በተጨማሪም፣ ሴቷ የበለጠ በቀላሉ በኤች. አይ. ቪ ልትያዝ ትችላለች፣ ምክንያቱም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የቆዳ መሰንጠቅ እንዲፈጠር ስለሚያደርግ ቫይረሱን ወደ ሰውነት ለመግባት ያስችለዋል።

ቂንጥር (Clitoris)

ይህ አካል ከማንኛውም የሰውነት ክፍል የበለጠ ብዙ የነርቭ ጫፎች ያሉት ነው። በተጨማሪም፣ ብዙ የደም አቅርቦት አለው። በሚነካበት እና የወሲብ መነቃቃት በሚኖርበት ጊዜ ቂንጥር በመጠኑ ያብጣል። ይህ ሴቷ ለባሏ የደስታ ምላሽ መስጠት እንድትችል የሚያስችላት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በትዳር አካላዊ ገጽታ ፍጹም የሆነ የግብረ ሥጋ እርካታ፣ ሰላምና ደስታ እንድታገኝ ያደርጋታል።

ያልተወለደ የአሥር ሳምንት ፅንስ እንኳ ተመሳሳይ የሆነ የአካል ክፍል ይኖረዋል፣ ሴት ከሆነች ወደ ቂንጥርነት፣ ወንድ ከሆነ ደግሞ ወደ ወንድ ብልትነት ያድጋል። ቂንጥር እና የወንድ ብልት ተመጣጣኝ የአካል ክፍሎች ሲሆኑ፣ የሚለያዩት የሴት ቂንጥር ተግባር ደስታን መስጠት ብቻ በመሆኑ ነው። የወንዱ ብልት ግን ደስታን ይሰጣል፣ የዘር ፍሬውን ወደ ሴቲቱ ያስተላልፋል፣ በተጨማሪም የሽንት ቧንቧ አለው። ቂንጥርን ማስወገድ የወሲብ ፍላጐትን ለመርካት አዳጋች ያደርገዋል እንጂ የወሲብ ፍላጐትን አያስወግድም። ቂንጥር እና ሌሎች ውጫዊ የብልት ክፍሎች ለፍላጐቷ ምላሽ ለመስጠት እና ፍላጐቷን ለመግለጽ ያስችሏታል። የወሲብ ፍላጎት ግለሰቡ ከሚያስበው፣ ከሚናገረው፣ ከሚሰማው፣

ከሚያየው እንዲሁም በመንካት እና በመነካት ከሚሰማው ነገር የተነሣ በአእምሮው ውስጥ የሚፈጠር ይመስላል። ከዚያም አእምሮ የወሲብ ብልቶች መለወጥ እንዲጀምሩ እና ለአካላዊ ንክኪው ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርገውን ፒቱ እጢ (pituitary gland) እድገንጥር (hormone) እንዲያመነጭ ይነግረዋል። ትክክለኛ በሆነ መንገድ የውጭ አካላቷ መነቃቃት፣ አእምሮዋ ዳግመኛ አካሏን እስኪያነቃቃው ድረስ የሴቷን ፍላጐት በማርካት ይጠናቀቃል። እድገንጥሮች ያለማቋረጥ እየመነጩና ሥራውን የሚያከናውኑት ብልቶች ከመቆረጣቸው የተነሣ ሰውነት ምንም ሊጠቀምበት የሚችልበት መንገድ ከሌለ፣ በዚያን ጊዜ ሴቲቱ በጣም ተስፋ ትቆርጣለች። በግብረ ሥጋ ስለማትረካ፣ ምናልባትም ሙሉ በሙሉ ስሜታዊ ስላልሆነ ከአካላዊ ግንኙነት መራቅ ትፈልጋለች። ለመርካት ስትል ምናልባትም ሌላ ግንኙነት ለመሞከር ትፈልግም ይሆናል።

ባሏም ቸልተኛ ሚስቱን ሊያረካ ወይም በእርሷ ሊረካ እንደማይችል ይሰማውም ይሆናል። ይህም የግብረ ሥጋ እርካታን ለማግኘት ከጋብቻ ውጭ ለመሄድ ወደ መፈተን ይመራዋል። በኬንያ ወንዶች ለመርካት ወዳልተገረዘች ሴት፣ ብዙውን ጊዜ ወደ ሴተኛ አዳሪ እንደሚሄዱ በጽሑፍ የሰፈረ መረጃ አለ። ምክንያቱም የተቆረጠችን ሴት ማርካትም ሆነ በእርሷ መርካት ስለማይችሉ ነው (Odeke)። ይህ ብዙ የጤና ችግሮችን ያስከትላል። ከእነዚህም መካከል አንዱ የኤች. አይ. ቪ ስርጭት ነው።

የእነዚህ የአካል ክፍሎች መወገድ፣ የደም ወሳጅ ቧንቧዎችን መቆረጥ ሊያስከትል ይችላል። ይህ ደግሞ አደገኛ የሆነን መድማት ሊያስከትል እና ወደ ሞት ሊያመራም ይችላል። የቂንጥር መወገድ የወንድን ብልት እንደ መቁረጥ እና እግዚአብሔር ለሴቶች የሰጠውን በጣም የተለየ እና መልካም ነገር የመውሰድ ያህል ነው። ማንም ሰው ይህንን ከሴት የመውሰድ መብት የለውም። ይህን ማድረግ እግዚአብሔር በፍጥረት ጥሩ ሥራ አልሠራም እንደ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ውሸት ነው፣ ውሸት እና ማታለል

ከሰይጣን የመጣ ነው። ሰይጣንን ስንሰማ እግዚአብሔር አይደሰትም።

ዐቢይ ከንፈር (Labia majora) እና ንዑስ ከንፈር (Labia minora)

እነዚህ የተጣጠፉ ቆዳዎች ሦስት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። የመጀመሪያው፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ደስታን መስጠት ነው። ምንም እንኳ ይህ አካል እንደ ቂንጥር የደስታ ስሜት እንዲሰማ የሚያደርግ ቢሆንም፣ ደስታ የመስጠት መጠኑ ግን ከቂንጥር ጋር እኩል አይደለም። ሁለተኛው አገልግሎቱ የብልትን አፍ ከጉዳት መጠበቅ ነው። ሦስተኛው አገልግሎቱ ደግሞ ልጁ በሚወለድበት ጊዜ መለጠጥ ነው። ይህ ከሆነ እናቲቱ ሳትቀደድ እና ሳትደማ ልጁ ሊወጣ ይችላል።

ይህ የተጣጠፈ ቆዳ በነርቭ ጫፎች የበለጸገ ስለ ሆነ ስፍራው የንክኪ፣ የሕመምና የሙቀት ስሜት በቀላሉ እንዲሰማው ያደርገዋል። ስፍራው በደም ሥር የበለጸገ ስለ ሆነም በሚነካካበት ጊዜ ያብጣል። ይህ ደግሞ ሴቷ ከባሏ ጋር በምታደርገው ወሲባዊ ግንኙነት የምታገኘውን ደስታ ይጨምራል። ዐቢይ ከንፈር ላብ እና ቅባት የሚያመነጩ እጢዎች ስላሉት፣ ስፍራውን ከመድረቅ እና ከሕመም ይጠብቁታል። ደረቅ (እርጥበት የሌለው) እና ሴቶችን የሚጎዳ ወሲብ የሴቷን የማርገዝ ዕድል ይቀንሳል።

ከንፈሩ ከተቆረጠ የሚፈጠረው አደገኛ መድማት፣ ድንጋጤን እና ሞትን ሊያስከትል ይችላል። ሴቲቱ ከመቆረጡ ስታገግም ጠንካራ ቆዳ ይፈጠራል። ይህም ምናልባት ያለማቋረጥ የሕመም ስሜት እንዲሰማት ያደርጋል። በቀላሉ ለመራመድና ለመዘዋወር አትችልም ይሆናል። ይህም ውኃ መሸከም እና ልጆች መጠበቅ የመሳሰሉት የጉልበት ሥራዎች አስቸጋሪ እንዲሆኑባት ያደርገዋል።

የጠነከረ ቆዳ እና የተሰፋ ከንፈር የሽንት መውጫ ቀዳዳን ሊዘጋ ይችላል። ይህ ከሆነ፣ ልጅቱ ሽንት ቤት በምትጠቀምበት ጊዜ ሁሉ ሥቃይ ይኖራታል። ስለዚህም ብዙ ጊዜ ላለመሽናት ስትል ሽንቷን

ልትቋጥር ወይም ውኃ ከመጠጣት ልትገታ ትችላለች። የውኃ እጥረት ደግሞ ኩላሊቷን ይጎዳዋል። ይህ የጤና መጓደል፣ በእርግዝና ጊዜ ችግርንና ያለ ጊዜ መሞትን ሊያስከትልባት ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የብልት መቆረጡ ከተፈጸመ በኋላ ባሉት ጥቂት ቀናት፣ ልጅቱ እንድትጠጣ የሚሰጣት ጥቂት ፈሳሽ ነው። ይህ ሞትን ሊያስከትል ይችላል። ድርቀቱ ደግሞ በእርጅና ጊዜ የመታወር ዕድሏ እንዲጨምር ያደርጋል።

የጠነከረው ቆዳ እና የተሰፋው ከንፈር ልጁ በሚወለድበት ጊዜ ከማኅፀን ለመውጣት አስቸጋሪ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፈጽሞ የማይቻል እንዲሆን ያደርገዋል። ልጁ ለመውጣት ረጅም ጊዜ ከወሰደበት፣ ሊሞት ይችላል። በተጨማሪም፣ የአእምሮ ጉዳት በሚያስከትል የንጹሕ አየር እጥረት ሊሠቃይ ይችላል። ይህ ማለት ልጁ የአካል ችግሮች ይኖሩበታል። እነዚህም ችግሮች የመናገር፣ የመራመድ፣ ትምህርት በአግባቡ ያለመቀበል ሊሆኑ ይችላሉ። በብልት አፍ ዙሪያ ያለው ጠንካራ ቆዳ ከተለመደው በላይ ስለሚቀደድ ምናልባትም መቆረጥ ያስፈልገው ይሆናል። ይህ ደግሞ ብዙ መድማትን ስለሚፈጥር፣ በወሊድ ጊዜ ልጁና እናቲቱ የበለጠ የመመረዝ ዕድል ይኖራቸዋል። እናቲቱ የኤች. አይ. ቪ ወይም የጉበት ብግነት (Hepatitis) ቫይረስ ተሸካሚ ከሆነች፣ ልጁ በቫይረሱ የመያዝ የበለጠ ዕድል አለው። እናቲቱም በቀላሉ በጋንግሪን ወይም በሰውነት ውስጥ የቁስል መበስበስ (gangrene) እና የመንጋጋ ቆልፍ በሽታዎች ትጠቃለች። እነዚህ ሁለቱም በሽታዎች ሞትን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

እስካሁን ድረስ የተቆረጡ ሴቶች በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች ለመያዝ የበለጠ የተጋለጡ መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ባይኖርም፣ እነዚህ ውጫዊ ብልቶች ከመቆረጣቸው የተነሣ ከንፈሩ ደረቅ፣ ጠባሳ እና የተጣበቀ ከሆነ፣ ባልየው ብልቱን ወደ ውስጥ ለማግባት የሚቸገር ይመስላል። ወሲብ በሚፈጽምበትም ጊዜ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ጉልበት መጠቀም ያስፈልገውም ይሆናል። በዚህ ጊዜ የእርሷ ጡንቻዎች

ይደግሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ፣ ቁስሉ የኤች. አይ. ቪ እና ሌሎች ቫይረሶችን በቀላሉ ይቀበላል።

ከውጫዊ ብልት ክፍሎች መካከል ማንኛውም በሚቆረጥበት ጊዜ፣ በልጅቱ ትግል ምክንያት መቁረጫው ከእጅ ሊያመልጥ ይችላል። በብልት አፍ እና በፊንጢጣ መካከል ያለው ግድግዳ ከተጐዳ፣ የሰውነት ቆሻሻ ያለማቋረጥ በብልት አፍ አልፎ ይፈሳል። ይህ መጥፎ ጠረን እና መመረዝን ያስከትላል። ፊኛውን የሚቆጣጠሩት ነርቮች እና ጡንቻዎች ከተጐዱ፣ ጉዳታቸው ዘላቂ ወይም እስከ መጨረሻ ይሆናል።

ማኅፀን

ማኅፀን ጽንስ አድጎ ለመወለድ ዝግጁ እስኪሆን ድረስ የሚይዝ (የሚሸከም) ከጡንቻ የተሠራ ከረጢት ነው። በእያንዳንዱ ወር የሴት እንቁላል ፅንስ ለመያዝ ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ፣ ማኅፀን ብዙ ደም የያዘ የጡንቻ ግድግዳ ይፈጥራል። እንቁላሉ ዘር ካገኘ፣ ይህ ጡንቻ ፅንሱ ማደግ እና መመገብ ይጀምር ዘንድ ለእንቁላል የተመቸ የመቀመጫ ስፍራ ይሆናል። እንቁላሉ ዘር ካላገኘ፣ ከተፈጠረው የጡንቻ ግድግዳ ጋር ሆኖ ከሰውነት ይወጣል። ለዚህ ፈሳሽ የሚሆን የሕክምና ቃል «ሜኑስትሩዌይሽን» (menstruation) ነው። በአማርኛ፣ የወር አበባ ጊዜ ተብሎ እንደሚጠራ ሁሉ፣ በሌሎች ባህሎችም ለዚህ የሚሆን የተለየ ቃል አለ።

ውጫዊ ብልት በሚቆረጥበት ጊዜ መመረዝ ሊፈጠር ይችላል። ይህ መመረዝ ደግሞ ወደ ውስጥ ዘልቆ ማኅፀንም እንዲመረዝ ሊያደርገው ይችላል። ከንፈር እና እጢዎች በመጎዳታቸው ምክንያት በኋላም መመረዝ ሊኖር ይችላል። የወር አበባ እንደ ልብ መፍሰስ ካልቻለ፣ ተጠራቅሞ በመቆየቱ የጠነከረው ደም፣ መመረዝንና ትኩሳትን ይፈጥራል። ይህም ማኅፀንን ለዘለቄታው ሊጎዳው እና ሞትንም ሊያስከትል ይችላል። ደሙ እብጠት ሊፈጥር እና በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንዳየናት ሴት የሽንት ቧንቧ ሊዘጋ ይችላል። እንዲህ የሆነች ሴት እርጉዝ ልትመስል እና ማኅፀኗም ሙሉ በሙሉ ሊጎዳ ይችላል። ማኅፀን ከተጎዳ ደግሞ

አንድ ሴት በፍጹም ልጅ መውለድ አትችልም።

እንቁልእጢ (Ovaries)

የዘር ከረጢት የሴቷን እንቁላሎች ይይዛል። አንዲት ሴት የምትወልደው የተወሰነ ቁጥር ካለው እንቁላል ጋር ነው። ስለሆነም አንዱ እንቁላሎች ከተደመሰሱ (ከተጎዱ)፣ ሊተኩ አይችሉም። የማኅፀን መመረዝ ወደ ዘር ከረጢት ሊዛመትና እንቁላሎቹን በመጉዳት ሴቲቱን መካን ሊያደርጋት ይችላል። በዚህ ጉዳይ ወንዶች የተለዩ ናቸው። ሰውነታቸው ዘር መሥራት የሚጀምረው ለአቅመ - አዳም ሲደርሱ ነው። እስከ ሕይወታቸውም መጨረሻ ድረስም አዳዲስ ዘርን ማምረት ይቀጥላሉ።

የማኅፀን ቧንቧዎች (Fallopian Tubes)

እነዚህ በዘር ከረጢት እና በማኅፀን መካከል የሚገኙ ቧንቧዎች ናቸው። መመረዝ በእነዚህ ቧንቧዎች ላይ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል። ጉዳቱ ቧንቧዎቹን ከዘጋቸው፣ የወንዱ የዘር ፍሬ ወደ እንቁላሉ ሊደርስ አይችልም። እንዲህ ሲሆን ፅንስ ሊፈጠር ይችላል፣ ግን ዘር ያገኘው እንቁላል በቧንቧው ውስጥ ይቀረቀራል። ይህም ቢሆንም እንኳ ፅንሱ ማደጉን ይቀጥላል። ይህ ለእናቲቱ በጣም አደገኛ ነው። በአስቸኳይ የሕክምና እርዳታ ካላገኘች ችግሩ ሞትን ያስከትላል።

ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮች

ከሴት ውጫዊ ብልት መቁረጥ ጋር በተያያዘ በእርግዝና ወቅት፣ በወሊድ ጊዜ እና ከወሊድ በኋላ ስለሚከሰቱ ለየት ያሉ ችግሮች ማወቅ፣ የልምድ አዋላጆችን ጨምሮ፣ የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ሁሉ አስፈላጊ ነው። በተለይ ደግሞ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ የተሰፋች ሴት ዘመናዊ የጤና አገልግሎት በማትፈልግበት አገር ውስጥ። የሴቶች ውጫዊ ብልት ከሚቆረጥበት፣ በተለይም ቆርጦ የመስፋት ልምድ ካለበት፣ አካባቢ የመጡ ሰዎችና ስደተኞች ዘመናዊውን ሕክምና ይፈራሉ። ምክንያቱም ዘመናዊውን የጤና ሳይንስ የተማሩ የጤና ባለሙያዎች እንዴት ሊረዷቸው እንደሚችሉ ስለማያውቁ ነው።

በእርግዝና ወቅት

የከፋው ዓይነት አቆራረጥ ለእርጉዝ ሴት ችግርን ይፈጥራል። በመጀመሪያ፣ ብዙውን ጊዜ የብልት ምርመራ ማድረግ አይቻልም ወይም በጣም ያሠቃያል። በእርግዝና መጀመሪያ ላይ የተሰፋውን እንደ ገና መክፈት (Deinfibulation) አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በእርግዝና ምክንያት የሚፈጠረው የሆርሞን መቀየር፣ በውስጠኛው እና በውጭው የብልት ክፍል የደም አቅርቦት (ዝውውር) እንዲጨምር ያደርጋል። በተጨማሪም፣ እነዚህ የእድገንጥር ለውጦች በአካባቢው ያሉ አንዳንድ ጡንቻዎች እንዲለጠጡ ያደርጋሉ። እነዚህ ሁለት ለውጦች ደግሞ የሴቷ የሽንት ከረጢት እና ፊኛዋ በቀላሉ እንዲመረዝ ያደርጋሉ። ሽንት ከሰውነት የሚወጣበት መተላለፊያ በመቆረጥ ምክንያት ከተጎሳ፣ የመመረዝ ዕድልን ይጨምራል (ሩሸዋን፣ ገጽ 99)።

ከእርግዝና በፊት የነበሩ እጢዎች (Cysts) በእርግዝና ጊዜ ያድጉና ምቾትን ይነፍጋሉ። የደም አቅርቦት (ዝውውር) በአካባቢው ከመጨመሩ የተነሣ፣ በእርግዝና ጊዜ መወገድ የለባቸውም። ያለመመቸቱን ለመቀነስ የሚደረግ የቅጠላ ቅጠል መድኃኒት መድማትን ሊያስከትልና የመመረዝ ዕድል እንዲጨምር ያደርጋል።

በወሊድ ጊዜ

በእርግዝና ወቅት ካልተደረገ፣ የተሰፋች ሴት በወሊድ ጊዜ ብልቷ መከፈት ያስፈልገዋል።

በሴት ውጫዊ ብልት መቆረጥ ላይ የተጻፉ ብዙ ጽሑፎች፣ መቆረጡ ቀዳዳን (Fistula) እንደሚፈጥር ይናገራሉ። የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) መረጃ በጉዳዩ ላይ እንዲህ ይላል፦

> በፊንጢጣና በብልት አፍ መካከል ያለ ቀዳዳ፣ በመቆረጥ ጊዜ፣ እንደገና ከመተርተር፣ ድጋሚ ከመሰፋት፣ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ከተዛባ ምጥ የተነሣ ይፈጠራል። የማያቋርጥ የሽንት እና የዐይነ ምድር መፍሰስ ሴቷን በሕይወት ዘመኗ ሁሉ ሊያስጨንቃት እና ከማኅበረሰቡ እንድትገለል ሊያደርጋት ይችላል።

ይህ አባባል ያለመግባባት ይፈጥራል። ፊስቱላ (Fistula) ማለት ቀዳዳ ማለት ነው። ታዲያ ይህ ቀዳዳ በአካል ላይ በማንኛውም ስፍራ ሊፈጠር ይችላል። ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚፈጠረው ቀዳዳ በብልት አፍ ወይም በወሊድ መተላለፊያ እና ፊኛ መካከል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ቀዳዳ በመቆረጥ የሚፈጠር ሳይሆን፣ የእናቲቱ የወገብ አጥንት (ዳሌ) በጣም ትንሽ በመሆኑ ምክንያት የልጇን ራስ ለማሳለፍ አንሶ ሲገኝ ነው። የልጁ ራስ በተደጋጋሚ የእናቲቱን የወገብ (የዳሌ) አጥንት ይገፋዋል። በዚህ ወቅት ታዲያ በልጁ ራስ እና በወገብ አጥንት (በዳሌ አጥንት) መካከል ያለውን ጡንቻ ይጎዳዋል። ከዚያም ሽንት በብልት አፍ አልፎ ይፈሳል። ይህ በተለይ ሴት ልጆች የሰውነታቸውን እድገት ሳይጨርሱ ተድረው በሚያረግዙበት ጊዜ የሚፈጠር የተለመደ ክስተት ነው።

አንዴ የልጁ ራስ በዳሌ ካለፈ፣ እንደዚህ ያለ ቀዳዳ ሊፈጥር አይችልም። ነገር ግን፣ ከመሰፋቱ ወይም ከመቆረጥ የተነሣ ሴቲቱ ጠንካራ ቆዳ ኖሯት ከሆነ፣ ይህ የመውለዱን ሂደት ቀርፋፋ ሊያደርገው ወይም ሊያቆመውም እንኳ ይችላል። የብልት አፍ የሚገኘው በፊኛ ቱቦ እና በፊንጢጣ መካከል እስከ ሆነ ድረስ፣ በወሊድ ሂደት የሚፈጠረው ግፊት እነዚህን አካላት በሚለያየው ጡንቻ ላይ ቀዳዳ ሊፈጥር ይችላል። ልጁ የውጭኛውን የቆዳ ግድግዳ (Perineum)፣ በብልትና በፊንጢጣ መካከል ያለውን ክፍል መግፋቱ በፊንጢጣ ጡንቻዎች ወይም በሽንት መተላለፊያ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ቀዳዳ ሊፈጥር ይችላል። እነዚህ ጡንቻዎች ከተጎዱ፣ ሴቲቱ ሽንት እና ዐይነ ምድር ፈጽሞ መቆጣጠር እንድትችል፣ ጠንካራ ተደርገው እንደገና መስተካከል ያስፈልጋቸዋል።

በብልት አፍ እና በሌሎች ሁለት መተላለፊያዎች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም ቀዳዳ ሴቲቱ ከሰውነቷ የሚወጣውን ሽንት እና ዐይነ ምድር መቆጣጠር እንዳትችል ያደርጋታል። በዚህ ምክንያት ከሚፈጠረው ሽታ የተነሣ ከማኅበረሰቡ ትገለላለች፤ በተጨማሪም፣ የመመረዝ ዕድል ይኖራታል። መቆረጥ እና ያለ

ዕድሜ ጋብቻ ለዚህ ዓይነቱ ችግር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ስለዚህም ይህንን ችግር የሚያመጡትን ሁለቱን ልማዶች ለማስቆም ቤተ ክርስቲያን እና ሰፊው ማኅበረሰብ ሊሠራ ይገባል።

ከወሊድ በኋላ

ከወሊድ በኋላ፣ በመከፈት እና በመቦጨቅ ምክንያት የተፈጠረው ቁስል መሰፋት ያስፈልገዋል። ክርስቲያኖች የተሰፋችን ሴት ለመክፈት ሲጠየቁ እንዴት ያለ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው አስቀድመው ሊያስቡበት ይገባል። ለሴቲቱ እና ለባሏ ምክር መስጠት መጀመር ያለበት በእርግዝውና መጀመሪያ ላይ ነው። ምክንያቱም፣ መድማት ከሌሎች ይልቅ በተሰፋች ሴት ላይ ይበረታል። ደም ማነስ የመከሰቱም ዕድል ከፍተኛ ነው። መድማት በኋላም ከመመረዝ የተነሣ ሊከሰት ይችላል።

ከአእምሮ ጤና ጋር የተያያዙ ችግሮች

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ዘገባ፣ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ፣ እንደ «ጸታ ጥቃት የሚቆጠር ነው።» ድርጊቱ ዘላቂ ወደ ሆነ የሥነ ልቦና ጉዳት ሊያመራና የሴቶችን የመራቢያ አካል ጤና ሊጎዳ እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም የሚታየው በሴቶች ላይ እንደ ተቃጣ የኃይል ጥቃት እና የሴቶችን መሠረታዊ መብት እንደ መጣስ ነው (ከኢንተርኔት የተገኘ መረጃ)። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚስከትለውን የስሜት ችግሮች በተመለከተ የተሠራው ጥናት በጣም ጥቂት ነው። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ሲገልጽ፡-

> *የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚስከትላቸው ሥነ ልቦናዊ ጉዳቶች ከአካል ጉዳቶች ይልቅ በሳይንሳዊ መንገድ ለመመርመር አስቸጋሪ ናቸው። ከድርጊቱ ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ጥቂት የሥነ ልቦና ሕመም ጉዳዮች ብቻ ተዘግበዋል። . . . ሳይንሳዊ መረጃ ከማነሱ ባሻገር፣ የተቆረጠ ሰዎች የግል መረጃዎች መቆረጥ የጭንቀት፣ የፍርሃት፣ የሃፍረት፣ የመካድ የመሳሰሉ ስሜቶችን እንዳሳደረባቸው*

ያሳያሉ፣ እነዚህ ሁሉ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ አሉታዊ ጉዳቶችን ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው። የድርጊቱ ድንጋጤና አስፈሪ ሁኔታ «ረጋ ያለ» (Calmer) እና «ታዛዥ» (Docile) ተብለው ለሚገለጹት ባሕርያት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ አንዳንድ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። እነዚህ ባሕርያትም የመቁረጥን ድርጊት በሚፈጽሙ ማኅበረሰቦች ዘንድ አዎንታዊ እንደ ሆኑ የሚቆጠሩ ናቸው (ከኢንተርኔት የተገኘ)።

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ በሴቶች ላይ የሚቃጣ የኃይል ድርጊት እንደ መሆኑ መጠን፣ ለዚህ ድርጊት የሚሰጠው ምላሽ ጾታዊ እና አካላዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰብ ይሆናል። በወሲብ ያለመርካት፣ የእምነት ማጣትና በራስ ያለመተማመን፣ ጭንቀት፣ ድብርት፣ ብስጭት እና የትዳር ቀውስ ከድርጊቱ መፈጸም የተነሣ በሴቶች ላይ የሚታዩ ችግሮች ናቸው ተብለው በዓለም የጤና ድርጅት ተዘርዝረዋል (ሐምሌ፣ 1966 ዓ.ም)።

እዚህ ላይ ግን በጾታ ጥቃት እና የሴትን ውጫዊ ብልት በመቁረጥ መካከል አንድ ትልቅ ልዩነት አለ። የጾታ ጥቃት ሁል ጊዜ ማለት ይቻላል፣ በጎበረተሰቡ ሲወገዝ፣ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ ግን የተዘበራረቀ ስሜት ይታያል። ድርጊቱ በሚፈጸምባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ይፈቀዳል፣ ደግሞም ይበረታታል። ለጥናት ዓላማ ስለ መገረዛቸው ቃለ መጠይቅ ባደረጉ ሰዎች ውስጥ የተቀላቀለ ስሜት ታይቷል። ብዙ ሴቶች ከመ-ሸጋገሪያ ሥርዓታቸው የተነሣ የሚሰጣቸውን ክብር ይናፍቃሉ።

> ድግስ፣ ስጦታዎች እና መቆረጡ በሚፈጸምበት ጊዜ ለሚቆረጡቱ የሚሰጠው የተለየ ትኩረት የመቆረጡን አሰቃቂነት ይቀንሰው ይሆናል። ነገር ግን በተረፉት ሴቶች ላይ የሚያመጣው ሥነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የማግኘቷ ስሜት ወጉንና ባህሏን ማክበሯ ብዙውን ጊዜ የእርሷ ብቸኛ ሚና ለሆነው ትዳር ብቁ ያደርጋታል። ያልተቆረጠች ሴት በማኅበረሰቡ ከመገለሏ የተነሣ በሥነ ልቦና

ልትሠቃይ ትችላለች። (ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል የመረጃ መረብ የተገኘ)።

በልጆች እና በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ቡድኖች ይህንን ጉዳይ ልብ ማለታቸው (ማጤናቸው) በጣም ጠቃሚ ነው። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ጨካኝ እና ልጆቻቸውን ሊጐዱ የሚፈልጉ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የሚፈጽሙት ነገር አይደለም። በዘመዳሞች መካከል እንደሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትና እንደ ሕፃን ልጅ ግርፋት ካሉ ጥቃቶች ጋር በተመሳሳይ ምድብ የሚቀመጥ አይደለም። ይልቁንም፣ ለሴት ልጃቸው እጅግ መልካም ነገር እንዲሆን በሚፈልጉ፣ በሠለጠነው (በምዕራቡ) ዓለም ለልጃቸው መልካም ነው ብለው የሚያምኑትን ነገር ለማድረግ ሲሉ ድርጊቱን በመፈጸም ሕግን በመጣስ ራሳቸውን አደጋ ላይ ለመጣል ዝግጁዎች በሆኑ ወላጆች የሚፈጸም ነው። በዚህ ምክንያት፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ልጆችን ከቤተሰብ ማራቅ አይረዳም። ሕግ እና የስደተኞች መርሐ ግብሮች የማኅበረሰብን እሴት መቀየርን ዓላማ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም፣ መቆረጥን ለመከላከል ቢያንስ ቢያንስ ልጆቹ ስለ ጉዳዩ አውቀው የራሳቸውን ውሳኔ እስከሚያደርጉበት ዕድሜ ድረስ መጠበቅ አለባቸው።

የሴቶችን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የትርፍ እና የኪሳራ እንድምታ የመኖሩ ጉዳይ ችግሩን ውስብስብ አድርጐታል። የአሳብ፣ የስሜት እና የባሕርይ ግጭት ሊያስከትልም ይችላል። ድርጊቱ አስቀድሞ የተፈጸመባቸው ብዙ ሴቶች እና እንደዚህ ዓይነት ጽሑፎችን የሚያነቡ፣ በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሰጣቸው አስደናቂ ስጦታ ከእነርሱ እንደ ተወሰደባቸው ይረዳሉ።

በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሰባት ውስጥ፣ «ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ» በሚለው ርእስ ሥር ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍትሔ ለመስጠት የሚቻለው ሁሉ ይሞከራል። ይሁን እንጂ፣ በዚህ ደረጃ በአጽንኦት መግለጽ የምንፈልገው፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሠራ የተጠናቀረ ጥናት አለመኖሩን ነው። ስለዚህም እኛ ያደረግነው አጠቃላይ መርሖዎችንና ሌሎች ከወሲብ ጋር

ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮችንና ተሞክሮዎችን አብሮ ማጤን፣ መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማየት እና በመረጃ የተደገፈ አሳብ መስጠት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ምርምር የሚያደርግ ሰው ብዙ ተግዳሮቶችን መጋፈጥ ያስፈልገዋል።

ለአንዳንድ የተለመዱ እምነቶች የሚሰጡ ምላሾች

የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥን ጉጂነት በተመለከተ የተዛባ አመለካከት ያለመኖሩን ለማረጋገጥ እንዲቻል አሳቡ ተነሥቶ መልስ ሊሰጥባቸው የሚገቡ በርካታ ባህላዊ እምነቶች አሉ። አንዳንድ ማኅበረሰቦች ቂንጥር የልጁን ጭንቅላት ከነካ ልጁ ይሞታል ብለው ያስባሉ። ቂንጥር መርዛማ አይደለም። ይልቁንም በጣም ጥሩ የአካል ክፍል እንጂ። ቂንጥር የሴቷን ደስታ ይጨምራል። ይህም የማርገዝ አቅሟን ያሳድጋል። በማንም ላይ ቢሆን በተለይ ደግሞ በልጁ ላይ ጉዳት ሊያደርስ አይችልም።

አንዳንድ ጊዜ ቂንጥርን ማስወገድ ልጃገረዶችን ሙሉ ሴት ያደርጋቸዋል ይባላል። ምክንያቱም የሚቆረጠው ክፍል (ቂንጥር) በሴት ላይ ያለ «የወንድ» አካል እንደ ሆነ ስለሚታሰብ ነው። አንዳንድ ሰዎች ቂንጥር ወደ ወንድ ብልትነት ያድጋል ብለው ያምናሉ። ይህ ግን ስሕተት ነው። ይልቁንም፣ ቂንጥርን ማስወገድ አንድን ሴት በተለየ ሁኔታ ሴት የሚያደርጋትን ነገር ማስወገድ ነው። ይህ የአካል ክፍል ወደ ወንድ ብልትነት ሊያድግ አይችልም። እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን የፈጠረው በብዙ መልኩ የተለያዩ አድርጎ ነው። በውስጣዊውም ሆነ በውጫዊው ነገራችን የተለያየን ነን። በውስጣችን በምናመነጫቸው ንጥረ ነገሮች እንኳ ሳይቀር እንለያያለን። ሴቶች ወደ ወንድነት ሊቀየሩ አይችሉም፤ ወንዶችም እንዲሁ ብልታቸውን በመቆረጥ ወደ ሴትነት መለወጥ አይችሉም።

ድርጊቱ ለንጽሕና እና ሽታን ለማስቆም ሲባል ይፈጸማል። እርግጥ ነው የተጣጠፈው ቆዳ ቆሻሻን ሊይዝ ይችላል። እጢዎች የሚያመነጩት ላብ እና ቅባት ሊቆይ ሊሸት ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ላቡ፣ ቅባቱም ሆነ የተጣጠፈው ቆዳ በእርግጠኝነት ለሴቷ ጤና የሚያገለግሉ ናቸው። ሁልጊዜ በውኃ እና በሳሙና በመታጠብ

እንዲሁም በንጹሕ ጨርቅ በመጥረግ ሽታውን በቀላሉ ማስወገድ ይቻላል። ለሳሙና መግዣ የሚሆን ገንዘብ ከሌለ ውኃ ብቻ መጠቀምም ይቻላል። ይህንን የአካል ክፍል ለማጽዳት የሚያስፈልገው በጣም ጥቂት ውኃ ነው። ሽንትን ገድቦ ስለሚያስቀምጥ ሙሉ ለሙሉ መስፋት መጥፎ ጠረን ሊያስከትል ይችላል። አካባቢው ሁልጊዜ እርጥብ ስለ ሆነ መመረዝ ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ደግሞ ሽታን ያስከትላል።

ለማጠቃለል፣ እያንዳንዱ የሴት ብልት ውጫዊውንም ሆነ ውስጣዊውን ክፍል ንድፉን ያወጣውም ሆነ በስፍራው ላይ ያስቀመጠው ጌታ ነው። የእርሱ ሥራ ደግሞ ፍጹምና እያንዳንዱ የአካል ክፍል ለሴቷ የአካል፣ የአእምሮ እና የመንፈስ ጤንነት የተለየ ሚናን ይጫወታል። እንዲሁም ልጅን በመውለድ ሂደት እና በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ ዓይነተኛ ሚና አለው። በጣም ግሩም እና መልካም የሆነን ነገር ለማጥፋት ምክንያት መስጠት እንዴት እንችል ይሆን?

ምዕራፍ ስድስት::

ለውጥ እና የለውጥ ተቃውሞ

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች (መሪዎች) ተሰበሰቡና የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ትክክል ያለመሆኑን ተማምነው፣ ክርስቲያኖች ልጆቻቸውን ማስቆረጥ የለባቸውም ብለው ወሰኑ:: ክርስቲያኖች ከዚህ ውይይት በኋላ፣ ሴት ልጅ የነበረው እያንዳንዱ መሪ ልጁ እንዳትገረዝ ሊያደርግ ወሰነ::

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩ ሴቶችም፣ በጉዳይ ላይ ትምህርት ተሰጣቸውና ድርጊቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለመሆኑንና መቆም እንዳለበት ተቀበሉ:: ሴቶቹ በቡድን ተከፋፍለው ለሠላሳ ደቂቃዎች ያህል እንዲወያዩና በአካባቢያቸው ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስልት ነድፈው እንዲያመጡ ተጠየቁ:: ምላሻቸው ግን ባንገረዝ ወይም ልጆቻችንን ባናስገርዝ ኖሮ የማግባትና የመውለድ ዕድል አይኖረንም ነበር የሚል ነበር::

በአፍሪካ ውስጥ ድርጊቱን ለመለወጥ የተደረገ ሙከራ

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ የባህል ለውጥ ለማምጣት ከመሞከር አንጻር ኬንያ ረዥም ታሪክ አላት:: በ1921 ዓ.ም በኬንያ ውስጥ ባሉት በኩኩዩ ማኅበረሰቦች መካከል የሚሠሩት የኤ ኣይ ኤም (AIM) ሚስዮናውያን የሴትን ግርዛት የሚደግፉ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዳይሆኑ ወሰነው ነበር:: በተለይ በኪጃቢ ጣቢያ ትሠራ የነበረችው ሁዳ ስታምፍ የተባለች ሴት፣ በሴቶች ትምህርት ቤት ውስጥ የሴትን ግርዘት በመቃወም ጠንከር ያለ አቋም ይዛ ነበር:: በዚህ ወቅት፣ ሚሲዮናውያን በመሬት ጉዳይና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እንዳይሰጥ በማድረግ የቅኝ ገዢ ባለሥልጣናትን እንደሚደግፉ ይታሰብ ነበር:: ምናልባትም በ1930 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የሁዳን አስገድዶ መገረዝ እና መገደል ያመጣው የእነዚህ ጉዳዮች መጣመር ይሆናል:: ይህ ጉዳይ ብዙዎችን ከአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ

አድርጓል። እነዚህ ለየት ያለ አሳብ የነበራቸው ሰዎች የራሳቸው ቤተ ክርስቲያናትንና ትምህርት ቤቶችን አቋቁመዋል (ሮበርት፣ ገጽ 230)። በኬንያ በጉዳዩ ላይ ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል ትምህርት ቢሰጥም፣ ያመጣው አዎንታዊ ውጤት ግን ጥቂት ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ድርጊቱ ሥር እየሰደደ ሄዷል። በሌላ አካባቢዎች ደግሞ ትምህርቱ ያመጣው ጥቂት ውጤት፣ ወላጆች ከባህላዊ ቆራጮች ይልቅ የጤና ባለሙያዎች ድርጊቱን ይፈጽሙ ዘንድ መጠየቃቸው ነው። እኔ እንደማምነው፣ ይህ የተፈጠረው የለውጥ ግፊት ከባህሉ ውጭ በሆኑ ሰዎች አማካይነት ሲመጣና በጉዳዩ ላይ የሚሰጡት ትምህርቶች የማኅበረሰቡን ዋና ዋና እሴቶች ሳይነኩ ሲቀሩ ምን እንደሚፈጠር የሚያሳይ አሳዛኝ ምሳሌ ነው።

እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ፣ በግብጽ ውስጥ የሴትን ብልት መቁረጥ የሚታየው እንደ ቀዶ ጥገና ሂደት ነው። ድርጊቱ የጤና ባለሙያ በሆነ ሰው ሳይፈጸም ቀርቶ፣ መቆረጥ ካለበት በላይ ቢቆረጥ ለጤና ጐጂ እንደ ሆነ ይታሰባል (ኤል ሐዲ፣ ገጽ 156)። ኤል ሐዲ እንደሚሉት፣ በግብጽ ውስጥ ልማዱን ለማስወገድ የተደረገው ሙከራ ትኩረት የሚያደርገው ድርጊቱ በሚያስከትላቸው የጤና እና የወሲብ ጠንቆች ላይ ነው። ድርጊቱን ከጤና ጋር አያይዞ ትኩረት መስጠቱ ሰዎቹ ስለ ችግሩ ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምርና ድርጊቱን ለመፈጸም ዘመናዊ የጤና ተቋማትን የመጠቀም ዝንባሌ እንዲጨምር አድርጎታል። ሆኖም ግን፣ የሴት ውጫዊ ብልት የመቁረጥን ድርጊት የሚያነሣሣውን እሴት እንዲለወጥ ወይም ድርጊቱን እንዲቀንስ አላደረገውም። የሴቶችን እውነተኛ ተሞክሮ ግምት ውስጥ ስለማያስገቡ፣ የማስተማር ዘመቻዎቹ ተአማኒነት የላቸውም። ጥናት የተደረገባቸው ብዙ ሴቶች ለጥናቱ በሰጡት መረጃ፣ ድርጊቱ በወሲብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሌለው አስተባብለዋል። ስለዚህም ከብልት መቆረጡ የተነሣ የሚፈጠሩትን ችግሮች ማጋነን፣ እንቅስቃሴውን በሚያደርጉት ሰዎች መልእክትና ግብጻውያኑ ሴቶች በሚጋፈጡት እውነታ መካከል የተአማኒነት ክፍተት ተፈጥሮአል (ኤል ሐዲ፣ ገጽ 160)።

እነዚህ ምሳሌዎች ስለ ባህል፣ ለውጥ እና ለውጡ ስለሚመጣበት መንገድ ጥቂት ጠንካራ ጥያቄዎችን እንድንጠይቅ አድርገውናል።

ባህልን ለመቀየር የሚደረው ጥረት ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል ነው ወይ?

የሥነ ሰብ ጥናት (Anthropology) እንደ አንድ ሙያ (ሥልጠና) ሆኖ ብቅ እንዲል ያደረገው የምዕራባውያኑ አሰሳ (Exploration) የአውሮፓውያኑን ማኅበረሰብ ከአፍሪካ፣ እስያ፣ አሜሪካ እና በፓስፊክ ደሴት ካሉ ማኅበረሰቦች ጋር ስላገናኘው ነው። እዚህ ላይ ልናስተውላቸው የሚገቡ ሁለት ምላሾች አሉ። የመጀመሪያው ምላሽ ማንኛውም የተለየ ሰው ያልሠለጠነ እና አላዋቂ እንደ ሆነ በማሰባቸው አውሮፓውያን በትምህርት አማካይነት ሥልጣኔ እና እውቀትን ለማምጣት የሥነ ምግባር ኃላፊነት እንዳለባቸው ተደርገው መቆጠራቸው ነው። በዚያ ጊዜ የአውሮፓውያን የማስተማር ሂደት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ እንደ መሆኑ መጠን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና ክርስትና ሰዎችን የማስተማሩ ሂደት አካል እንደ ሆነ ይቆጠር ነበር። ሌላው ሰብአዊነት የጎደለው ተለዋጭ አስተሳሰብ ደግሞ ራሳቸውን እንደ «ሙሉ ሰው» አድርገው የሚቆጥሩ እና አዳዲስ የተገኙትን ሕዝቦች «አነስተኛ ሰው» እንደ ሆኑ የሚያምን ነው። ይህንን አሳብ በመቀበላቸው ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች በባሪያ ገዥ ሥርዓት ላይ ጥያቄ አልነበራቸውም።

ሥነ ሰብ እንደ ልዩ የሙያ ዘርፍ ሆኖ ሲገለጥ ግን፣ ተመራማሪዎች «ብአሰሳው ወደ ተገኙት አዳዲስ ሰዎች» ዘንድ ለመኖር መሄድ ጀመሩ። በእንግድነት የሄዱባቸው ሕዝቦች ከእነርሱ የሚለዩበትን የአኗኗር ዘይቤአቸውን መጻፍ ዓላማ አድርገው ቋንቋቸውን አጠኑ። የሥነ ሰብ ተመራማሪዎቹ የተለያዩ ባህሎችን ሲገነዘቡ፣ ልዩነት ማለት «ስሕተት» ወይም «ኋላ ቀርነት» ማለት ያለመሆኑን እና በሁሉም ባህል ውስጥ ሥርዓትና ምክንያት እንዳለ ቀስ በቀስ እየተገነዘቡ መጡ። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ እንደ

ጋብቻ፣ መንግሥት፣ ዝምድና ብሎም እንደ መሸጋገሪያ ሥርዓት ያሉ ሥርዓቶች መኖራቸው እየታወቀና እየተደነቀ መጣ። ይህ እያደገ የመጣ በሌላ ባህል ያለን ጥሩ ነገር ማድነቅ «ኖብል ሳቬጅ» (Nobel Savage) ወይም «ላልሠለጠኑት ክብር» የሚለውን አስተሳሰብ አስነሣ። ይህም ያለ ዘመናዊው ቴክኖሎጂ በምድራቱ ላይ የሚኖሩ ሰዎች፣ አውሮፓን ባጥለቀለቀው የስነታምነትና ቁሳዊ አስተሳሰብ ሳይበላሹ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው የሚኖሩ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ ያጠቃልላል። የአዝጋሚ ለውጥ (Evolution) ጽንሰ አሳብ ሃይማኖትን የሚያስቀምጠው ግዑዝን ነገር ከማምለክ ተነሥቶ አንድ አምላክን በማምለክ አልፎ ወደ ሳይንስ እንዳደገ ነው። «የመጀመሪያውን ሃይማኖት» በማነቃቃት ወደ መነሻችን እንመለስ፣ የቀደመውን የሥረ መሠረታችንን ሰብአዊ ማንነት እንወቅ የሚለው አሳብ የዘመኑ ፋሽን ሆኗል። ይህ ደግሞ የዓለም ባህል በውጭ አስተሳሰብ መበላሸት የለበትም፣ ስለዚህም «በመጀመሪያ» ሁኔታቸው ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚቻለው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት ከሚለው አስተሳሰብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የ«ንጹሕ» ባህል አስተሳሰብ ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን «ፖስት-ሞደርኒዝም» (Post- Modernism) ወይም የድኅረ ሥልጣኔ ፍልስፍና ተላልፏል። ይህ ፍልስፍና አንጻራዊ ዓለም የሚል ሲሆን፣ የሚለውም ፍጹም የሆነ ነገር ስለሌለ፣ ትክክል የሆነውን ከስሕተቱ የሚለካበት ወይም የሚወሰንበት ፍጹም ነገር የለም የሚል ነው። እንግዲህ ባህልን *መገዳደርና መቀየር ትክክል ነው ወይ?»* የሚለውን ጥያቄ *መጠየቅና* መልሱንም *መፈለግ* ያለብን በዚሁ ዐውድ ውስጥ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍጹምነት (Biblical Absolutes) እና በባህላዊ አንጻራዊነት (Cultural Relativity) መካከል ያለውን ችግር እንድንተነትንና እንድናስብ የሚረዳን ጠቃሚ የአስተሳሰብ ናሙና ሜየርስ አቅርበውልናል (ግሩንላን እና ሜየርስ ገጽ 256 እና ሜየር 248)። በሰፊው የባህል ዐውድ ያቀረቡትን አሳቦች ለመረዳት ጥረት እናደርጋለን፣ ስለዚህም እነዚህን አሳቦች የሴትን ውጫዊ ብልት

መቁረጥ በሚለው ጥያቄ ላይ ለማዋል የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ ለመጠቀም እንሞክራለን::

		መጽሐፍ ቅዱሳዊ	
		አንጻራዊነት	ፍጹማዊነት
ባህል	ፍጹማዊነት	ሀ የሁኔታ ሥነ ምግባር	ለ ልማዳውያን
	አንጻራዊነት	መ የሕግ ተቃርኖ (ሕግ የለሽ)	ሠ የጋራ መከባበር

የ«ኖብል ሳቬጅ ጽንሰ አሳብ አራማጆች አንጻራውያን (Relativists) ናቸው:: እነርሱ በባህል ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር በባህሉ ውስጥ ባለው ሰው ዘንድ ትክክል ነው ይላሉ:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንጻራዊ (Biblical Relativist) የሆነ ሰውም መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ተመሳሳይ ነገርን ይናገራል:: እንደዚህ ዓይነት ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ለእኔ ትክክል ነው ነገር ግን ለሁሉም ሰው ትክክል ላይሆን ይችላል ይል ይሆናል:: ይህ አባባል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገርን ይላል የሚል አንድምታ አለው::

ሜየርስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ባህላዊ አንጻራውያንን (Biblical & Cultural Relativists) የሆኑ ሰዎች ሕግ እንደሌላቸው (Antinomian) አድርገው ገልጸዋቸዋል (በሳጥኑ ውስጥ «መ» ን ይመልከቱ):: በዚህ ምድብ ያሉ ሰዎች፣ አንድን ነገር ትክክል ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመወሰን ተጨባጭ የሆነ መንገድ እስከሌለ ድረስ፣ በባህሎቹ ውስጥ ያሉ ሰዎች ድርጊቱን ባሉበት ሁኔታ ጥሩ ከመሆኑ አንጻር አይተው የራሳቸውን መመሪያ መደንገግ ይችላሉ

ይላሉ። ተመሳሳይ የሆነ ግብረ ገባዊነት ግጭት (Moral Dilemma) የገጠማቸው ሁለት ሰዎች ለጉዳዩ ፍጹም የተለየ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። አንጻራውያን ሁለቱም ምላሾች በእኩል ደረጃ ዋጋ እንዳላቸው አድርገው ይቀበሏቸዋል። በተግባር ሲታይ ግን፣ እንደዚህ ዓይነት አቋም ለመያዝ የማይቻል ነው። በአንድ ባህል ውስጥ ያሉ ሰዎች ከባህል ተለይተው ሊኖሩ አይችሉም፣ እንዲሁም ደግሞ ባህሎች ከሌሎች ባህሎች ተለይተው ሊኖሩ አይችሉም። አንድ ሰው እንደ ግለሰብ የሚፈጽመው ድርጊት እና አንድ ባህል ጥሩ ወይም መጥፎ ብሎ የሚቀበለው ነገር በባህሉ ውስጥ እና ውጭ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ አለው። ይህ መርሖ በባህል ውስጥ፣ ለሴት ውጫዊ መቆረጥም ድርጊት ተግባራዊ ሲሆን፣ ችግሩ ግልጽ ይሆናል። «የምትገረዘው» ሴት ድርጊቱ ትክክል እንዳልሆነ ብታምን እና «ገራዥዋ» ደግሞ ትክክል ነው ብትል ውጤቱ ግጭት ይሆናል። ከዚህም የሚያሸንፈው በአካል የበለጠ ጠንካራ የሆነው ይሆናል።

ይህንን ምዕራፍ እየጻፍኩኝ ሳለ፣ ችግሩን በግልጽ የሚያሳይ ጭቅጭቅ በኬንያ ተነሥቶ ነበር። በቅርቡ ኬንያ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን ሕገ ወጥ የሚያደርግ ሕግ አውጥታለች። የተወሰኑ ልጃገረዶች በአንድ የክርስቲያን ድርጅት አማካይነት በተዘጋጀ ተለዋጭ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ዝግጅት ላይ እንዲገኙ ተደረገ። ወቅቱ ልጃገረዶቹ የትልቅነት ደረጃ ለማግኘት የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ሁሉ፣ ከግርዘቱ በስተቀር፣ ተደረገላቸው፣ ሊማሩ የሚገባቸውንም ነገሮች ተማሩ። በባህላቸው ግን ግርዘት ወደ አዋቂነት የመሸጋገሪያ ሥርዓቱ አካል ነው። ታዲያ እነዚህ ልጃገረዶች ወደ ቤት ሲመለሱ በአስቸኳይ «እንዲገረዙ» ግፊት ተደረገባቸው። እነርሱም ድርጊቱን የሚከላከል ሕግ እንዳለ ስላወቁ አምልጠው ሊረዳቸው በሚችል ድርጅት መጠጊያን ጠየቁ። ወላጆቹም ለፍርድ ሊቀርቡ ሆነ። በዚህ ጊዜ ባህላዊ አንጻራውያን፣ ክርስቲያናዊ ድርጅቱ፣ የኬንያ ሕግ

አውጭዎች፣ የሴቶቹ ወላጆች እና ባህላዊ ልማዱ ሁሉ ትክክል ናቸው ይላሉ። እንዲህ ዓይነቱን አቋም መያዝ እንደማይቻል ግልጽ ነው።

ምናልባት ብዙ ሰው ባህላዊ ፍጹማውያን (Cultural Absolutes) ሊሆኑ ይችላሉ። ባህላችን በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ጥሩ ነው፣ እናም እያንዳንዱ ሰው በእኛ ባህል መሠረት ቢኖር፣ ሥርዓት ይኖራል ብለን ወደ ማመን እናዘነብል ይሆናል። እኛ ነገሮችን የምናደረግበት መንገድ፣ አንድን ነገር ትክክል ነው አይደለም ብለን የምንወስንበት ሕግ ይሆናል። ባህላዊ አናጻራውያን ክርስቲያኖች ሲሆኑ፣ ከሚከተሉት ሁለት ነገሮች መካከል አንዱ ይሆናል። የመጀመሪያው ሊሆን የሚችለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንጻራውያን (Biblical Relativists) መሆን ነው (በሳጥኑ ውስጥ «ሀን» ይመልከቱ)። በዚህ ምድብ ያሉ ሰዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ዐውድ ውስጥ በተለያየ መልኩ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ግብረ ገባዊ እሴቶች (Moral Values) አሉት ይላሉ። እንደ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ላሉት ችግሮች፣ ድርጊቱ ትክክለኛ ነው ከሚል አቋም ይቀጥሉና መጽሐፍ ቅዱስ ከባህሉ አንጻር መተርጎም አለበት ይላሉ። እንዲህ ዓይነት አቋም ያላቸው ሰዎች መሰፋቱ (Infibulation) ሴቷን ከጋብቻ ውጪ የወሲብ ግንኙነት እንዳታደርግ የሚላከል ከሆነ፣ ድርጊቱ ትክክል ነው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ።

ሁለተኛው ሊሆን የሚችለው አማራጭ ደግሞ ባህላዊ አንጻራውያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንጻራውያንም (Biblical Absolutist) መሆን ነው (በሳጥኑ ውስጥ «ለ»ን ይመልከቱ)። እውነተኞች ከሆንን፣ ይህ ብዙ ክርስቲያኖች፣ በተለይም ከአንድ ባህል ብቻ የመጡ ሰዎች ባሉበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ፣ የሚገኙበት ምድብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እና ባህል ሁለቱም ገላጭ (Normative) እንደ ሆኑ ይታሰባል። «ባህሌ ጥሩ ነው፣ ጥሩ የሆነ ነገር ሁሉ ደግሞ ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ እኔ ነገሮችን የማደርግበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው» ወደሚል አስተሳሰብ

ይወስዳል። ይህም ከእኔ ውጭ የሆነ ባህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ሊል ጥቂት ብቻ የቀረው ነው። ወግ አጥባቂዎች (Traditionalists) ለባህላዊ ድርጊቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫን ይፈልጋሉ።

ይህ ለባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት መወገድ የታገሉ ሰዎች አቋም ነበር። የባሪያ ሥርዓት ለደቡብ አፍሪካ፣ ለሕንድ እና ለአሜሪካ እድገት ጥቅም ስለ ነበረው፣ ጉዳዩ ይታሰብ የነበረው እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍጹማዊነት ነበር። ክርስቲያን የነበሩ ባሮች ጌቶቻቸውን እንዲሰሙ እና መልካም ባሮች እንዲሆኑ ይመከሩ ነበር። አንድ ወግ አጥባቂ፣ «እግዚአብሔር የሙዚቃ መሣሪያዎችን ተጠቅመን እንድናመልክ ይነግረናል፣ የእኔ ባህል ደግሞ ከበሮ እና ኦርጋን ይጠቀማል። ስለዚህ ከበሮና ኦርጋን ተጠቅሞ ማምለክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ማንም ጊታር የሚጠቀም ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም» ይላል።

ከላይ ከቀረቡት የአስተሳሰብ ናሙናዎች መካከል አንዳቸውም፣ «ባህልን መለወጥ ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል ነው ወይ?» ለሚለው ጥያቄ አርኪ መፍትሔ አይሰጡም። ሜየርስ ያቀረቡት አራተኛው የአስተሳሰብ ናሙና ጥያቄውን ለመመለስ ጥቂት ይረዳናል (በሳጥኑ ውስጥ «ሠ» ን ይመልከቱ)። ይህም አስተሳሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ላይ ሳናቅማማ፣ በባህላችን ውስጥ እንድንሠራ በማድረግ ይህንን ጥያቄ እንድንመልስ ይረዳናል። ይህንን «የጋራ መከባበር» (Mutual Respect) ብለውታል። ይህ የአስተሳሰብ ናሙና መጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም፣ ባህልን ደግሞ አንጻራዊ የሚል ነው። ይህ ማለት፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና ባህል በሚጋጩበት ጊዜ፣ ባህል መቀየር አለበት። ደንብ መሆን ያለበት ባህል ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ለማረጋገጥ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ፣ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ባህል በቁም ነገር መታየት አለባቸው።

የአሳብ ናሙና ባህላዊ አንጻራዊነትን ከሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (Ethical Relativism) ጋር እንዳይምታታብን ያደርጋል። ባህላዊ ልምድ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር በማይጣረስበት ሁኔታ ውስጥ ልምምዱ መወገዝ የለበትም። የመጽሐፍ ቅዱሳዊነት አስተሳሰብ ተግባር ላይ የሚውልበት ቅርጽ (Form) በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የተለያየ ይሆናል። ስለሆነም፣ ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር መስረቅ ትክክል አይደለም ይላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ሥነ ምግባራዊ ፍጹማዊነት ነው። ይሁን እንጂ፣ እያንዳንዱ ባህል ባለቤትነትን (Ownership) እና ይዞታን (Posession) በተመለከተ የራሱ ግንዛቤ አለው። ይህ ግንዛቤ ታዲያ መስረቅ የሚለው ቃል ተግባር ላይ ሲውል የተለያየ ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል። በኢየሱስ ዘመን በአንድ ሰው ማሳ ውስጥ መተላለፍ እና ለመብላት ፍሬን መቅጠፍ ተቀባይነት ነበረው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ግን በንግድ እርሻ ውስጥ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ እንደ ስርቆት ይቆጠራል። በኢትዮጵያ ውስጥ፣ ባህላዊ ሙዚቃዎችን በነፃ መጠቀም ከባህልም ሆነ ከሥነ ምግባር አንጻር ተቀባይነት አለው። ነገር ግን፣ ዘመናዊ ሙዚቃዎችን ያለ ክፍያ ማባዛት ባለቤቱና ጸሐፊው ከሥራው የሚያገኙትን ገቢ መውሰድ ስለ ሆነ፣ እንደ ስርቆት ይቆጠራል። በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ፣ መጠሪያ ስም እንደ ግል ንብረት ስለሚቆጠር፣ በአንድ ሰው ስም ልጅህን ብትሰይም ሰርቀሃል ማለት ነው።

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ይህንን መርሕ በቁም ነገር አይተነዋል። የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጡን ድርጊት በቁም ነገር የሚወስዱ ብዙ የጉዳይ ጥናቶች (Case Studies) ቀርበዋል። ከሥርዓቱ ጋር አብረው የሚሄዱት አንዳንዶቹ ተግባራት (Functions) ጥሩ ናቸው። መቆረጡ የመሸጋገሪያ ሥርዓቱ አካል ሲሆን፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ የመሆን ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ የተለየ የማስተማሪያና ከልጅነት ወደ አዋቂነት ምናልባትም ወደ ጋብቻ-የመሸጋገሪያ ወቅት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእነዚህ መካከል

አንዱንም እንኳ አይኮንንም። ይሁን እንጂ፣ እኛ የብልት መቆረጡ በጤና ላይ የሚያስከትላቸውን ተጽዕኖዎች እና የድርጊቱን ምክንያቶች ጭምር በቁም ነገር አይተናቸዋል።

እነዚህን ምክንያቶች እና የድርጊቱን ውጤት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ጠንከር አድርገን በታማኝነት ማየታችን ድርጊቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጭ ነው የሚል እምነት እንድንይዝ ያደርገናል። ባህላዊ ድርጊት ከእግአብሔር ቃል ጋር የሚጋጭ ከሆነ፣ ግጭቱ ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ታዲያ ይህ ሆኖ እኛ ድርጊቱን ካልቀየርነው ከሥነ-ምግባር አንጻር ትክክል አላደረግንም ማለት ነው።

ኤል ሐዲ ይህንኑ አስመልክታ ስትጽፍ እንዲሁ ብላለች፡-

> . . የባህሉን ዐውድ ከግምት ውስጥ ማስገባታችን በድርጊቱ ትክክለኝነት ወይም ስሕተተኝነት ላይ ፍርዳችንን ከመስጠት አያድነንም። ይልቁንም፣ እንዲህ ማድረጋችን ድርጊቱን ለመለወጥ በምንመርጠው ስልት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

ታዲያ ባህሉን ለመቀየር መምረጥ ያለብን አንዳንድ ስልቶች ምንድን ናቸው?

ቅርጽ እና ትርጉም

«የሴቶች ግርዘት መቆረጥ ነው ብሎ በመናገር ሰዎች ባሕርያቸውን እንዲቀይሩ ልናሳምናቸው አንችልም» (አቡሻራፍ፣ ገጽ 127)። በዚህ አባባል ጸሐፊዋ ብትስማማም፣ አቡሻራፍ ግን ይህ የማይሆነው ለምን እንደ ሆነ በደንብ አልመረመሩም። አንድ ሰው መርዝ መጠጣት እንደሚገድለው/ላት ብትነግሯቸው፣ የሚገድለውን ነገር መጠጣት ያቆማሉ። ነገር ግን፣ ሰውየው ማስጠንቀቂያው ከተሰጠው በኋላ ቢጠጣ እና ቢሞት፣ ሰዎች የመረጃውን እውነትነት ያምናሉ! የሚገርመው ግን፣ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ እና ሌሎች ባህላዊ የጤና ድርጊቶች የሚያስከትሉትን ጉዳት ሰዎች ቢያውቁም እንኳ ድርጊቱ መፈጸሙ ቀጥሏል። አንዳንድ ባሕሪዎች ለመለወጥ ለምን አስቸጋሪ ይሆናሉ?

ሜየርስ ቅርጽ ብለው የሚጠሯቸው፣ ባህል የያዛቸውን

ተጨባጭ ነገሮችን ነው። ቅርጾች የሚያጠቃልሉት ቁሳዊ ባህል (ዕቃዎች)፣ ቃላዊ የሆኑና ቃላዊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን ነው። ቅርጽ እንደ እምነቶች፣ እሴቶችና ደንቦች ያሉ የማይታዩ ነገሮች የሚተላለፉበትና የሚገለጹበት መንገድ ነው። እነዚህን የማይታዩ ነገሮች መግለጫ የሆኑትን ነገሮች ሜየርስ ትርጉም ብለው ይጠሯቸዋል (ገጽ 230)። ትርጉም የሚገለጸው በቅርጽ አማካይነት ነው።

ብዙ ቅርጾች በራሳቸው ገለልተኛ ሲሆኑ፣ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ግን አሉታዊ፣ አሉንታዊ ወይም የተለያዩ ትርጉሞች ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ፣ ማቀፍን (ቅርጽ) ብናይ፣ ይህ ድርጊት በአንድ ባህል ውስጥ የሰላምታ፣ በሌላ ባህል ውስጥ ግን ወሲባዊ ቅርርብን መግለጫ ሊሆን ይችላል። የወንዶች እጅ ለእጅ መያያዝን (ቅርጽ) ብናይ፣ ይህ ድርጊት በብዙ የአፍሪካውያን ባህል ውስጥ የጓደኝነት መግለጫ ሲሆን (ትርጉም)፣ በብዙ የአውሮፓ ባህሎች ውስጥ ግን የወሲብ ቅርርብ መግለጫ ነው። የወርቅ መስቀል በሰንሰለት አድርጉ በአንገት ላይ ማንጠልጠል፣ በአንድ ባህል ውስጥ ሰውዬው ክርስቲያን መሆኑን ሲገልጽ፣ በሌላ ባህል ውስጥ ደግሞ ከክፉ መንፈስ ለመጠበቅ ያለን ፍላጎት የሚያመለክት ነው። ከበሮ በአንድ ባህል ውስጥ የበዓልና የደስታ መግለጫ ሲሆን፣ በሌላ ባህል ውስጥ ደግሞ ከጥንቆላ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ሁለቱም ቅርጽም ሆነ ትርጉም በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ፣ የምርት መበላሸትን ለመከላከል (ትርጉም) ልጅን በወንዝ ውስጥ መወርወር (ቅርጽ)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቅርጹ ተቀባይነት የሌለው ይሆንና ተግባሩ ግን ዋጋ ይኖረዋል። አንዳንድ የመሸጋገሪያ ሥርዓቶች ከልጅነት ወደ ጉልምስና መሸጋገር እና ልጆቹን የአዋቂነት ኃላፊነት የማሠልጠን ተግባር (Function) አላቸው። ይሁን እንጂ፣ የሥርዓቱ አካል የሆኑት ብዙዎቹ ድርጊቶች ወይም ቅርጾች ለሰውነት ጎጂ የሆኑ አሠራሮችን፣ ወይም ባዕድ አምልኮዎችን፣ ወይም ሰይጣናዊ ልምምዶችን፣ ወይም ደግሞ ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆኑ

ድርጊቶችን ያካትታሉ። መሸጋገሪያ ወቅት ትምህርት የሚሰጥባቸው አንዳንድ ነገሮች ጠቃሚ ሆነው ሳሉ፣ የማስተማሪያው መንገዱ ግን ትክክል አይደለም።

ባህሎች አንዱ ከሌላው ጋር ሲገናኝ እና ባህሉ ውስጥ ያሉ ሰዎች አዳዲስ ነገሮችን ፈልገው ሲያገኙ፣ ሲፈጥሩና ሲፈለስፉ ቅርጾች ይቀየራሉ። በባህሎች መካከል ከሚፈጠር መገናኘት የተነሣ የሚመጣው ለውጥ የውጭ ባህል መቀበል (Acculturation) ይባላል። ይሄ የባህል መገናኘት በዓለም ውስጥ ባሉ በሁሉም ባህሎች ውስጥ ያለ ሲሆን፣ በቁሳዊ ባህል፣ በቴክኖሎጂ እንዲሁም በኢኮኖሚ ውስጥ እናየዋለን። ይህም በግንኙነት፣ በማኅበረሰባዊ ቁጥጥር እና በመንግሥት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። እንደዚህ ዓይነት ለውጦች በተለየ ሁኔታ ጎልተው የሚታዩት ደግሞ ከአጅ ወደ አፍ ከሆነ ግብርና ወይም ከአርብቶ አደር ዘላንነት ባህል ወደ ቴክኖሎጂያዊ፣ ገበያ-ተኮር ኢኮኖሚ በተሸጋገረ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ነገሮች እሴቶችንና ንጽረተ ዓለምን ሳይቀይሩ ሊለወጡ ይችላሉ። አዲስ ቁሳዊ ባህል አብዛኛውን ጊዜ ከባህሉ ጋር አግባብነት ያለው ትርጉምና እሴት ይሰጠዋል። አዳዲስ ቴክኖሎጂ እና የኢኮኖሚ ለውጦቹም በተመሳሳይ ሁኔታ የባህሉ እሴቶች እና የእምነት ሥርዓት ሆነው ሊቀረጹ (ሊስተካከሉ) ይችላሉ።

አሁን፣ እነዚህ ሁሉ የሴትን ውጫዊ ብልት ከመቁረጥ ጋር እንዴት ይዛመዳሉ? በአውሮፓ የሴቶችን ብልት መቁረጥ የሕክምና ድርጊት ነው። እንደ መድኃኒት (ቅርጽ) ይለወጣል፣ የሴት ውጫዊ ብልትን የመቁረጥ ድርጊትም የተወገደው ከዚህ በኋላ ትርጉም ስለሌለው ነበር። ይሁን እንጂ፣ በምዕራፍ 2 ውስጥ የቀረበው ጥናት የሚያሳየው በአፍሪካ ውስጥ የሴቶችን ውጫዊ ብልት መቁረጥ በመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ድርጊት ያለመሆኑን ነው። በጠቅላላው ንጽረተ ዓለማቸው ውስጥ ሥር ሰዷል። በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በዝምድና፣ በወሊድ እና በጉርምስና ሥርዓቶቹ፣ በጋብቻ፣ በኑሮ ደረጃ፣ በማኅበራዊ መዋቅር እና በኢኮኖሚ አቅጣጫዎች ድርጊቱ ትርጉም አለው። አንዳንድ ጊዜ የጎሣው

አጠቃላይ መዋቅር የሚሸከረከረው የሆነ ዓይነት አካላዊ መቆረጥን የጠቅላላ ሥርዓቱ አንድ አካል አድርጐ በሚይዝ ምሥጢራዊ ማኅበረሰቦች እና የጉርምስና ሥርዓቶች ዙሪያ ይሆናል።

ስለዚህም አካላዊ እና የጤና አደጋዎችን በተመለከተ በማስተማር ደረጃ ከለውጥ አንጻር የሚፈለገውን ውጤት ባያስገኝ የሚያስገርም አይደለም። የተገኙት ተደጋጋሚ ለውጦች ሁሉ የቴክኖሎጂ ለውጦች ናቸው። «የተማሩ» ወላጆች ገራገሮች ለሚቆርጧቸው ለእያንዳንዶቹ ሴቶች አዲስ ምላጭ እንዲጠቀሙ ወይም ልጃገረዶቹ ንጹሕ መሣሪያዎች እና ማደንዘዣ ጥቅም ላይ ወደሚውልበት ክሊኒክ እንዲሄዱ አጥብቀው ይጠይቃሉ። ነገር ግን ጥልቅ እና ዘለቄታዊ ለውጥ ለማየት የምንፈልግ ከሆነ፣ እምነቶችንና አስተሳሰብን በመለወጥ ሥራ መጀመር አለብን።

ጥቅም ያላቸውን ልዋጮች መጠቀም

አንድ ባህላዊ ድርጊት ዋጋ ያለው በሚሆንበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ውጤት የሚያመጣ ተለዋጭ መንገድ ለማቅረብ በጥንቃቄ ማሰብ አለባት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ለውጥ አንድን ነገር ከባህል ውስጥ የሚያስወግድ ዓይነት ከሆነ፣ ድርጊቱን በተሻለ ሌላ ነገር መተካት አለብን። ይህንን ካላደረግን ግን፣ ድርጊቱን ማስቀረት የበሰበሰን እንጨት ከሕንፃ ውስጥ እንደ ማስወገድ ነው። በጥሩ፣ ጠንካራ እና አዲስ እንጨት ወይም ደግሞ በሌላ ነገር ካልተካነው፣ ሕንፃው በጠቅላላ ሊወድቅ ይችላል። ስለዚህም፣ ለምሳሌ፣ ሴትን ለጋብቻ ብቁ የሚያደርጋትን ድርጊት ለማስወገድ የምንጥር ከሆነ፣ ጋብቻው ሊፈጸም የሚችልበት ተቀባይነት ያለው ባህላዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ (ተለዋጭ) መንገድ መፈለግ አለብን።

ጆን ምቢቲ የአካምባን የግርዘት እና የመቁረጥ ሥርዓት እንደገና በመተርጎም የተለዋጭ መርሕን ተግባራዊ አድርገዋል። መገረዝ ለአካምባዎች የአዋቂ ሰዎች ቡድን በሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ የመሳተፍ ሙሉ መብትን ይሰጣል። ወጣቶቹን የጎሳው

አካል አድርጎ የሚያስቆጥራቸው ሲሆን፣ እንዲሁም የመገለልና የትምህርት ወቅትም ነው። ምቢቲ እንደሚሉት፣ የክርስቲያን ጥምቀት በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ የመግባት እና ከአሮጌው ሕይወት የመለየት ምልክት ነው። ከጥምቀት በፊት ባለው የትምህርት ጊዜ ሰውየው ስለ አዲሱ ዜግነት ደስታና ኃላፊነት የሚማርበት ጊዜ ነው። እንደ አካምባዎች ግርዘት ሳይሆን፣ ጥምቀት አማኞቹን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኛቸው ነው (1971፣ ገጽ 122)። ይህ የጥምቀትንና የጌታ እራትን ተምሳሌትነት የበለጸገ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ ከግርዘት ተምሳሌትነት የበለጠ ትርጉም ያለው እንዲሆን ያደርገዋል።

የኬንያ ማራክዌት ከመቶ በላይ ልጃገረዶችን በአንድ ላይ ብልታቸውን የሚቆርጡበት ሥርዓት አላቸው። ይህ ሥርዓት ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የሚሰጠውን ትምህርት ያጠቃልላል። የወርልድ ቪዥን፣ ክርስቲያናዊ የግብረ ሰናይ ድርጅት፣ ዳይሬክተር የሆኑት ዳንኤል ኪፕቱጂን አዕምሯዊ የሴቶች የመሸጋገሪያ ሥርዓት (Intellectual Female Initiation) ብለው የሚጠሩትን ሥርዓት አስተዋውቀዋል። በዚህ ሥርዓት ወጣት ሴቶች በዓመት አንድ ጊዜ የማራክዌት ልማዶችን እና እሴቶችን ይማራሉ። ትምህርቱንም ያጠናቀቁ በሴትነት ክብር (Status of Woman) «ይመረቃሉ» (ቼቡሲሪ፣ ገጽ 54)።

በኬንያ ለውጥን ለማፋጠን የሚረዳ ተመሳሳይ ፕሮጀክት «በቃላት አማካይነት መገረዝ» (Circumcision Through Words) በመባል ይታወቃል። እነዚህ ሴቶች ተገልለው የሚቀመጡበት ወቅት አላቸው። በዚህ ወቅት ከጤና ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ይማራሉ። በመገለሉ ማብቂያ ላይ ግብጣ ይደረጋል። ይህ ልዋጭ ሥርዓት በተዋወቀበት አካባቢዎች የሴት ውጫዊ ብልት የመቁረጥን ልምድ 15% እንደ ቀነሰ ይነገራል (ሮቢንሰን፣ ገጽ 70)።

እኛ፣ ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን፣ ከእነዚህ ትምህርታዊ ልዋጮች የበለጠ የምንሰጠው ልዋጭ አለን።

በክርስቶስ ስለሚገኝ አዲስ ሕይወት ልናስተምር እና ሴቶች ክርስቶስ ያደርጉት ዘንድ የሚፈልገውን ነገር በማድረግ፣ የማጎበረሰባቸውን እሴቶች መጠበቅን ጨምሮ፣ መልካም ተምሳሌት እንዲሆኑ ማስተማር እንችላለን።

ሌሎች የለውጥ ወኪሎች

የለውጥ ወኪሎች በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ያሉ መሣሪያዎች ሲሆኑ፣ እግዚአብሔር ለውጥን ለማምጣት ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ብዙ መሣሪያዎች እንዳሉ ተረጋግጧል። በጣም ውጤታማ የሆነው የለውጥ ወኪል መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ እርሱም በትክክለኛው የእግዚአብሔር ቃል ስብከት አማካይነት እንደሚሠራ አረጋግጠናል። በሰዎች አመለካከት ላይ ጥልቅ የሆነ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለውና ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንዲሠሩ ኃይል የሚሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህን እንጂ፣ እግዚአብሔር ሌሎች መንገዶችንም የለውጥ ወኪሎች አድርጎ ይጠቀምባቸዋል።

ድርጅቶች

በሴኔጋል መንደሮች የሚሠራ ቶስታን (TOSTAN) በመባል የሚታወቅ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ግብረ ሠናይ ድርጅት የመሠረተ ትምህርት፣ የተዋልዶ ጤና እና ሌሎች ትምህርቶችን ያጠቃለለ ሥልጠና ይሰጣል። በዚህ ሰፊ ሥልጠና መሠረት ሴቶቹ ራሳቸው ሊያስወግዷቸው የሚፈልጉትን ጉዳይ ይወስናሉ። በዚያም ሴቶቹ የሴትን ብልት መቁረጥ ሊያቆሙት የሚፈልጉት ድርጊት መሆኑን ወስነዋል (አቡሻራፍ፣ ገጽ 139-140)።

በማሊ፣ 94% የሚሆኑት ሴቶች በመቆረጥ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 10% የሚሆኑት ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ወይም ከተፈጸመ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ይሞታሉ። ፕላን ኢንተርናሽናል (Plan International) የሚባለው ድርጅት የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን ለመከላከል ያደረገው፣

የጤና ግንዛቤዎችን በማስጨበጥ እና ለቆራጮች (ለገራጮች) ሌላ የገንዘብ ማግኛ መንገድን በማሠልጠን ነበር። ይሁን እንጂ፣ የበለጠ ሁሉን አቀፍ የሆነ አቀራረብ የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኝ ተረዱ። የድርጊቱን አደጋ ከሰፊ የጤና ዐውድ አንጻር ለሴቶች ማስተማር ጀመሩ። ውሳኔ ሰጭ የሆኑት ወንዶችም እንዲማሩ አደረጉ። ሥልጠናው ለገራጮቹ ተለዋጭ የገቢ ምንጭ በመስጠት ፈንታ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንደ ሆነላቸው ተገነዘቡ። ስለዚህም ድርጊቱን ለማስቆም ገራጮቹ እና ማኅበረሰቡ የሴትን ውጫዊ ብልት ከመቁረጥ ጋር ያያያዟቸውን እሴቶች መድረስ እንደሚያስፈልጋቸው አወቁ (ማክኮንቪል፣ ገጽ 25)።

በኢትዮጵያም ጎጂ ባሕል አስወጋጅ ኮሚቴ ባህላዊ ድርጊቶችን አስመልክቶ ጥናት ያካሂዳል፣ ፖስተሮችንና ሌሎች ነገሮችን ይሠራል። በተጨማሪም ጎብረተሰቡን ያሠለጥናል።

መንግሥታት

በአዲስ አበባና በዳካር የተደረጉ ጉባዔዎች፣ የአፍሪካ መንግሥታት የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚቃወም ሕግ ያስተላልፉ ዘንድ ጠይቀዋል (አቡሻሪፍ፣ ገጽ 139)። በቡርኪናፋሶ፣ በኮትዲቯር፣ ጋና፣ ሴኔጋል እና ታንዛኒያ ሕግ ወጥቷል (አቡሻሪፍ፣ ገጽ 141)። በቅርብ ጊዜ ፈረንሳይ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሚቃወሙ ሕግጋትን አውጥታለች። ጂቡቲም ይህንኑ ፈለግ ትከተል ዘንድ ግፊት ተደርጎ ሕግ እንዲወጣ ቢ[illegible]ም፣ በሥራ ላይ ግን አልዋለም፤ ቂንጥርን መቆ[illegible] ዘየክሊኒኮቹ ቀጥሏል። ስለዚህም መንግሥታት ሕጉ[illegible] ሠጡት የሰብአዊ መብት ተጽራካሪ ድርጅቶችን ለማባ[illegible] ለማድረግ አስበው አይመስልም። በግብፅ አገርም እንጂ፣ ተ[illegible] ለና 1996 ዓ.ም በጥንቃቄ የተዘጋጀው እንዲህ ዓይነት በ1[illegible] ሐኮች ተቃዋሚዎችን ዝም ለማሰኘት እንጂ ማኅበረሰቡን ከመቀየር አንጻር ያደረጉት ተጽዕኖ ጥቂት ነው። አሁንም በግብፅ በ1959 ዓ.ም የሕክምና ባለሙያ ባልሆነ ሰው መቆረጥ ተከልክሎ ነበር

(ኤል ሐዲ፣ ገጽ 152፣ 159)። ሕጉች ታዲያ የሴትን ውጫዊ ብልት መቆረጥ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ እንዲፈጸም አደረጉት እንጂ ድርጊቱን አልቀነሱትም። በ1994 ዓ.ም ለሴቶች ደህንነት ሲባል የሕዝብ ሆስፒታሎች ቂንጥርን የመቁረጥ ሥራ እንዳይሠሩ የተጣለው እገዳ ተነሣላቸው (ኤል ሐዲ፣ ገጽ 158)። በ1996 ዓ.ም ደግሞ ድርጊቱ በግልም ሆነ በሕዝብ የሕክምና ተቋማት ውስጥ እንዳይፈጸም የሚያግድ ሕግ ወጥቶ ነበር (ኤል ሐዲ፣ ገጽ 159)።

ምዕራፍ ሰባት::

ለተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ

«በንግግሩ መጀመሪያ ላይ (በሌንያ ላሉ የአንደኛ ደረጃ ልጃገረድ ተማሪዎች) አስቀድመው የተገረዙ ልጆች፣ አዋቂ እና «ልዩ» መሆናቸውን ለማሳወቅ በሚፈለግ መልኩ አንገታቸውን ቀና አድርገዋል:: ትንንሾቹ ደግሞ በአንድ አዛኝ አስተማሪ ፊት ለፊት፣ በፊተኛዎቹ ወንበሮች ላይ ተጨናንቀው ተቀምጠዋል:: ከአንድ ወይም ከሁለት ሰዓታት በኋላ፣ በኋለኛው መቀመጫ ላይ የተቀመጡት ልጆች ዓይናቸው እንባን ያፈሰሰ ጀመር:: እነዚህን ልጃገረዶች በጣም የነካቸው ጉዳይ ያለፉበት ጎጂ ድርጊት (ግርዘቱ) የማይለወጥ መሆኑን ማወቃቸው ነው:: እግዚአብሔር እናቶቻቸውንና አያቶቻቸውን እንደ ረዳ እነርሱንም በእርግጠኝነት ያኖራቸዋል በማለት ከሚደረገው የአስተማሪዎቹ እና የአጥኚዎቹ ክርክሮች በስተቀር እነርሱ ግን የሚጽናኑ አልነበሩም::» (ጋቺሪ፣ ገጽ 32)::

ሁሉም ሴቶች የተፈጠሩት በእግዚአብሔር አምሳል ነው:: ስለ-ሆነም፣ ሰውነትን መጉዳት እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝነው አስቀድመን አይተናል:: ይህን ማድረግ እርሱ ጥሩ ሥራን አልሠራም እንደ ማለት ነው:: የጋብቻ ግንኙነትን መጉዳትም እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል:: ልጆችንም ከመወለዳቸው በፊትም ሆነ በኋላ መጉዳት እንደዛው እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል:: የግብረ ሥጋ ፍላጐታችን እግዚአብሔር የሰጠንና መልካምም እንደ ሆነ አይተናል:: የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለወንድም ሆነ ለሴት ሥቃይ የተሞላው ወይም ኃይለኛ እንዲሆን ቀደም ተብሎም አልታቀደም፣ ወደ ፊትም አይታቀድም:: ይልቁንም፣ የታቀደው በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ለጋራ ደስታ ሁለቱን ሰዎች ወደ አንድነት እንዲያመጣ ነው:: ስለዚህም ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል ማንኛውንም የሚጥስ፣ የግብረ ሥጋ ድርጊት ወይም በመፈጸሚያ በአካላቱ ላይ የሚፈጸም ተግባር ሁሉ ስሕተት ነው:: ስለዚህ ጉዳይ ግልጽ

ልንሆን ያስፈልጋል። ከሴቷ ፈቃድ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ፣ በትዳር ውስጥ ቢሆንም እንኳ፣ የኃይል ጥቃት ነው። አስገድዶ መድፈር ነው። የሴቷን ወሲባዊነት የሚጎዳ ማንኛውም ድርጊት የጾታ ጥቃት ነው። በዚህ ዓይነት ድርጊት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን በመበደል ጥፋተኞች ናቸው። በሴቶች ላይ የኃይል ርምጃ መውሰድ፣ ሴቶችን ከመውደድ ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ነው። ኢየሱስ ሲናገር፣ ሰውን መጥላት ከመግደል ጋር ተመሳሳይ ነው ብሏል።

እግዚአብሔርን ብንጸርና መልካም የሆነውን ነገር ብንቀይር፣ ድርጊቱ ሁል ጊዜ አሉታዊ ውጤት ይኖረዋል። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ለትዳር የሚያገለግልን የሴቶች የአካል ክፍል እንደሚጎዳ መገንዘብ አለብን። ጋብቻ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዴት ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚያሳይ ምስል እስከ ሆነ ድረስ፣ ባህል ውስጥ ያለውን ትዳር ማበላሸት ወደ ሌላው ተዛምቶ ሁሉንም ግንኙነት፣ በተለይም ደግሞ እምነትን የሚያካትተውን ግንኙነት ያበላሻል።

ይህ ሁሉ ምናልባት ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ሐኪም በሽታው ምን እንደ ሆነ ካላወቀ ሊያድነው አይችልም። ሐኪሙ አንዴ ችግሩ ምን እንደ ሆነ ካወቀ፣ ለማስተካከል አብዛኛውን ጊዜ የቀደ ጥገና ቢላዋውን መጠቀም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በሰይፍ ተመስሎ ተገልጾአል፤ እርሱም እንደ ቀደ ጥገና ሐኪሙ ቢላዋ በባህል ውስጥ ጥሩ ያልሆነውን ለማዳን እና ለማስተካከል ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

አሁን ሴቶችን ከመቆረጥ እና ከጾታ ጥቃት ለመከላከል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አንባቢዎቼ ሁሉ እንደ ተሰማችሁ አምናለሁ። ይሁን እንጂ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለው እውነታ ግን ብዙ ሴቶች በአንድ ወይም በሌላ የመቆረጥ ሂደት ውስጥ ማለፋቸው ነው። በዚህ የተጎዱ ሁለት ቡድኖች ይኖራሉ። የመጀመሪያዎቹ፣ መቆረጡ የተፈጸመባቸው ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ

ደግሞ፣ በመቁረጡ የተሳተፉት ናቸው። ምናልባት አንዳንዶች ራሳቸውን በሁለቱም ምድቦች ውስጥ ያገኙ ይሆናል።

ይህንን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሴቶች እና በችግሩ ዙሪያ ሰዎችን ለሚያማክሩ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥቂት የሚጠቅም ነገር ለመናገር መሞከር እንፈልጋለን። አስቀድመን እንደተናገርነው፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የተካሄደው ጥናት አነስተኛ ነው። እኛ አፍሪካውያን ብንሆንም፣ ባህላቸው ይቆረጡ ዘንድ ስለሚጠብቅባቸው ሴቶች ጉዳት እና ደስታ የውስጥ እውቀት እንደሌለን ጸሐፊዎቹ አረጋግጠውልናል። ይሁን እንጂ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ደንቦች ሲጣሱ፣ በዔድን ገነት የተጀመረው ሥቃይ እንደሚቀጥል እናምናለን። በተጨማሪም፣ በጌታ ኢየሱስ ሞት አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት መታደሱንና ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ያለን ገዥነትም አስቀድሞ በታቀደው መልኩ ሊሆን መቻሉን እናምናለን። ከዚህ የሚቀጥለው አሳብ በትሕትና የቀረበው በአሳዛኝ መልኩ በቂ አለመሆኑን በማወቅ ቢሆንም፣ ከጉዳዩ ጋር ለሚታገሉ ሰዎች ጥቂት መምሪያን እንደሚሰጥ ተስፋ በማድረግ እና የበለጠ ብቃትና ልምድ ያለው ሰው አስፈላጊውን ጥናት አድርጎ ግኝቶቹን ለንባብ ያበቃ ዘንድ በመጸለይ ነው።

ለጥቃቱ ሰለባዎች የሚሆን እርዳታ

የጥቃት አቅጣጫዎች

ብዙ ክርስቲያን ጸሐፊዎች እና አማካሪዎች (ለምሳሌ፣ እንደ ማክኑት፣ አንደርሰን እና ግሽዊንድ-ቦሽ) የሰው ልጆች አካል፣ ነፍስ እና መንፈስ እንዳላቸው ይስማማሉ። ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው የተሠራው ከሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ነው። በመጀመሪያ፣ እያንዳንዳችን የተለየ ገጽታ ያለው የሚታይ እና የሚዳሰስ አካል አለን። የገጽታችን መለያየት በጸጉር፣ በቆዳ፣ በዓይን ቀለም ወይም በሌላ ሊሆን ይችላል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ነፍሳችን ወይም ስሜታችን፣ አሳባችንን እና ባሕርያችንን ያጠቃልላል። እነዚህ ነገሮች ልዩ ስብዕናችንን ወይም ሥነ ልቦናችንን ለመሥራት

ይቀናጃሉ። ሦስተኛ፣ እኛ እያንዳንዳችን መንፈስ አለን። ይህ የማይታየው የእኛነታችን አካል ነው። አካላችን ሲጠፋ፣ መንፈሳችን የተፈጠረው ግን ለዘላለም እንዲኖር ተደርጎ ነው። አንድ ሰው በአካል፣ በመንፈስ ወይም ደግሞ በነፍስ ሊጎዳ ይችላል። ፈውስም በእነዚህ ሦስት አቅጣጫዎች ሁሉ ሊካሄድ ይገባል። የብልት መቆረጥ ሴቶችን በአንዱ፣ ብዙውን ጊዜ ግን በሦስቱም አቅጣጫዎች ሊጎዳቸው ይችላል። በብልት መቆረጥ ሂደት ውስጥ ያለፈች ሴት ፈጽማ ትፈወስ ዘንድ እርዳታ ያስፈልጋታል።

አካል

የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ የሴቶችን አካል ይጎዳል። ብዙዎቹ የአካል ላይ ጠባሳዎች ሊስተካከሉ አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሕክምናዎች በመቆረጡ ምክንያት የሚከሰት ያለመመቸት እና ሥቃይን ይቀንሳሉ። በዚህ ሁኔታ የምትሠቃይ ሴት ስለ ችግሩ የሚያውቅ ሐኪም ወይም የማኅፀን ስፔሻሊስትን እርዳት ለማግኘት ትፈልግ ይሆናል።

ነፍስ

የሴቶችን ውጫዊ ብልት መቁረጥ በሴቶች ላይ እንደ ተሰነዘረ የጾታ የኃይል ጥቃት እንደሚቆጠር በምዕራፍ 5 ውስጥ ተመልክተናል። ስለሆነም ይህ ድርጊት የተፈጸመባቸው ሴቶች የሚኖራቸው ሥነ ልቦናዊ ምላሽ፣ የአካል እና የጾታ ጉዳት ከደረሰባቸው ሴቶች ጋር ሊመሳሰል እንደሚችል መጠበቅ አለብን። ኮሊንስ ሲናገሩ፣ የሰውነት ጉዳት በአስተሳሰቦቻችን፣ በስሜቶቻችን እና በባሕሪያችን ላይ ጉዳትን ያደርሳል ብለዋል (ገጽ 300)።

የሴት ውጫዊ ብልት መቆረጥ የጥቅምና የጉዳት አንድምታ መኖሩ የአሳብ፣ የስሜት እና የባሕርይ ውሕጉበር የሚያመጣ ውስብስብ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል። በአስተሳሰብ አቅጣጫ፣ ግለሰቧ አስቀድሞ ጉዳዩን በአምንታዊ መልኩ ትመለከተው ይሆናል። መቆረጡ ሴቷ ከልጅነት ወደ አዋቂነት የማደጓ መግለጫ በመሆኑ ግምት ሊሰጠው ይችላል። ይሁን እንጂ፣ አሁን ስለ ተፈጸመው ነገር አዲስ አሳብ ሊኖራት እና ድርጊቱን በተለየ

መንገድ ልታስተውለው ትችላለች። ሁለተኛ፣ በስሜት አቅጣጫ ደግሞ፣ የቁጣ፣ የሃፍረት፣ የበደለኝነት፣ ብቁ ያለመሆን እና የዋጋ ቢስነት ስሜት ልታዳብር ትችላለች። ድርጊቱ እንደሚፈጸምባቸው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው «የሚገረዙት» ደግሞ፣ በቤተሰባቸው እንደ ተካዱ ይሰማቸዋል። ሴቲቱ ሰዎችን ልትፈራ ወይም ወደ ፊት የበለጠ ሥቃይ ይኖረኝ ይሆናል ብላ ልትፈራ ትችላለች። ስጋት እና ጭንቀት ይኖራትም ይሆናል። ከአካሏ ላይ አንድን ነገር የማጣት ስሜት ሊኖራትና ከዚህም የተነሣ ስለ ጠፋው ነገር ጎዘን እና ምሬት ሊሰማትም ይችላል። ካደጉ በኋላ የተቆረጡት በኃይል ተገደው በአደባባይ በመጋለጣቸው የማይጠፋ ሥቃይ፣ ትዝታና የመዋረድ ስሜት ይኖራቸዋል። በመጨረሻም፣ ባሕርይን በተመለከተ፣ የማይወስኑ፣ በራሳቸው መቆም የማይችሉ ሆነው ራሳቸውን ያገኙታል። በዚህ ሁኔታ የተጠቁ ሰዎች እነርሱም ራሳቸው አጥቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

አሳብ፣ ስሜትና ባሕርይ የተገናኙ ናቸው። የባሕርይና የስሜት መለወጥ የአእምሮ መታደስን ያጠቃልላል። አእምሮአችን ሲታደስ ባሕርያችን ይቀየራል፣ ሊቀየርም ይገባዋል። ባሕርያችን ለመቀየር አስበን በምንወስንበት ጊዜ ባሕርያችን ሲቀየር፣ ስሜታችን እና አስተሳሰባችን ተቀይሮ እናገኘዋለን።

ክርስቲያን ስንሆንና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሲኖር፣ እኛ ትክክል ነው ብለን በምናስበው እና መንፈስ ቅዱስ ስለ አካላችን፣ ትዳርና ወሲብ በእግዚአብሔር ቃል በኩል ከሚያስተምረን ትምህርት ጋር ሊጋጭ ይችላል። ጳውሎስ በቆላስይስ 3:5 - 10 ላይ ሲናገር፣ «እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፣ . . . የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል» ይላል። የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ በተመለከተ፣ አንዳንድ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን፣ ስሜቶችን እና ባሕርያትን ልንለውጣቸው ይገባል። ለራሳችን ሕይወት እንዲሁም ለእርሱ ፍቅርና መመሪያ እንዴት ምላሽ እንደምንሰጥ ኃላፊነት እንዳለብን ልናስታውሰው ይገባል።

ለሌሎች እግዚአብሔር ምን እንደሚል ልንነግራቸው እንችላለን፣ ግን እያንዳንዱ ሰው ቃሉን መተግበርና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለውጥን የማምጣት ኃላፊነት አለበት።

የአሳብ፣ የስሜት እና የባሕርይ ለውጥ የማምጣቱን ሂደት ለማቀላጠፍ እርዳታ ማግኘት ያስፈልገን ይሆናል። በዚህ ምክንያት፣ ከብልት መቆረጡ የተነሣ የተጐዱ ሴቶች ካሉ፣ ተሞክሯቸውን እና ጉዳታቸውን የሚያካፍሉት ሩኅሩኅ ክርስቲያን ጓደኛ ወይም አማካሪ እንዲፈልጉ ይበረታታሉ።

መንፈስ ቅዱስ

አዳምና ሔዋን፣ እንደ እግዚአብሔርና መላእክት፣ መንፈሳዊ ፍጥረት ሆነው ተፈጥረዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እኛም መንፈሳዊ ፍጡራን ነን። በምዕራፍ 3 ውስጥ፣ የሰው ልጅ መውደቅ ከእግዚአብሔር እንደ ለየው፣ ከገነት እና በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ከማድረግ እንዳጎደለው አይተናል። ከኃጢአት የተነሣ ሰዎች ለመንፈሳዊ ሞት ተዳረጉ። ቢሆንም ግን፣ እግዚአብሔር በጸጋው ጣልቃ ገባ እና መንፈሳችን ለዘላለም ይኖር ዘንድ ልጁ ስለ እኛ ይሞት ዘንድ ላከው። የነፍስ መዳን የምናገኘው የግል ኃጢአታችንን ንሥሓ በመግባት እና ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛ ችን አድርገን በመቀበል ነው። በውስጣችን ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ልኳል። እኛም ይህንን ውሳኔ ስናደርግ መንፈሱ መሪያችን እና አጽናኛችን ሆኖ ያገለግለናል።

እስካሁን ድረስ ይህንን ምርጫ ያላደረጉቱ በመንፈሳዊ ነገር ሲጐዱ፣ በሕይወታቸው ብዙ አቅጣጫዎች ፈውስን ሲፈልጉ ራሳቸውን ያገኙታል። መንፈሳዊ ፈውስ ወይም የመንፈስ ደኅንነት ሊገኝ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስን በመምረጥ ብቻ እንደ ሆነ ሊገነዘቡ ያስፈልጋል።

ብልት መቁረጡ በሃይማኖታዊ ሥርዓት በሚታጀብበት ጊዜ (ልጅቱን ይጠብቃት ዘንድ መናፍስትን እንደ መለመን ወይም መማፀን ያለ)፣ ለውጥ ማምጣቱ በመንፈሳዊ አቅጣጫ የተለየ

ጉዳት ሊያመጣ ይችላል። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የዘር መናፍስትም ሆነ «ጠባቂ መናፍስት» የሚባሉት ቦታ የላቸውም። የሚያስፈልገን ብቸኛ መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው። በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሥር መሆን እና በሰው ሕይወት ውስጥ የማይፈለጉ የመናፍስት አሠራሮችን ማፍረስ ጠቢብነት ነው። ለዚህም የበሳል እና እውቀት ያለው የመጋቢ፣ የሽማግሌ ወይም የጓደኛ እርዳታን ማግኘት ያስፈልግ ይሆናል።

የእርዳታ ምንጮች

ባለፈው ክፍል ለአካል፣ ለነፍስ እና ለመንፈስ ፈውስ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ተጠቅሷል። ክራብ እና አሌንደር የተባሉ ጸሐፊዎች፣ ሰው ለእርዳታ ሊሄድባቸው የሚችል አራት ምንጮችን ጠቅሰዋል። እነዚህም እግዚአብሔር፣ ግለሰቡ (ራሱ ሰውየው)፣ ጓደኞቹና ቤተሰቡ እንዲሁም ሰፊው ማኅበረሰብና ባለሙያዎች ናቸው።

እግዚአብሔር

እግዚአብሔር አፍቃሪና ተንከባካቢ አባት ነው። ልጆቹ ሙሉ እና ጤናማ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም ሕይወትን በሙላት እንዲኖሩ ይፈልጋል። ሥቃያችንን እንዲፈውስ እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅ እና በማመን ልንቀርበው ይገባል። እርሱ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር በተለየ መንገድ ይሠራል። በመፈወሱ ሂደት ሌሎችን እንደ መሣሪያ አድርጉ ይጠቀማል፣ ወይም ደግሞ ከእያንዳንዳችን ጋር በቀጥታ ይሠራም ይሆናል። እርሱ የእኛን የተለዩ ስብእናዎቻችንን፣ ፍላጎቶቻችንን እንዲሁም ለሕይወታችን ያለውን ፍጹም ዕቅድ ያውቃል፣ ከእያንዳንዳችንም ጋር በተለየ መንገድ ይሠራል። ከእርሱ ጋር በጸሎት መገናኘት እንችላለን። ደግሞም እርሱ በእኛ ውስጥ ለሚሠራው ሥራ ልባችንን መክፈት ያስፈልገናል። እግዚአብሔር እንደ ፍጹም አጽናኝ አድርጉ ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንደ ላከው አስታውሱ። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ከክፉና መጥፎ ነገር ውስጥ መልካም ነገር እንደሚያወጣም አስቡ። በሮሜ 8:28 ውስጥ ጳውሎስ

ሲናገር፣ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» ይላል። እግዚአብሔር የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥን ድርጊት እንኳ ሳይቀር በመጨረሻ «ለበጎ ሊያደርገው» ይችላል።

ግለሰቡ

እኛ እያንዳንዳችን ለመረጥነው ምርጫችን ኃላፊነት አለብን። በሕይወታችን ውስጥ የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ፣ በተለይም ትናንሽ ልጆች ሆነን የሚፈጸምብንን መቆጣጠር ባንችልም፣ ለዚህ ድርጊት የሚኖረንን ምላሽ ግን ልንቆጣጠር እንችላለን። የድርጊቱ ሰለባ የሆነ ሰው ምሬት፣ ቁጣና ጎዘን የሞላበት ሕይወት ለመምራት ሊመርጥ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይቅር ማለትን እና በእርሱ ውስጥ እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠራ ሊፈቅድ ይችላል። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ ለማወቅ በጸሎት ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ራሳችንን በራሳችን ልንፈውስ አንችልም። ሆኖም ግን፣ ለድርጊቶቻችን፣ ለነገሮች ለምንሰጣቸው ምላሾች እና ለምንመርጣቸው ምርጫዎች ኃላፊነት መውሰድ አለብን። በጸሎት ፍላጎቶቻችንና መሻቶቻችን ለእግዚአብሔር ልንናገር ያስፈልገናል። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር የሚለውን በትዕግሥት መስማትና በቃሉ ከተሰጠው መመሪያ ላይ መጣበቅ፣ እንዲሁም እርሱ ይፈውስ ዘንድ መፍቀድ ያስፈልጋል።

የራሳችንን ልጅ አስመልክቶ ለምንመርጠው ምርጫ በግል ኃላፊነት አለብን። አሳዛኙ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እናቶች እና አያቶች፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ በልጃቸው መቆረጥ ላይ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ነው። እንደ ወላጅ ወይም አያት፣ ልጆቻችንን ከመቆረጥ ለመከላከልና በንቃት ድርጊቱን ለመቃወም መወሰን አለብን።

ማኅበረሰቡ

የማኅበረሰብን ደንብ መከተል ግምት በሚሰጠው ባህል ውስጥ የተናጠል ለውጥን ማምጣት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሴቶች

በቡድን ሆነው ይህንን ጽሑፍ አብረው ቢያነቡት መልካም ሊሆን ይችላል። በቡድኑ ውስጥ አንዱ ሌላውን ሊረዳ፣ አንዳቸው ላንዳቸው ሊጸልዩ እና አንዳቸው ለሌላቸው ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ። በትክክለኛ ምክንያት ለውጥ የሚፈልገው ቡድን ብዙውን ጊዜ ባህሉን ሁሉ ወደ እርሱ አሳብ እንዲያዘነብል ሊያደርግ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ መቀየር እንደሚቻል አንዳንድ ሰዎች ምሳሌ ሆነው መታየት ካልቻሉ ለውጥ አይመጣም። ይህ ትልቅ ጥንካሬን የሚጠይቅ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ተቃውሞ እና መገለልን ሊያስከትል ይችላል። ቢሆንም ግን፣ ትክክለኛ ያልሆነውን ነገር ተቃውመው ለመቆም የተዘጋጁ ብዙ ሰዎች እስካሉ ድረስ፣ ትልቁን ቡድን የመቀየር ሰፊ ዕድል ይኖራል። በባህል ውስጥ ብዙ ሰዎች በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲፈልጉ፣ የባህል ለውጥ ማምጣት ቀላል ይሆናል። ይህን ለማድረግ ዓመታት ወይም የአንድ ትውልድ ዕድሜን ያህል ሊፈጅ ይችላል።

በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የሚስቱ ደስታ እንዲጨምር እርሷን ከመርዳት አንጻር ባል ሊያደርግ የሚችለው ብዙ ነገር አለ። ይህም በግርጌ ማስታወሻ ውስጥ ተጠቅሷል።

ሙያዊ እርዳታ

ብልት በመቆረጥ ሂደት ውስጥ ከማለፍ የተነሣ የሚፈጠሩትን ስሜቶች እና አሳቦችን መፍትሔ ለመስጠት፣ የባለሙያ እገዛ ማግኘት የሚጠቅም ሊሆን ይችላል። ክርስቲያን ሴት፣ የባለሙያ ክርስቲያን አማካሪዎችን፣ የመጋቢዎችን፣ የማኅበረሰብ ጥናት ባለሙያ፣ የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን ወይም የበሰሉ ክርስቲያኖችን እርዳታ ታገኝ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ፣ ከመቆረጡ የተነሣ ከሚፈጠር ሕመም ፋታ ለማግኘት ወደ ሕክምና ባለሙያዎች ዘንድ መሄድ ይጠቅማል።

ለአማካሪዎች እና ለረዳቶች የሚሆን ምክር

ይህ ክፍል የተጻፈው የብልት መቆረጥ ሰለባዎች የሆኑትን በአሳብ በመደገፍ፣ ችግራቸውን በማዳመጥ፣ በመምከርና በማማከር ለሚረዱ ግለሰቦች ነው። እንዲህ የሚያደርገው ሰው የሠለጠነ

ባለሙያ ወይም ደግሞ ጓደኛ ሊሆን ይችላል። ጉዳቱ ከደረሰባት ሴት ጋር ተመሳሳይ ባህል ያለው ወይም ደግሞ ከተለየ ባህል የመጣ ሊሆንም ይችላል። ምናልባትም እርዳት የምትሰጠው ሴት ራሷ በተመሳሳይ ነገር ውስጥ ያለፈች ወይም ያላለፈች ልትሆን ትችላለች። ብቻ እርዳታ ሰጭዎቹ ከየትም ይምጡ ከየት፣ በምንም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ይለፉ፣ መርሐው ለሁሉም አማካሪዎች ያገለግላል።

የሴት ውጫዊ ብልት መቆረጥ ሰለባዎችን ምክር አስመልክቶ እስከ አሁን ብዙ ጥናት የተደረገበት ጉዳይ አይመስልም። በዚህ ክፍል፣ የማማከር አጠቃላይ መርሐ የብልት መቆረጥ ሰለባዎችንም በማማከር ላይ ተግባራዊ መሆን ቢችልም፣ ብዙ ሳይንሳዊ ግብአቶች ግን ለዚህ ጉዳይ ብቻ በተለየ ሁኔታ ያስፈልጋሉ።

በብዙ የማማከር ሥልጠናዎች ላይ አማካሪዎች የራሳቸውን አስተያየት ተግባራዊ እንዳያደርጉት አበክሮ ይነገራቸዋል። ይኸው ተመሳሳይ አሳብ የብልት መቆረጥ ሰለባ የሆነችን ሴት በማማከሩ ወቅትም ተግባራዊ መሆን አለበት። አማካሪዋ ራሷ የችግሩ ሰለባ ሆና መፍትሔ ያላገኘችበት ከሆነች፣ የጉዳት፣ የቁጣ ወይም የተስፋ መቁረጥ ስሜቷን በማማከሩ ወቅት እንዳታወጣው እና የማማከሩን ሁኔታ እንዳያደናቅፈው መጠንቀቅ ይኖርባታል። ለዚህ የሚመከረው ከድርጊቱ ጋር በተያያዘ ከሚሰማት ሥቃይ ፈጽማ ያልዳነች ወይም መፍትሔ ያላገኘች ሴት በማማከሩ ሥራ ውስጥ እንዳትገባ ነው።

የማማከር ሥልጠናው አካል ሆኖ ለአማካሪዎች የሚነገረው ፈራጅ ያልሆነ ስሜት እንዲኖራቸው ነው። የመቆረጡ ድርጊት በሚፈጸምበት ባህል ውስጥ ያላደገች አማካሪ ምናልባት ለጉዳዩ የምትሰጠው ምላሽ ድርጊቱን በመፍራት እና በመኮነን ሊሆን እና ይኸው ወደ ማማከሩ ዐውድ ሊተላለፍ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ አማካሪው ወይም እርዳታ የሚሰጠው ሰው በአእምሮው ውስጥ ሊያኖረው የሚገባው እውነታ ጉዳዩን በአንድ በተለየ ባህል ውስጥ ሆነው ሲያዩት የተለየ ገጽታ እንደሚኖረው ነው። በሚፈጸምበት ባህል ውስጥ ድርጊቱ እንደ ጉዳት (ጥቃት) እንደማይቆጠር ራሳችንን ማስታወስ ያስፈልጋል። ጆሪ ማኪ የሚናገሩትን እንስማ፦

ከባህሉ ውጭ እንዳሉ እንደ ሌሎቹ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ አስፈሪ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፣ በባህሉ ውስጥ ላሉ ግን ድርጊቱ እንደ ኃይል እርምጃ ሳይሆን እንደ ጥርስ ሕክምና ነው። አሜሪካኖች ልጆቻቸውን ኃይለኛ የጥርስ ሕክምና ድርጊት እንዲፈጸምባቸው ያደርጋሉ፣ ይህንን የጥርስ ሕክምና እንዲያገኙ ያለማድረግ የሕይወት እና የጋብቻ ዕድላቸውን ማበላሸት ነው። እስኪ አንድ የውጭ አገር ሰው መጥቶ ይህ የጥርስ ሕክምና አደገኛና በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ደግሞ ወደ አደገኛ በሽታ የሚያመራ እንደ ሆነ ሲናገር አስቡት። ድርጊቱ ለልጆቻችን መልካም ጥርስ ያስገኛል ብለን ከተቀበልን በኋላ አደጋ አለው ብሎ ማመን እስቸጋሪ ይሆንብናል። ያገኘ ነው መረጃ ትክክለኝነት ካረጋገጥን በኋላም እንኳ ሌሎች ሰዎች ማድረጋቸውን ካላቆሙ እኛም ለልጆቻችን ውብ ጥርስ የሚያስገኘውን ድርጊት ለመተው እንቸገራለን። (ከኢንተርኔት የተገኘ፡- የሴት ውጫዊ ብልት መቆረጥ ትምህርት እና ኔትወርኪንግ ፕሮጀክት ድረ ገጽ)።

የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት የትልቁ ሥርዓት ክፍል እንደ ሆነም ማስታወስ ያስፈልገናል። ከጥንት ጀምሮ የነበረ ሥር የሰደደ ባህላዊ ድርጊት ነው። ችግሩን መድረስ የምንችለው በግለሰብ ላይ ብቻ በማተኮር ሳይሆን፣ ሰፊውን ማኅበረሰብ እያሰብን ስልታዊ መንገድ በመጠቀም ነው።

በትልቁ የባህል ሥርዓት ውስጥ፣ የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ የሚፈጸመው የወሲብ ልቅነትን ለመቆጣጠር ወይም ወጣት ሴቶችን ተገዶ ከመደፈር ለመጠበቅ ሊሆን ይችላል። የሴት ውጫዊ ብልት መቁረጥን ለማስቀረት በሚሠራበት ጊዜ፣ በድርጊቱ ፈንታ ሌሎች ክፋቶች እንዳይተኩ የማኅበረሰቡ አጠቃላይ አሠራርና እሴቶች ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ሊለወጡ ያስፈልጋል። እኛ ውጪ ያለን ሰዎች፣ ባህሉ ውስጥ ዘልቀን ገብተን በአሠራሩ ላይ ያለውን ችግር ካቃለልን በኋላ በማፈግፈግ አሠራሩ ሁሉ እንዲፈርስ ማድረግ አንችልም። የዓለም የጤና ድርጅት የሴቶች ጤና ዓለም አቀፍ ኮሚሽን ዋና ዳይሬክተር ሚያዝያ 12፣ 1994 እንደሚከተለው

የተናገሩትን ልብ እንበል፡-

. . . ልምዱን ማውገዝ ብቻ አንዳንዶቻችን ጥሩ እና ጻድቅ የመሆን ስሜት እንዲሰማን ቢያደርግም፣ ለችግሩ ግን መፍትሔን አይሰጥም። ዓላማችን መውቀስ እና ማውገዝ አይደለም። ወይም ደግሞ በሆነ ዓይነት ጎጠረ-ባህላዊነት ስም ዝም ማለትና መፍዘዝ አንችልም። ብልትን የመቁረጥ ድርጊት የሚያም እና በሕፃኗ ሴት ልጅ፣ በኋላም ደግሞ በትልቋ ሴትዮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳለው እናውቃለን። መሥራት ያለብን ግን ሁል ጊዜ የሰዎችን ባህል እና ባህላዊ እሴቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ድርጊቱን ከራሳችን አንጻር እያየን ትርጉም የሌለው እና ጎጂ አድርገን ከቆጠርነው፣ ድርጊቱን በሚፈጽሙት ዘንድ የምንፈልገውን ነገር ማከናወን (ለውጥን ለማምጣት) አንችልም። ሰዎች ባህላቸውን የሚቀይሩት አዳዲሶቹ ድርጊቶችን እንደ ቀድሞዎቹ ሁሉ ትርጉም እና ጥቅም ያላቸው ሆነው ሲቀርቡላቸው ነው። ስለዚህም፣ ማቀድ ያለብን ትርጉሙን ሳይተዉ፣ ድርጊቱን ብቻ እንዲተዉት ሰዎችን፣ ሴቶችንም ጨምሮ፣ ማሳመን ነው። (ከዓለም የጤና ድርጅት የመረጃ መረብ የተገኘ)።

አንዲት ሴት፣ ካላት ደረጃና አቅም አንጻር በማኅበረሰቧ የሚደርስባትን ግፊት እና መገለል ተቋቁማ መቆም ሊያቅታት ይችላል። ስለዚህም ተመራጭ የሚሆነው መንገድ ከግለሰቦች ይልቅ ከሴት ቡድኖች እና ከሰፊው ማኅበረሰብ ውስጥ ከተውጣጡ ቡድኖች ጋር በተለይም ደግሞ የኅብረተሰቡ መሪዎች ከሆኑ ወንዶች ጋር መሥራት ነው። ከሴቶች ጋር በተናጠል በምንሠራበት ጊዜ ደግሞ፣ ከማኅበረሰባቸው ለሚመጣባቸው ተቃውሞ ልናዘጋጃቸውና እንዴት ምላሽን እንደሚሰጡ እንዲወስኑ ልንረዳቸው ያስፈልጋል።

መፍትሔ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች

ግለሰቧን በመርዳት እና በማዳን ሂደት ውስጥ በጸሎት በመታገዝ መፍትሔ ማግኘት የሚገባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

ጉዳትን መቋቋም

የተቆረጠች ሴት የአካል ክፍሏን አጥታለች፣ ያ የአካል ክፍል ደግሞ ከደስታ ጋር ግንኙነት ያለው ነው። የሚያሳዝነው ታዲያ፣ አንዱ በአካል ላይ የተፈጸመውን ድርጊት መለወጥ ያለመቻሉ ነው። ዕድሜዋ ልጅ እያለ እና ማስታወስ በማትችልበት ጊዜ ቀለል ያለ መቆረጥ የተፈጸመባት ሴት፣ ችግሯም ቀለል ያለ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ቂንጥሯን የተቆረጠች ወይም ጠባሳ ያለባት ግን የጠፋውን ነገር የሚያስታውሳት ሥቃይ አላት። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለች ሴት ኀዘኗን ለማስወገድ የሆነውን ነገር መቀበል እና ካለው ሁኔታ ጋር መኖርን መማር ያስፈልጋት ይሆናል። እግዚአብሔር ግን መልካም ነው። በእንደዚህ ዓይነት የኀዘን ወቅት እንደ አጽናኝ ሆኖ እንዲረዳን መንፈስ ቅዱስን ልኮልናል።

የውስጥ ግጭትን መቋቋም

በመቆረጥ ምክንያት ስለሚፈጠሩት ስሜቶች እና አሳቦች ብዙ ብለናል። በፈቃዷ «የተገረዘች» ሴት ከመጀመሪያውም ከድርጊቱ ተጠቃሚ የመሆን ስሜት ይሰማታል። የምትጠቀመውም በማኅበረሰቧ ውስጥ ክብርን፣ ማንነትንና ተቀባይነትን በማግኘት ነው። በተጨማሪም፣ የማግባት እና ልጅ የመውለድን መብትም ታገኛለች። ስለ ድርጊቱ ትምህርት ያገኘች ሴት ግን፣ እነዚህ ሁሉ ባህላዊ እሴቶች የተመሠረቱት ትክክል ባልሆነ ነገር ላይ እንደ ሆነ ታውቃለች። ይህ ደግሞ የስሜት ግጭትን ሊያስከትል ይችላል። ክብር፣ ማንነት እና ተቀባይነት የማጣት ስሜት ይሰማታል። የማግባት እና ልጅ የመውለድ መብቷን ባታጣም፣ ተሰምቷት የማያውቅ ዓይነት የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማት ይሆናል። እነዚህ ስሜቶች ትክክል ባልሆነ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በሌላ አነጋገር፣ ሁልጊዜ ትክክል ያልሆነ የወቀሳ ስሜት ይሰማታል። እነዚህን ስሜቶች ማስተካከል የምንችለው አእምሯችንን በትክክለኛ መረጃ በመሙላት ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ እና ድርጊቱ ለምን እንደሚፈጸም የሚናገሩ ምዕራፎችን ማንበብ ይጠቅማል። በዚህ ስሜት ውስጥ ያለች ሴት በባህሏ ውስጥ ድርጊቱ ለምን

እንደሚፈጸም መጠየቅ እና ከዚያም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ክፍሎች ማንበብ ሊረዳት ይችላል። እግዚአብሔር አእምሮዋን እንዲያድስ እና ለሕይወቷ ያለውን ዓላማ እንዲያሳውቃት መጠየቅም ያስፈልጋታል። በምታነብበት፣ በምታጠናበት እና በምትጸልይበት ጊዜ ጌታ እርሱ የሚፈልገውን እንድትፈልግ ያስችላታል።

ጉዳተኛዋ ሴት ዕለት በዕለት የተለያዩ አሳቦችና ስሜቶች የሚፈራረቁባት ነች እና አማካሪው ወይም እርዳታን የሚያደርግላት ሰው ችግሯን ተረድቶ በትዕግሥት ሊረዳት ይገባል።

የዋጋ ቢስነት ስሜትን መቋቋም

ከኃጢአታችን የተነሣ ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር ሕልውና ለመግባት የማይገባን ነን፣ ይህ መሆኑ ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋችንን አያሳንሰውም። በእርሱ ፊት ዋጋ ስላለንም ነው ኃጢአታችንን ከእኛ ይወስድልን ዘንድ ኢየሱስን ወደ እኛ ሊልክ የተዘጋጀው። ወደ ቈላስይስ የተላከው መልእክት ጠቃሚ ነው። በቈላስይስ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ጽፏል፣ «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና። ለአለቅነትና ከሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነው በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል።» ኤፌሶን 1:3-14 ያለውን ክፍል አንብቡ እና ክርስቲያን ስለ ሆናችሁ የምታገኙትን በረከቶች ሁሉ ዘርዝሩ።

ይቅርታ

በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ፦ «ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም» (ማቴዎስ 18:21-22)።

ኢየሱስ ጴጥሮስን ሌሎችን ይቅር እንዲል ያዘዘበት ምክንያት፣ እግዚአብሔር የእኛን ኃጢአት ወይም መተላለፍ ይቅር ስላለ ነው። ነገር ግን፣ ይቅርታን ለመገንዘብ ጥቂት ጊዜ ወስደን እኛ ከምን ይቅር እንደ ተባልን መረዳት ያስፈልገናል። ኃጢአት ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምባቸው ሁለት ቃላት አሉ። ከእነዚህ

ውስጥ የአንደኛው ቃል ትርጉም «ዒላማን መሳት» የሚል ነው። ወታደሮች ሲሠለጥኑ፣ ጥይታቸውን በትክክል እንዲጠቀሙበት ለማስተማር ዒላማን የመምታት መደበኛ ልምምድ ያደርጋሉ። አንድ ዒላማ ይኖራል፣ እነርሱም በዒላማው ላይ ያለውን ትንሽ ምልክት ለመምታት መሞከርና መምታት አለባቸው። በሚሞክሩበት ጊዜ ዒላማውን ይመቱታል ወይም ይስቱታል። በዚህ ጊዜ መካከለኛ ውጤት የለም። ሊመጣ የሚችለው ውጤት መቶ ከመቶ ወይም ደግሞ ዜሮ ከመቶ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። እርሱም፣ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» ብሎናል (1ኛ ጴጥሮስ 1:15)። የእግዚአብሔርን ቅድስና የማያንጸባርቅ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የማይፈጽመውን ምንም ዓይነት ነገር ብንሠራ፣ ዒላማችንን ስተናል። በሌላ አነጋገር፣ በእግዚአብሔር የቅድስና መመዘኛ ተመዝነን ቀለናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአትን ለመግለጽ የሚጠቀምበት ሁለተኛው ቃል «መተላለፍ» የሚለው ነው። ይህ ቃል የተሠመረን መሥመር ማለፍ የሚል ትርጉም አለው። ይህ መሥመር የእግዚአብሔር ሕግ ነው። የእርሱን ፍጹም ፍቅር፣ ጽድቅና ቅድስና የማያንጸባርቅ ማንኛውንም ነገር እንዳናደርግ፣ እንዳናስብና እንዳንፈልግ እግዚአብሔር አዞናል። እግዚአብሔርን በፍጹም መውደድ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ሌሎችን በሚወዳቸው መንገድ እኛ ልንወዳቸው ሳንችል ስንቀር ያን ጊዜ ሕጉን ተላልፈናል። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው።

ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የኃጢአት መረዳት በአሁኑ ጊዜ እምብዛም አይታወቅም። ሰዎች ኃጢአትን የሚገልጹት ጥሩ ሰዎች የሚያስወግዱት (የማይፈጽሙት) ወይም ደግሞ ማኅበረሰቡ ትክክል አይደለም ብሎ የተስማማበት ነገር እንደ ሆነ አድርገው ነው። ዝነኛ የሆነው አስተሳሰብ የሚያስተዋውቀው፣ ስለ ባህላችን እና ስለ ራሳችን ጥሩ ስሜት ሊሰማን ይገባል የሚልን አሳብ ነው። ባሕል በራሱ ጥሩ ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል። ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠሩ፣ ባህል የእግዚአብሔርን መልካምነት ያንጸባርቃል። ነገር ግን፣ ሰዎች ኃጢአተኞች ስለ ሆኑ፣ ሁሉም

ባህል ይህንን ኃጢአተኝነት የሚያንጸባርቅ ሆነ። ባህላዊ ልማዶች ከእግዚአብሔር ሕግጋት ጋር የማይጣረሱ ከሆኑ ልማዶቹ መልካምና ሊበረታቱ የሚገባቸው ናቸው። ነገር ግን፣ ባህሉ በትእዛዝ የተከለከለ ወይም ጥርት ብለው ከቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሖዎች ጋር የሚጣረስ ሆኖ ሳለ ድርጊቱን በመፈጸም መቀጠል ኃጢአት ነው። ምንም እንኳ ድርጊቱን ለመቀየር ፈጽሞ የማይቻል ቢመስልም እንኳ፣ በማድረግ መቀጠሉ አሁንም ኃጢአት ነው። በባህላችን ጀርባ መደበቅና ትክክል ያለመሆኑን ማስተባበል አንችልም። መልካም እና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ልምዶች ማስተዋወቅ፣ ጎጂነታቸው በግልጽ የሚታዩትን እና ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ለመቀየር መሞከር ይኖርብናል።

የአካል ክፍሎቻችንን እግዚአብሔር እንዳቀደላቸው መሥራት እንዳይችሉ አድርገን ብናስወግዳቸው፣ ብናበላሻቸው ወይም ደግሞ ጉዳት ብናደርስባቸው ኃይለኛ እና ቅዱስ የሆነውን ፈጣሪ እግዚአብሔርን እንበድላለን። ሌላውን ሰው እግዚአብሔር በሚወድድበት መንገድ አልወደድነውም። ከዚህ ኃጢአት ጋር በመጋፈጥ ይቅርታን መጠየቅ ማወቅ አለብን።

እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ባሕርያችን ያደረገውን ይቅርታ ልናውቅ ይገባናል። ደግሞም በቀጣይነት በየቀኑ ለምንሠራቸው ኃጢአቶች ከእግዚአብሔር፣ ለምንፈጽምባቸው በደሎች ደግሞ ከሰዎች ይቅርታን ማግኘትን ልናውቅ፣ እንዲሁም እኛንም የበደሉንን ሰዎች ይቅር ማለት ያስፈልገናል። እነዚህን ጉዳዮች እያንዳንዳቸውን በየተራ እናያቸዋለን።

መጀመሪያ፣ በእግዚአብሔር ላይ ስለማመፃችን ይቅር ልንባል ይገባል። ኃጢአተኛ ስለ ሆነው ባሕርያችን የእግዚአብሔር ይቅርታ መሻት አለብን። የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ በንስሐ እና በእምነት ልንቀርብ ይገባናል። ይቅርታን የሚሰጠው ማን እንደ ሆነ እና ለምንና እንዴትስ ይቅር እንደሚል ሊገባን ያስፈልጋል።

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምክንያት

ከሕይወት ዛፍ እንደ ተገደቡ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ዐመፃቸው ያመጣውን ዘላቂ ጠንቅ መቀበል ነበረባቸው። ደግሞም ከዐመፃቸው የተነሣ ፍጥረት ሁሉ ተቀየረ። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ ኃጢአትን መቅጣት አለበት። ለኃጢአት በቂ የሆነ ቅጣት በዘላቂነት ከእግዚአብሔር መለየት ነው። አዳምና ሔዋን ሁሉ ከዔድን ገነትና ከሕይወት ዛፍ የመብላት ዕድላቸውን አጡ። አዳምና ሔዋን እንዲሁም እኛም ሁላችን ኃጢአትን ሠርተናል። የሴትን ውጫዊ ብልት መቁረጥ ልንፈጽማቸው ከምንችላቸው በርካታ ኃጢአቶች መካከል አንዱ ነው። እኛም ሁላችን ለዘለቄታው ከእግዚአብሔር መለየት ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና» ይላል (ሮሜ 6:23)።

ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ሰይጣንን ስለሚያሸንፈው ዘር የገባውንም ቃል ኪዳን ታስታውሳላችሁ። ያ ዘር ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚያደርሰው መንገድም ነው (ራእይ 2:7)። ኢየሱስ በዚህች ምድር ይኖር ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጣ። እርሱ እኛ በምንፈተንበት በእያንዳንዱ መንገድ ቢፈተንም እንኳ፣ የኖረው ግን ፍጹም እና ኃጢአት አልባ ሕይወት ነበር። ሁሉንም ዓይነት ፈተና ከመጋፈጡ በስተቀር ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጢአትን አልሠራም። ኢየሱስ በእንጨት መስቀል ላይ ሥቃይ እና ጭካኔ የሞላበት ሞት የሞተው ባልፈጸመው ኃጢአት ነው። ያስገደሉት የእኔና የእናንተ ኃጢአቶች ናቸው። እርሱ የሞተው አስቀድመን የሠራነውን ደግሞም ወደ ፊት የምንሠራውን ኃጢአት ሁሉ ያስወግድ ዘንድ ነው። መፈጸማችንን የምናውቀውን ደግሞም እንደ ፈጸምነው የማናውቀውን ኃጢአቶቻችንን ሁሉ ያስወግዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ሲበድሉ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚቆጣ ተነግሮናል። ኢየሱስ በሞተ ጊዜ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የተቆጣውን ቁጣ ሁሉ ወደ ራሱ ወሰደው። በተጨማሪም ለእኛ የሚገባውን ቅጣት የእርሱ አድርጎ ወስዶታል። እርሱ ስለ ሞተ እኛ መኖር ቻልን። ሮሜ 6:23 ሲናገር፣ «የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው» ይላል። ይህንን ስጦታ ተቀብለን

ከኃጢአታችን በመመለስ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን ብንጠይቀው ይቅር ይለናል።

እግዚአብሔር እንዴት ይቅር ይለናል?

ይቅር የሚለን በኢየሱስ የመስቀል ሞት አማካይነት ነው።

እግዚአብሔር ኢየሱስ እንዲሞት የላከው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር ኢየሱስን የላከው፣ ቅዱስ ጻድቅ ደግሞም ኃጢአትን የሚጠላ ስለ ሆነ ነው። ኃጢአት መቀጣት ያለበት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ግን ይወደናል፣ ከእኛም ጋር ግንኙነት ይኖረው ዘንድ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር ለምን ይወደናል?

የሚወደን በእርሱ መፈቀር ስለሚገባን ወይም መልካም ስለ ሆንን ሳይሆን፣ ስለ ፈጠረን ነው።

ይቅር የሚለን ምን ያህል ነው?

እርሱ ይቅር የሚለን ኃጢአታችንን ሁሉ ነው፣ አስቀድመን የሠራናቸውን፣ አሁን እየሠራናቸው ካለነው ደግሞም ወደ ፊት ከምንሠራው ኃጢአት ሁሉ ይቅር ይለናል። ይቅርታ አደረገልን ማለት ስለ ኃጠአታችን አይቀጣንም፣ ኃጢአታችን አይቆጠርብንም ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጽድቅ ይለዋል።

በንስሐና በእምነት ወደ ኢየሱስ ስንመለስ እና በመስቀል ሞቱ ስናምን ጻድቅ እንሆናለን። ደግሞም ይቅርታን እናገኛለን። ይህንን የምንቀበለው ኢየሱስ የሞትን ዕዳ ስለ ከፈለልን ነው።

ከጸደቅን በኋላ ምን ይሆናል?

በእኛ ውስጥ ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ልኳል። የእርሱ ሥራ እኛን ማጽናናት፣ ማስተማር፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የምናንጸባርቅበትን እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናደርግበትን ብቃት መስጠት ነው። ይህ ሂደት መቀደስ ይባላል።

ነገር ግን፣ አንዴ ይቅር ከተባልን በኋላም እንኳ ቢሆን፣ እግዚአብሔርንና ሌሎችን በመበደል ኃጢአትን እንሠራለን። በየቀኑ በቀጣይነት ለምንሠራው ኃጢአታችን የእግዚአብሔርን ይቅርታ ማግኘት ያስፈልገናል። ስለሆነም፣ ከጌታ ጋር ባለ ግልጽ እና ከሕሊና ወቀሳ ነፃ በሆነ ግንኙነት ደስ እንሰኝ ዘንድ፣ በቀጣይነት ይቅርታ ማግኘትን ልንፈልግ ይገባል። በአባትና በልጅ መካከል ያለው ግንኙነት፣ ሁልጊዜም የተጠበቀ ነው። ወላጆቻችን ወላጅ መሆናቸውን አያቆሙም። ነገር ግን፣ በወላጆችና በልጆቻቸው መካከል ያለ ግንኙነት ሊበላሽ ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታም፣ አንዴ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን የእርሱ ልጆች መሆናችንን ማቆም አንችልም፣ ግንኙነታችንን ግን ልንጐዳው እና ልናበላሸው እንችላለን።

ቀጥሎ የቀረበው እውነተኛ ታሪክ አሳቡን በደንብ እንረዳው ዘንድ ያግዘን ይሆናል። ሰዎች በቡድን ሆነው ወደ ገጠር ይጓዙ ነበር። የሚጓዙበት መንገድ ጠባብ እና አቧራማ ነበር። በአንድ መንገድ ጥግ ሲታጠፉ አንዲት ላም በድንገት ገባችባቸውና ሊያድኗት ሳይችሉ ቀርተው ገጯት። ላሚም በመንገዱ ተሽከረከረች፤ ግጭቱ የሚጎዳት ባይሆንም፣ ምናልባት ሚዛኗን ልትስትና ልትበረግግ ትችል ነበር። ሾፌሩ እረኛውን በዓይኑ መፈለግ ጀመረ። በዚህ ጊዜ በጉንጮቹ ላይ እንባው እየወረደ የሚሮጥ ልጅ አየ። ልጁ ለምን ተበሳጨ ብላችሁ ታስባላችሁ? ላሚ በተመታችበት ቅጽበት ልጁ አባቱን ፈራ። ልጁ ግን የአባቱ ልጅ መሆኑን ባያቆምም፣ ወደ ቤቱ ለመሄድ ግን አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጥርበት ሆነ። ከአባቱ ጋር ለመብላትም ሆነ በአንድ ክፍል ውስጥ አብሮ ለመሆን አልፈለገም። ላሚ መገጨቷን ለአባቱ መናገርና ይቅርታን መጠየቅ ደግሞም ውጤቱን መቀበል ያስፈልገው ነበር። ይህ ምናልባትም ላሚን ለማግኘት መመለስ እና ውጤቱን መቀበል ያስፈለገው ይሆናል። የልጁ እና የአባቱ ግንኙነት የሚታደሰው ጉዳዩ ታምኖ ሲስተካከል ብቻ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ኃጢአትን ወይም ትክክል ያልሆነን ነገር በሰማዩ አባታችን ፊት በምናደርግበት ጊዜ፣ ወደ እርሱ ዘንድ ሄደን ማዘናችንን መናገር ያስፈልገናል።

የእግዚአብሔር ይቅርታ ላወቅነውም ሆነ ላላወቅነው ኃጢአት ይቅር እንደሚለን አይተን ነበር። በተጨማሪም ንስሐ፣ ኃጢአትን መናዘዝ እና መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ሊለወጡ የሚገባቸውን ነገሮች እንዲያሳየን ለመፍቀድ መዘጋጀት ነው። እግዚአብሔር ቸር ስለ ሆነ፣ ያጠፋነውን ጥፋት ሁሉ በአንድ ጊዜ አያሳየንም። ይህ ቢሆን ግን ልንጎዳና መኖር ልንታክት እንችላለን። ነገር ግን፣ ቀስ በቀስ በሕይወታችን ውስጥ ያሉትን ኃጢአቶች ስንረዳ፣ እያንዳንዱን በእግዚአብሔር ፊት ልናመጣው እና በጉዳዩ ላይ ይቅርታን ልንጠይቅ እንችላለን። ይህም ከእርሱ ጋር ያለን ግልጽና ደስታ የሞላበት ግንኙነት እንዲቀጥል ያደርጋል። በእምነት ስናድግ፣ ስለ ኃጢአት ምንነት ያለን መረዳትም ያድጋል። እናም እግዚአብሔር ባለፈ ጊዜ ፈጽመነው፣ ነገር ግን በእምነታችን ልጅ ከመሆናችን የተነሣ ጥፋት እንደ ሆነ ያላወቅነውን ኃጢአት ሁሉ እግዚአብሔር ትኩረት እንድንሰጥበት ያደርጋል። ይህን ለመረዳት የሚያግዘን ሌላ ታሪክ ደግሞ እንይ።

በጨለማ ስፍራ ሆኖ የሚጫወት እና በጣም የሚደሰትን አንድ ልጅ እናስብ። በዚህ ስፍራ የሚደረጉ ስሜት የሚሰጡና ደስ የሚያሰኙ ነገሮች ሆኑ። ቀስ በቀስ ግን በአካባቢው ብርሃን መብራት ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ታዲያ ቅጠልና ስንጥሮች በልብሱ ላየ እንደ ተጣበቀ አየና ልብሱን አወለቀ። ብርሃኑ እየደመቀ ሲሄድ እየቆፈረ ሲደሰትበት በነበረው መሬት ላይ የሞተች ላምን አየ። ይህን ጊዜ ተጠየፈና ወደ ኋላው አፈገፈገ። አሁንም ብርሃኑ የበለጠ እየደመቀ ሲሄድ፣ ሸሚዙ እንደ ቆሸሸ አስተዋለና አጸዳው። አሁንም ብርሃኑ በእርግጥ ሲደምቅ ቡናማ ጫማውም ቆሸሾአል። የእግዚአብሔር ቃልም በሕይወታችን ውስጥ እንደ ብርሃን ነው። በመጀመሪያ ክርስቲያን ስንሆን ጥቂት ኃጢአቶቻችንን ብቻ እናያለን። ከእነዚህ ኃጢአቶች ሸሽተን የእግዚአብሔር ቃል ማጥናታችንን ስንቀጥል ደግሞ፣ መጽዳት የሚገባቸውን ሌሎች የሕይወታችንን አቅጣጫዎች ደግሞ ያሳየናል። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።

የሴትን ውጫዊ ብልትን ከመቁረጥ ድርጊት ጋር በተያያዘ፣ ብዙ ሰዎች ስለ ሠሩት ልዩ ኃጢአት የእግዚአብሔርን ምሕረት መፈለግ

አለባቸው:: ይህ የሚያጠቃልለው:-

- ድግስ በመደገስ ከማኅበረሰቡ ክብር ለማግኘት የፈለጉ አባቶች፣
- ለሚደረግባቸው ግፊት ተንበርክከው ልጆቻቸውን ለገራጆች የሰጡ እናቶች፣
- ከመቆረጡ ተግባር ቁሳዊ ጥቅምን የሚያገኙ ገራጆች (ቆራጮች)፣
- «የተገረዘች» ሴት ብቻ ነው የማገባው የሚሉ ወጣት ወንዶች፣
- ላልተቆረጠች ሴት ሙሉ ጥሎሽ የማይሰጡ ቤተሰቦች፣
- ድርጊቱ በሆስፒታል ወይም በክሊኒክ ውስጥ ካለመፈጸሙ የተነሣ የሚፈጠረውን የቁስል መመርቀዝ (Infection) እና ሕመም ለመከላከል ሲሉ በዚህ ሥራ ላይ የተሠማሩ የሕክምና ባለ ሙያዎች፣
- ሴቶች ልጆች ወደ ቆራጮች ዘንድ እንዲሄዱ የሚያመቻቹ የቤተሰብ አባላት፣
- ሴት ልጅ ካልተገረዘች መጥፎ ባሕርይ ይኖራታል ወይም ደግሞ ስላልተገረዘች ዕቃ ትጥላለች (ትሰብራለች) የሚሉ ሰዎች፣
- የወላጆቻቸውን ምክር በሚጻረር መልኩ ተደብቀው ቆራጮች ዘንድ የሚሄዱ ልጃገረዶች፣
- ባልተቆረጡ ሴቶች ላይ የሚያሾፉ ልጆች እና ወጣቶችን ነው::

ብዙ ጊዜ የሚገርዙ ሰዎች ድርጊቱን የሚፈጽሙት ክፉ ነገር የማድረግ ወይም ጉዳት የማድረስ ፍላጎት ኖሯቸው አይደለም:: ይልቁንም፣ ራሳቸውን የሚቆጥሩት በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉ ወንዶችና ሴቶች ጥቅም አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች እንደ ሆኑ አድርገው ነው:: ነገር ግን፣ ምንም እንኳ ድርጊቱን በፈጸምንበት ጊዜ ኃጢአት እንደ ሆነ ባናውቅም፣ አንድ ነገር ትክክል እስካልሆነ ድረስ አሁንም ድርጊቱ ኃጢአት ነው:: መጥፎ መሆኑን ማወቅ ጥሩ እንጂ መጥፎ ዜና አይደለም:: ይህ ማለት እኛ ወይም

ባህላችን ምንም አለ ምን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።

ይቅርታ ሦስተኛ ገጽታ አለው። የጎዳናቸውን ሰዎች ይቅርታቸውን መፈለግ ደግሞም መጠየቅ አለብን። ይህንን ማድረግ የማንችልበት ጊዜ ግን ይኖራል። ምክንያቱም ሰዎቹን አናገኛቸው ይሆናል። አንዳንዴ የረሳውን ሰው አስታውሶ ጉዳዩን እንደገና መክፈት ሰውየውን ይጎዳዋል። በዚህ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለ ማወቅ ብቻ በቂ ነው። ጉዳዩን ወደ ኋላ እንተወውና ወደ ራሳችን ሕይወት እንመለስ። ሰዎች አንተን/ቺን ይቅር ማለት አሻፈረኝ ሊሉም ይችላሉ። እንዲህ ከሆነ የሌሎች ሰዎች ይቅር ያለማለት የእናንተ/ቺ ችግር አይደለምና ለጌታ ተዋቸው።

የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ ትክክል ያለመሆኑን የተገነዘቡ ወላጆች ልጆቻቸው ዘንድ በመሄድ ድርጊቱን ለምን ትክክል እንዳልሆነ አስረድተው ይቅርታን መጠየቅ አለባቸው። ሴት ልጆቻቸውን ያስቆረጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (ሽማግሌዎች) ልጆቻቸውን፣ እርስ በርሳቸው እንዲሁም የሚመሩትን ጉባኤ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። መሪዎች ምሳሌ መሆን አለባቸው። ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ግልጽ እንዳደረገው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነቀፋ የሌለበት እና ለልጆቹ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ተናግሯል (ቲቶ 1፡6)። ገራጮች ድርጊቱ ትክክል እንዳልሆነ በግልጽ ማመን እና የቆረጧቸው ሴቶችንና የልጆቹን ቤተሰቦች ይቅርታ ለማግኘት መፈለግ አለባቸው። ባሎች እና አባቶችም የችግሩ አካል እንደ መሆናቸው መጠን ክሚስቶች እና ከሴት ልጆች ይቅርታን በመፈለግ፣ የመፍትሔው አካል መሆን አለባቸው።

ይህንን ባታደርጉ፣ ከሕሊና ወቀሳ ጋር ትኖራላችሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ግልጽ እና መልካም ግንኙነት ከመኖር ትተጓጎላላችሁ። ዴቪድ አውግሰበርገር የሚከተለውን አሳብ ሰጥቷል፡-

> ሕይወትህን በታማኝነት በእግዚአብሔር ቃል ስታስገዛውና በሕይወትህ ውስጥ ካሉ እውነተኛ ወቀሳዎች ጋር ስትጋፈጥ፣ ራስህን ከሰዎች ወቀሳ እንዲሁም ከጓደኞችህ እና ከጠላቶችህ

ግፊት ነፃ ታወጣለህ። . . . የተገታ ኃጢአት ይጎዳል፣ የተናዘዙት ኃጢአት ግን ያድናል (ገጽ 78)።

አሁን ሌሎችን ይቅር የማለትን ሂደት እንመልከት። ማቴዎስ እንዲህ ብሎ ይናገራል፦ «የበደሏችሁን ይቅር የምትሉ ከሆነ የሰማዩ አባታችሁ እናንተንም ይቅር ያላችኋል። እናንተ ግን የሌሎችን ኃጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁ የእናንተንም ኃጢአት ይቅር አይላችሁም።» በሥጋ፣ በስሜት ምናልባትም በመንፈሳዊው ረገድ የተጎዱ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች የጎዷቸውን ሰዎች በልባቸው ከቻሉም በግንባር አግኝተው ይቅር ሊሏቸው ይገባል። አንድ ነገር ከእኛ እንደ ተወሰደ ማወቅ የቁጣ ስሜት ሊፈጥር ይችላል። ቁጣ ሁልጊዜ ስሕተት አይደለም። ሰዎች እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ሲቀሩ መቆጣት ትክክል ነው። ኃጢአት በሆኑ ልምምዶች መቆጣት ትክክል ነው። እግዚአብሔርም በእነዚህ ነገሮች ይቆጣል። መቅደሱ ትክክለኛ ላልሆነ ጥቅም ሲውል ባየ ጊዜ፣ ጌታ ያደረገው እንደዚህ ነበር። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥም እግዚአብሔር ቁጣችንን በጸሎት እንድንገልጽ እንደሚፈቅድልን እናያለን። መጠንቀቅ ያለብን ግን ቁጣችን እንዳይገነፍልና ወደ ምሬት እንዳይለወጥ ነው። በጎዱን ሰዎች ላይ ማማረር ትክክል አይደለም። ስዎች ጎድተውን ከሆነ፣ መጎዳታችንን ማመንና ስሜታችንን መጋፈጥ አለብን።

ይቅርታ የማናደርግ ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ይጎዳል። ከእግዚአብሔር ጋር ቀጣይ እና ግልጽ የሆነ ግንኙነት ይኖረን ዘንድ፣ የጎዱንን ሰዎች ይቅር ማለት አለብን። ይቅር ያለማለት የሚጎዳው እነርሱን ሳይሆን እኛ ራሳችንን ነው። መራርነት ደስታን ካሉን ግንኙነቶች ውስጥ ሁሉ ይወስድብናል። የተጎዱ ሴቶች ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዳይበላሽ ሲሉ የጎዷቸውን ይቅር ማለት ያስፈልጋቸዋል። ሳትቆረጪ በፊት ያሾፉብሽን ወዳጆችሽን፣ ጓደኞችሽን እንዲሁ የቆረጠሽን/ችሽን ሳይቀር ይቅር ማለት አለብሽ። ባልሽ የተገረዘች (የተቆረጠች) ሴት ፈልጎ ከነበረ ወይም ደግሞ በሠርግሽ ዕለት ምሽት ጎድቶሽ ከሆነ እርሱንም ቢሆን ይቅርታ

አድርጊለት። ይቅር ስትይ ከሰማዩ አባትሽ ጋር ደስተኛ የሆነ ግንኙነት ይኖርሻል።

አንዳንድ ጊዜ የበደሉንን ይቅር እንዳልናቸው ልንነግራቸው ያስፈልገናል። ነገር ግን፣ ይህንን ማድረግ የማይቻልበት ወይም ይህንን ማድረጋችን ለበደለን ሰው የማይጠቅምባቸው ጊዜአት አሉ። ከዚህ በኋላም እንኳ በሌሎች ላይ ቂም ያለመያዛችንን እርግጠኛ መሆን አለብን።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች ሲናገር፣ «እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፣ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፣ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» ይላል (3:13-14)። ይህ ምንባብ ይቅር የምንልበትን ሁለት ምክንቶች ይሰጠናል። በመጀመሪያ፣ ክርስቶስ በውስጣችን ካለ ይቅር ተብለናል፣ ስለዚህ እኛም ይቅር ማለት አለብን። ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ይቅር እንድንል ስላዘዘን ይቅር ማለት አለብን። ጳውሎስ በመቀጠል፣ የክርስቶስ ሰላም ልባችንን ይግዛ ይላል። ይህ የሚሆነው ቃሉን በማጥናት ውስጥ እርሱን እያወቅነው ስንመጣ ነው።

እግዚአብሔር ሰዎችን ይዋጃል። የዳኑ ሰዎች ባህላቸውን በእግዚአብሔር ቃል ሥር ሲያደረግ በህልም ሊዋጅ ይችላል።

ማጠቃለያ

አበባ ስንቀጥፍ፣ በቤታችን ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ደስ ልንሰኝበት እንችላለን። አንዲትን ትንሽ ሴት ልጅን ስንቆርጣት ግን፣ የእግዚአብሔርን ውብ ፍጡር ለዘላለም እናጠፋለን። ከዚህ በላይ እንኳ የጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደ ሆነች እና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነች ይናገራል። ይህን ስናጠፋ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለቅሳል፣ እኛም ልናለቅስ ይገባናል።

ተጨማሪ ማስታወሻ ለወንዶች

ባሎች ሆይ፣ ሚስቶቻችሁን ውደዱ
(በተሾመ ነጋሽ)

ክርስቲያን ከሆኑ ቤተሰቦች የተወለደች እንደ ጎሳው ልማድ ሴት ልጆቿን በግልጽ በአደባባይ ሳይሆን በግል «ያስገረገዘች» አንዲት ኤኒያዊት ሴት የሚከተለውን መረጃ ሰጥታለች::

«አንድ አዛውንት ስለ አዋቂነት ሕይወት ለማስተማር አንዳንድ ጊዜ ይጋበዙ ነበር:: አኺህ ሰው ወሲብ ልጅ ለመውለድ ብቻ የሚጠቅም እንደ ሆነ ይነግሯቸው ነበር:: ሴት ከወንድ ይልቅ በወሲብ ጠንካራ ስለ ሆነች ብልት መቁረጥ የሴቷን የወሲብ ፍላጐት ይቀንሳል ይሏቸውም ነበር:: ወንድ የሚረካው ከሴቷ ጋር ፍቅር እንደ ሠራ ወዲያው ሲሆን፣ ሴቷ ግን እስከ ሦስት ቀናት ሊወስድባት እንደሚችል ይነግሯቸው ነበር:: የሴቶች የወሲብ ፍላጐት እንደ እስክ ስለ ሆነ ቶሎ እንደማይጠፋ እና የወንድ ግን እንደዛ እንዳይደለ ያስረዷቸዋል:: ብልት መቆረጥ ይህንን በሴት ውስጥ ያለውን ፍላጎት ያቀዘቅዛል:: ሴቲቱ እስኩ ሲጀምራት እንደምታብጥ ተነግሯቸዋል:: ይህ ታዲያ እስከ መቆረጥ መወገድ አለበት:: ብልቷን ከተቆረጠች በኋላ ሴት በወሲብ ደስ ልትሰኝ የምትችለው በአእምሮዋ እንጂ በአካሏ አይሆንም::» (ጋቺሪ፣ 25፣ 26)::

ወሲብ በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የፍቅር መግለጫ እንዲሆን የታቀደ ነው:: ጥንዶች አብረው እንዲዘልቁ እና አንዳቸው በሌላቸው ደስ ይሰኙ ዘንድ ለመርዳት የተፈጠረ ነው:: ይህም ልጆች ፍቅርን በሚያገኙበት ሁኔታ ውስጥ እንዲወለዱ ተብሎ የታቀደ ነው:: ባልየው ምን ያህል ጠንካራ እንደ ሆነ ለማሳየት ሚስቱ ከእርሱ ጋር ትተኛ ዘንድ የሚያስገድድበት የኃይል ድርጊት እንዲሆን አልታቀደም:: ሚስት እንድትሠቃይ ወይም ከባሏ ጋር እንድትጣላ ተብሎ አልታሰበም::

የለውጥ ጥሪ

ትዳር የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በመጀመሪያ ጥንዶቹ ይህንን ቃል ኪዳን መረዳት አለባቸው። ይህ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት በቀጥታ የሚያንጸባርቅ ምሥል ነው። የባልና የሚስት ግንኙነት ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ካለው ግንኙነት ጋር የሚስተካከል ነው። ስለዚህ፣ ሊከበር ይገባዋል። ልቅ ወሲብ የምትፈጽምበት ወይም ደግሞ የተወደደች ሚስትህን እንደ ወሲብ ዕቃ የምትቆጥርበት ቦታ አይደለም። ወሲብ ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ የነበረ ሲሆን፣ ያቀደውም እግዚአብሔር ራሱ ነው።

ሆኖም ግን፣ የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ሰይጣን፣ ሰውን በማታለል ዋናውን ንድፍ አበላሽቷል። ከዚህ የተነሣ፣ ሰዎች እንደታቀደላቸው በትዳር ሕይወት ደስ አልተሰኙም። በግብረ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ ለጋራ ደስታ ባልና ሚስት ፍቅራቸውን መካፈል አለባቸው። ለመስጠት እና ለመቀበል እንዲሁም ጥልቅ እርካታን ለማግኘት እግዚአብሔር ዕድሉን ሰጥቷል።

ይሁን እንጂ፣ ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ ይህ አይሆንም። ከብዙ ችግሮች መካከል አንዱ የወሲብ ብልቶች ፈጣሪው እና የመጀመሪያው ንድፍ አውጪ ካሰበው ውጭ እንደ ገና መሠራቱ ነው። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ወሲብ እንዲኖር ያደረገው ለእኛ እርካታ ነው። ሰውነታችንን ለማስተካከል ብንሞክር፣ በጭካኔ ድርጊት ውስጥ እየገባን ነው። ይህ ደግሞ ፈጣሪውን ይጐዳል።

እግዚአብሔር የሴትን የወሲብ ብልቶች ፈጥሯል። የሆነ ዓይነት ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ታዲያ እርሱ ለምን ፈጠራቸው? እያንዳንዱ የአካል ክፍል የተፈጠረበት ዓላማ አለው። ብዙ ደም ወደ ብልት አካባቢ የሚፈስ ከሆነ፣ በእርግጠኝነት እግዚአብሔር እንዲቆረጥ አልፈለገም። እግዚአብሔር በሰው የአካል ክፍሎች ጨዋታን ይጫወታልን? በፍጹም አያደርገውም! እግዚአብሔር የማያስፈልግ አካል በሰውነታችን ውስጥ በፍጹም አያስቀምጥም። እርሱ የሚሠራውን ያውቃል። ዋናውን ንድፍ እንደገና እንዲሠራ ሰውን የሚመክረው ሰይጣን ነው። እርሱ የመጀመሪያ ውሸታም ነው። ባለፈው ጊዜያት ዋሽቷል፣ አሁንም

በመዋሸቱ እንደ ቀጠለ ነው።

ሰዎች ሆይ፣ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ደስታ ተሠርቋል። ከሚስቶቻችሁ ጋር ሆናችሁ በሕይወት ደስ እንድትሰኙ ሰይጣን አይፈልግም። ስለዚህም በሴት ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ስሜት አንቂ አካል ስረቁ እያለ ያስተምራል። የሴት ውጫዊ ብልትን መቁረጥ በሴቶች እና በወንዶች ላይ የሚፈጸም የጭካኔ ኃጢአት ነው። ክርስቲያን እንደ መሆናችን፣ ይህንን ድርጊት በመቃወም ድምጻችንን ከፍ አድርገን ማሰማት ያስፈልገናል። ድርጊቱ ለሴቶች ኢ-ሰብአዊ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የእግዚአብሔርን አምሳል ማበላሸት ነው። ውድ ባሎች፣ በሴት ልጆቻችሁና በሚስቶቻችሁ ላይ የሚፈጸመውን የጥቃት ድርጊት ትቃወሙ ዘንድ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ።

አንድ ጣትህን ብታጣ፣ ጉድለት ይኖርብሃል። የብልትህን ጫፍ ብትቆረጥ ግን፣ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ በአካል እና በስሜት ትጎዳለህ። እንዲህ ከሆነ ታዲያ፣ ለምን ሚስትህ፣ እኅትህ ወይም ሴት ልጅህ ቂንጥሯን እንድታጣ ታደረጋለህ? ከናፍሮችህ ካሉበት ቦታ እንዲወገዱ ቢደረግ፣ ምግብ መብላት አትችልም፤ በተጨማሪም ሽሚዝህን እና ሱሪህን ታበላሻለህ። በዚህ ጭካኔ በተሞላበት መቆረጥ ምክንያት የብልት ከንፈሮች ቢነሡ፣ የአፍ ከንፈርህን እንደ መቆረጥ እና አፍህን ክፍት የመተው ያህል መጥፎ ነው። ክርስቲያኖች ይህንን መጥፎ እና የሚያሠቃይ ድርጊት መዋጋት አለባችሁ። ይህንን መጥፎ ድርጊት ለመዋጋት በጋራ መተባበር አለብን።

ቤተ ክርስቲያኖችም የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊት ያልተባረከ እና መጥፎ እንደ ሆነ ማስተማር አለባቸው። እኛ ክርስቲያኖች ለድምጽ አልባ ሰለባዎች ድምጻችንን ማሰማት አለብን። ልጆችን እና ሴቶችን እንደ ቅርጫ ሥጋ እንዲቆረጡ መፍቀድ የለብንም። እርካታችን በእነርሱ ሥቃይ መሆን የለበትም። በድርጊቱ የሚጐዱት ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ እኛ ወንዶችም ልናገኘው የሚገባንን ደስታ ተቀምተናል። ሰይጣን ግን በእርግጥ የእኛን ደስታ አይፈልግም።

የመልካምነት ጥሪ

በድርጊቱ ምክንያት የሴቶች ደስታ በተጎዳበት ሁኔታ ውስጥ፣ የጋብቻን ግንኙነት ለእጎቶቻችን የበለጠ ደስታ የሚሰጥ የሚሆነው ባሎች የፍቅር መሥራት ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ነው። በጫጉላ ጊዜ አዲሱ ባል ብልቱን በሚስቱ ውስጥ በሚያስገባበት ጊዜ ትዕግሥት ሊኖረው እና ቀስ ሊል ይገባዋል። በጣቶቹ እያሻሻት ጊዜ ማጥፋት አለበት። እንዲህ ካደረገ በጣም አይጎዳትም። ይህ ሊደረግ የሚገባው በችኮላ ሳይሆን፣ ጥንዶቹ ጊዜ ሲኖራቸው እና ለብቻ ሲሆኑ ነው። ቀስ ማለት እና ትዕግሥት ታላቅ ጥንካሬን ያሳያል። የብልት ከንፈር ከተቆረጠ፣ በከንፈር ላይ ያለው ቅባትን የሚያመነጭ ዕጢ ከተወገደ ባርቶሊን ዕጢም (Bartholin Gland) ተጎድቶ ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት የሴቷ ብልት ደረቅ ስለሚሆን ወደ ውስጥ መዝለቅ ያስቸግራል። በወሲብ ወቅት አርቴፊሻል የብልት ማለስለሻ ቅባት ምናልባትም ቫዝሊን የደረቀውን የብልት መተላለፊያ ይረዳዋል። ውኃ ወይም ምራቅ እንኳ ቢሆን አካባቢውን ለማለስለስ ይረዳል። ነገር ግን ኮንዶም የምትጠቀሙ ከሆነ፣ ቫዝሊን ወይም ቅባት ነክ የሆነ ማንኛውንም ነገር መጠቀም አያስፈልግም። ምክንያቱም ቅባቱ ኮንዶሙን ከጥቅም ውጭ ያደርገዋል።

በባል እና ሚስት መካከል የሚደረግ የፍቅር ጨዋታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። በሴት እና በወንድ መካከል ያለ የአካል ግንኙነትን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰፍሮ የምናገኘው በዘፍጥረት 26:8-9 ውስጥ ነው። በሚስት እና በባል መካከል የሚደረግ የፍቅር ጨዋታ ኃጢአት እንዳልሆነ አምናለሁ። በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ንጉሥ ሰለሞን እንዲህ ብሏል፣ «ግራው ከራሴ በታች ናት፣ ቀኙም ታቅፈኛለች።» (መኃልየ 2:6)። መጽሐፉን ከሚስትህ ጋር አብራችሁ አንብቡት። በውስጡ ያለውን አንዳንድ ምክሮችን እና ጥበቦችንም ሞክሯቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ አስፈላጊነት እየተናገረ፣ ራሳችንን ከእግዚአብሔር የበለጠ ትክክል ነን ብለን ለማሰብ እኛ ማን ነን? ከልማዳዊ ማዕቀቦች እና ነውሮች ውጭ የፍቅር ጨዋታ ስሕተቱ ምን ላይ እንደ ሆነ ንገሩኝ። ንጉሥ ሰሎሞን በተጨማሪ ሲናገር፣ «ከምትወድዳት

ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ» ይላል (መክብብ 9፡9)። ከሚስትህ ጋር ሆነህ በሕይወት መደሰት አትፈልግምን?

ምንም እንኳ ሚስቱ የተገረዘች እና በጣም ምርጥ የስሜት አንቂ ብልቷን ወይም ብልቶቿን ያጣች ቢሆንም፣ ራስ ወዳድ ያልሆነ እና ብቃት ያለው ባል ስሜቷን የማነቃቃት ሚና ይጫወታል። ባል ከሚስቱ ጋር ጠንካራ ግንኙነት እና የሚያረካ የግብረ ሥጋ ልምድ ይኖረው ዘንድ የሚከተለውን ከሚስቱ ጋር ማድረግ ያስፈልገዋል። ሴቶች ለንክኪ እና ለአስደሳች ቃላት ምላሽን ይሰጣሉ። ስለዚህ፣ እንደምትወዳት እና እንደምትንከባከባት ንገራት። መወደድን የምትጠላ ሴት በዓለም የለችም፣ እርግጥ ነው ማንም ሰው መወደድን አይጠላም። ፍቅርን ለመግለጽ ባህላችን እንቅፋት መሆን የለበትም። ለምትሠራው ሥራ አመስግናት። እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ። ለእናንተ መጥፎና ጥሩ የሆነውን ነገር እንዳችሁ ለአንዳችሁ ንገሩ። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርስ በርሳችሁ ግልጽ ሁኑ። ባል ሚስቱን ወደ እርካታ ሊያደርሳትና ከእርሷ ጋር በወሲብ ደስ መሰኘት ከፈለገ፣ በብዙ መንገድ እርሷን ማነቃቃት መጀመር አለበት (ለምሳሌ፡- እቀፋት፣ ነካካት፣ ካለችበት ቦታ አስጠራት፣ ወዘተ. . .) አንዳንድ ጊዜ ይህንን ማድረግህን በማለዳ ጀምር። በአጠቃላይ፣ ሴቶች እንደ ወንዶች በማየት አይማረኩም። እነርሱ የሚፈልጉት ፍቅር ነው፣ አሁንም ደግሞ ፍቅር ነው። እነርሱ የሚማረኩበት ምትሐታዊ ነገር ለእነርሱ አሳቢ ሆኖ መገኘ ት ነው።

ባል ለሚስቱ አሳቢና ስሜቷን የሚረዳ ሊሆን ያስፈልጋል። ወሲብ በሚፈጸምበት ጊዜ የሥቃይ ስሜት ካለ፣ ማናቸውም አይረኩም። ሴቲቱ ለግንኙነት ዝግጁ ካልሆነች እና የወሲብ ብልቷ ካልቆመ፣ እርሷን የማስደሰት ሙከራህ ገና ድሮ ከሽፏል። ከሥነ ልቦናዊ መነቃቃት በፊት አካላዊ ግንኙነት መቅደሙ ትክክል አይደለም። ሚስትህ ስሜት እንዳላት አስታውስ፣ እርሷ የወሲብ ዕቃ አይደለችም።

በጥበብ የሚደረግ እንክብካቤ፣ ራስን የሚሰጥ ማንነት፣

ትሕትና፣ ጥንቃቄ እና ክብር ማግኘት ከአልጋ ጨዋታው ይልቅ ለሴቷ የበለጠ ትርጉም ይሰጧታል። በአልጋ ላይም፣ ስሜት አንቂ አካላቷን በመነካካት በዝግታ እና በጥንቃቄ ልታነቃቃት ያስፈልጋል። ሚስትህን አንተ ፈጥነህ ወደምትደርስበት የእርካታ ደረጃ ለማምጣት ጊዜ ይወስዳል። በወሲብ ጨዋታ ጊዜ ባልየውም ሆነ ሚስቲቱ ራቁታቸውን መሆን አለባቸው። በልምድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚደረገው ክፍሉ ፍጹም ጨለማ ከሚሆን ይልቅ፣ ደብዛዛ ብርሃን ቢኖር ጥሩ ነው። ሰውየው ሚስቱን በማየት፣ እርሷም ደግሞ እርሱን በማየት፣ ደስ መሰኘት አለባቸው። ይህ የበለጠ መቀራረብን ያመጣል።

ባል በመደባበስ፣ በመሳም፣ «በፍቅር መንካት» በመነካካት፣ በማድነቅ ጊዜ ወስዶ ለደስታዋ አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት። ጡቷንና፣ ቂንጧዋን መነካካት፣ ታፋዋን መደባበስ፣ ጆሮ ግንዷን፣ አንገቷን፣ ሆዷንና ጭማ አጥንቷን አካባቢ መዳሰስ፤ የምላስ ጫፍንም መጠቀም ለማነቃቃት ተግባሩ እንደሚረዱ የታወቀ ነው። በጀርባ በኩል የአከርካሪ አጥንት አካባቢ ሁሉ ስሜት ሰጪ ስፍራ ነው። ብልህ እና የተወደደ ባል እነዚህን ስፍራዎች አንዱን ከአንዱ በኋላ ለመነካካት (ለመደባበስ/ለመዳሰስ) ቢሞክር፣ ባለቤቱን የማነቃቃት ዕድሉ በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል።

ሁልጊዜ የአንድነት እና የግንኙነት መንፈስ ፍጠር። ሴቶች በተፈጥሯቸው ከአንድ ከሚያምኑትና ከሚወዱት ሰው ጋር ቅርበት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። አንተ ሚስትህን የምትወድድ ባል ከሆንህ፣ ፍቅርህን እርሷን በመቀበል እና ባለመናቅ ግለጽላት። እጎቶችን ለማስዋብ በሚል ሰበብ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መንገድ ሲቀየሩ እና ለጣዖት አምልኮ ሥጋቸው ሲቆራረጥ ዝም አንበል። ትክክለኛ መረጃ ለሌላቸው ወንዶች የራስ ክብር ሲባል ውድ የሆነውን የሴቶች ሕይወት ለሞት የሚዳርገውን ልምድ መደገፍ የለብንም። ለልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ ግምት መስጠት እና በሴቷ ላይ ልቅ በመሆን ጥንካሬውን የሚያሳይ ሰው

ጀግና አድርጎ መቆጠሩ ክፉ ልማድ ነው። ይህ የሴት ደስታ እንዲሠረቅ፣ እንድትሠቃይ እና የወሲብ ሰማዕት እንድትሆን ሰይጣን የሚመክረው ምክር ነው።

ለአእምሮ ሰላም ሲል፣ ሚስቱ የወንጀል እና የጭካኔ ድርጊት በፈጸሙት ላይ ካላት የሥነ-ልቦና ቀውስ እና ቁጣ እንድትወጣ ባሏ ሊረዳት ይገባል። ወሲብ በሴት ላይ ያለህን ጉልበት ወይም «ወንድነትህን» የምታሳይበት ቦታ አይደለም። ይህ በተለይ በአዲስ ጋብቻ ውስጥ እውነትነት አለው። ከመቆረጡ የተነሣ ሴት ወንድን መፈለጓ እንደማይቆም ወንዶች መረዳት አለባቸው። የወሲብ ፍላጐት ተፈጥሯዊ እና እግዚአብሔር የሠራው ነው። በኃጢአት ምክንያት ወሲብ ቢበላሽም፣ ሰይጣን ሊሰርቀው ግን አይችልም። የወሲብ ፍላጐት በአእምሮ ውስጥ ይጀመርና በሰውነት ውስጥ በሚፈጠር እድገንጥር ይደገፋል።

ስለዚህም፣ ባሎች ብልታቸው የተቆረጡ ሚስቶቻቸውን በብዙ መንገድ ሊረዱ ይችላሉ። ይህን ለማድረግ ወንዱን የሚያስከፍለው ራስ ወዳድ ያልሆነ መነሣሣት እና ለጋራ እርካታ የሚስቱን ስሜት ማነሣሣት ነው። እርሷ እንደ ባሏ አጋር እንጂ እንደ ወሲብ ዕቃ መቆጠር የለባትም።

ተቀጥላ

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢትዮጵያ ሕግጋት እይታ

(ከዩኒሴፍ በተገኘ ድጋፍ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር የተዘጋጀ፣ አዲስ አበባ፣ 1997 ዓ.ም) ከሚለው በከፊል የተወሰደ፣

በአዲሱ የወንጀል ሕግ ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተሰጠው ትኩረት

በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሕይወት፣ በአካልና በጤና ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

አንቀጽ 561 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴትና ሕፃናት ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ

አንቀጽ 562 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴት ወይም በሕፃን አካል ላይ ጉዳት ማድረስ

አንቀጽ 564 በትዳር ጓደኛ ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚኖር ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ

አንቀጽ 565 ሴትን መግረዝ

አንቀጽ 566 የሴትን ብልት መስፋት

አንቀጽ 567 በሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት የሚፈጸም የአካል ጉዳት

አንቀጽ 568 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፍ

አንቀጽ 569 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ ስለ መሆን

አንቀጽ 570 ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈጸሙ ማነሳሳት

እነዚህን ድንጋጌዎች ጉዳዩን ከሚመለከቱት የቀድሞው የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጾች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው እናያለን::

አንቀጽ 565 ሴትን መግረዝ

> «ማንኛውም ሰው በየትኛውም የዕድሜ ክልል የምትገኘውን ሴት የገረዘ እንደ ሆነ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል::»

አንቀጽ 566 የሴትን ብልት መስፋት

«1 ማንም ሰው የአንዲትን ሴት ብልት የሰፋ እንደ ሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

2 በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ድርጊት የአካል ወይም የጤና ጉዳት ደርሶ እንደ ሆነ በወንጀል ሕጉ ከፍተኛ ቅጣት የሚጥል ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።»

አንቀጽ 587 ሴትን መጥለፍ

1 ማንም ሰው አንዲት ሴትን አገባታለሁ በሚል አሳብ በሀይል የጠለፈ እንደ ሆነ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመው በማስፈራራት፣ በዛቻ፣ በተንኰል ወይም በማታለል ፈቃደኛ እንድትሆን ካደረገ በኋላ እንደ ሆነ፣ ከሰባት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

2 የጠለፋ ድርጊቱን ተከትሎ አድራጊው ሴትየዋን አስገድዶ የደፈረ እንደ ሆነ በዚህ ሕግ ስለ አስገድዶ መድፈር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት በተጨማሪ ይቀጣል።

3 የጠለፋውን ድርጊት ተከትሎ በጠላፊውና በተጠላፊዋ መሀከል ጋብቻ መፈጸሙ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም።

4 ተበዳይዋ በጠለፋው ድርጊት ለደረሰባት የህሊናና የማቴሪያል ጉዳት አግባብ ባላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ የመጠየቅ መብቷ የተጠበቀ ነው።»

አንቀጽ 561 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴትና ህፃናት ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ

1 ማንም ሰው

ሀ) የእርጉዝ ሴትን ሆድ በማሸት ወይም በመውለድ ላይ ያለችን ሴት አካል በማርገፍገፍ፣ ወይም

ለ) አዲስ የተወለደ ህፃንን እትብት እበት ወይም እንደ እበት የመሰሰለ ነገር በመቀባት፣ ህፃንን ፀሐይ በመከልከል ወይም ቅቤ በማቀጥ፣ የህፃንን እንጥል በመቁረጥ፣ ግግ በማውጣት ወይም እንዳይከተብ በማድረግ፣ ወይም

ሐ) ይህን የመሳሰለና ጎጂነቱ በሕክምና ሙያ የታወቀ ልማዳዊ ድርጊትን በመፈጸም የእርጉዝ ሴት ወይም የህፃን ህይወት እንዲያልፍ ያደረገ እንደ ሆነ፣

በመቀፍጭ ወይም ከሦስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

2 የሴቲቱ ወይም የህፃኑ ሞት የደረሰው በቸልተኝነት እንደ ሆነ ስለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ 543/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የሴቶችን መብት በሚመለከተው አንቀጽ 35/4/ የሚከተለው ተደንግጎ እናየዋለን::

«ሴቶች ከጎጂ ባህል ተፅዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት፣ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው::»

የኤ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ባህል ነክ ዓላማዎች በተገለጹበት አንቀጽ 96/1/ ላይ የሚከተለውን እናገኛለን:-

«መንግሥት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዴሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ሃላፊነት አለበት::»

ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 7

«ማንም ሰው ጨካኝ ኢ- ሰብዓዊና አዋራጅ በሆነ መንገድ መያዝ ወይም መስተናገድ አይገባውም::»

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውንም ዓይነት መድልኦዎች ለማስወገድ የወጣ ኮንቬንሽን

አንቀጽ 2 (ረ)

«በሴቶች ላይ አድሏዊ አሠራርን የሚያንጸባርቁ ማናቸውንም ዓይነት ሕጎች፣ ደንቦች፣ ባህላዊ አሠራሮችንና ልማዶችን ለማስወገድ አባል ሀገሮች ሕግ ማውጣትን ጨምሮ አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተስማምተዋል::»

አንቀጽ 5(ሀ)

«አንዱን ፆታ የሌላው የበታች በማድረግ፣ ወይም አንዱን በሌላው ላይ የበላይ በማድረግ፣ እንደዚሁም ፆታን መሠረት በማድረግ ማኅበራዊ ሚናን የሚወስኑ ባህላዊና ልማዳዊ አፈጻጸሞችን ለማስቀረት አባል ሀገሮች አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ተስማምተዋል::»

የቃላት መፍቻ

መቆራረጥ (Mutilation):- አንድን የአካል ክፍል ጥቅም እንዳይሰጥ ወይም ቀድሞ ይሰጥ ከነበረው ጥቅም ባነሰ መልኩ እንዲያገለግል አድርጎ መቀየር ወይም መቁረጥ (መተልተል) ነው::

ምሥጢራዊ ማኅበረሰብ (Secret Society):- በልዩ ልዩ ምክንያት ከሚኖሩበት ማኅበረሰብ የተገለሉ የማኅበረሰብ አካላት ወይም ጎሳዎች ናቸው (ለምሳሌ፣ በቀድሞ ጊዜ የእጅ ሙያ የነበራቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ቀጥቃጭ ወይም ቡዳ ተብለው የሚደርስባቸው ዓይነት መገለል ነው::)

ሴጋ (Masturbation):- ራስን በራስ የወሲብ ስሜትን የማርኪያ መንገድ ነው::

ቂንጥር (Clitoris):- በሴት ብልት አፍ አካባቢ በላይ በኩል የሚገኝ ቆም ያለ እንጥል መሰል ነገር ሲሆን፣ በአፈጣጠሩ ብዙ የነርቭ ጫፎች የተከማቹበትና ብዙ የደም ዝውውር የሚደረግበት ስፍራ ስለ ሆነ፣ የሴት የወሲብ ስሜት እንዲነቃቃም ሆነ እንዲረካ ወሳኝ ሚናን የሚጫወት ነው::

ባህላዊ ሥርዓት (Traditional Practice):- በአንድ ባህል ውስጥ እንደ ደንብ ተቆጥሮ፣ በተወሰነ ጊዜና ወቅት የሚፈጸም ድርጊት ነው::

ባህላዊ እምነት (Traditional Religion):- በአንድ ባህል ወስጥ ከአያት ከቅድም አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እምነት ነው::

እድገንጥር (Hormone):- በአካል ላይ የተለያዩ ስሜቶችን ለመፍጠርና አካል ለተለያዩ ሁኔታዎች ምላሽን እንዲሰጥ ለማስቻል በአካል ውስጥ ያሉ የተለያዩ እጢዎች በተለያዩ ጊዜያትና የተለያዩ ሁኔታዎች በአካል ላይ በሚከሰቱበት ጊዜ የሚያመነጩት የሰውነት ንጥረ ነገር ነው:: (የተለያዩ እጢዎች የሚያመነጩት የተለያዩ ዓይነት ንጥረ ነገሮችን ነው::)

እጢ (Gland):- ንጥረ ነገሮችን የሚያመነጩ የአካል ክፍሎች ናቸው::

የመሸጋገሪያ ሥርዓት (Passage Ritual):- በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ልጆች የልጅነት ዕድሜያቸውን ጨርሰው ወደ ኮረዳነት ወይም ጉርምስና በሚሸጋገሩበት ጊዜ መሸጋገራቸውን የሚያስታውቁ የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጸማሉ፣ የሚፈጸሙት ድርጊቶች ደግሞ የራሳቸው የሆነ የአፈጻጸም ወግና ደንብም

ይኖራቸዋል፣ ይህ የአፈጻጸም ደንብ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ይባላል። (ለምሳሌ፣ የሴቶች ውጫዊ ብልት መቆረጥ በብዙ ቦታዎች የመሸጋገሪያ ሥርዓት ነው።)

የመውጣት ሥርዓት (Coming-out Ritual):- በአንዳንድ ባሕሎች ውስጥ ልጃገረዶች ብልታቸውን ከተቆረጡ ወይም ወንዶች ከተገረዙ በኋላ ቁስላቸው እስኪድን ድረስ ወይም የጾታ ሚናቸውን አጠናቅቀው እስኪማሩ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ተገልለው እንዲቀመጡ ይደረጋል። ተገልለው የመቆየታቸው ዓላማ ግቡን ሲመታ ተመልሰው ከማኅበረሰቡ ጋር ይቀላቀላሉ። ይህ ከተገለሉበት ስፍራ ወጥቶ ከማኅበረሰቡ ጋር ዳግም የመቀላቀሉ ሂደት የራሱ የሆነ ወግና ሥርዓት አለው። ይህም ሥርዓት የመውጣት ሥርዓት ይባላል።

የጉርምስና ሥርዓት (Puberty Ritual):- ይህ ቃል በመጽሐፉ ውስጥ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ከሚለው ቃል ጋር አንዱ በሌላው እየተለወጠ ጥቅም ላይ የዋለ ስለ ሆነ፣ ከላይ ለ «የመሸጋገሪያ ሥርዓት» የተሰጠውን ፍቺ ይመልከቱ።

የዓይን እናት (Birth Assistant):- ሴት ልጅ በልጅነቷ ብልቷን በምትቆረጥበት ጊዜ መቁረጫውንና የቆራጯን ድርጊት አይታ እንዳትበረግግ በዕድሜዋ ተለቅ ያለች ሴት ዓይኗን ጨፍና እንድትይዛት ይደረጋል፣ ይህች ዓይኗን ጨፍና የያዘቻት ሴት ለተቆረጠችው ሴት ልጅ የዓይን እናት ትባላለች።

ግርዘት (Circumcision):- ከሃይማኖት ወይም ከንጽሕና ጋር በተያያዘ ምክንያት ጥቂት ቆዳን ከወንድ ብልት ጫፍ ላይ መቁረጥ ነው። ድርጊቱን በትክክል ባይገልጸውም እንጂ አንዳንድ ጊዜ ግን የሴትን ውጫዊ ብልት የመቁረጥ ድርጊትም ግርዛት በሚል ቃል ይገለጻል።

ጥሳ:- በአማራ ባሕል ውስጥ ሕፃናት ከተቆረጡ ወይም ከተገረዙ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት ያህል ልጆቹ ወዳሉበት ክፍል እንዳይገቡ የሚከለከሉ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ልጆቹ ከመምጣታቸው በፊት ባለው 24 ሰዓታት ውስጥ ወሲብ የፈጸሙ ናቸው። በዚህ ምክንያት ከመግባት የሚከለከሉ ሰዎች «ጥሳ» ይባላሉ።

ጥቃት (Abuse):- በኃይል የሚፈጸም ድርጊት። በራስ ወይም በሌላ ሰው ላይ የሚፈጸም አካልን ወይም ስሜትን የሚጎዳ ማንኛውም ድርጊት ጥቃት ነው።

ዋቢ መጻሕፍት

Abusharaf, Rogia Mustafa.(2000). Questioning the Tradition: Female Circumcision in Sudan. In M. Turshen (Ed.), *African Woman's Health* Eritrea: Africa World Press.

Alwal, Adem. (1957). Birth Customs in Gimma. *University College of Addis Ababa, Ethnological Society, Bulletin No 7.*

Amnesty International.*(1998)* www.amnesty.org/ailib/intcam/femgen

Augsburger, David.(1970). *The Freedom of Forgiveness 70 x 7.* Chicago: Moody Press.

Barker-Benfield, B.(1976). *The Horrors of the Half Known Life.* New York: Harper Row. Berkeley: University of California Press.

Chebusiri, Wanyama. (Oct to Dec 2000). Ancient Ordeal. *Focus on Africa*, BBC.

Collins, Gary R.(1988). *Christian Counselling: A Comprehensive Guide.* Revised Edition. Dallas: Word Publishing.

El Hadi, Amal. (2000). Female Genital Mutilation in Egypt. In M. Turshen (Ed.), *African Woman's Health.* Eritrea: Africa World Press.

Freeman, Dena & Pankhurst, A. (2001). *Living on the Edge.* Addis Ababa University, College of Social Sciences.

Gachiri, Ephigenia W.(2000). *Female Circumcision With Reference to the Agikuyu of Kenya.* Nairobi:Pauline Publications.

Girma Mohammed. (2001). *The Practise of FGM in Hadiya Culture.* Unpublished Cross Cultural Communication Paper, ETC, Addis Ababa.

Haile Bubbamo Arficio. (July 1973). *Journal of Ethiopian Studies, Vol. 11 No 2.* Addis Ababa: Ethiopia.

Inter African Committee (IAC). (2000). On Traditional Practices Affecting the Health of Women and Children. Arusha: Tanzania.

Lewis I.M. (1955). *Peoples of the Horn of Africa*. London.

Mackie, G. (1998). *www.fgmnetwork.org/articles/mackie*.

Mayers, M. K. (1987). *Christianity Confronts Culture*. Michigan: Zondervan.

Mbiti, John S. (1971). *New Testament Eschatology in an African Background*. London: Oxford

Mbiti, John S. (1988). *African Religions and Philosophy*. Kenya: Heinemann.

McConville, Brigid. (2002). *Developments, Issue 17.*

National Committee on Traditional Practices of Ethiopia.(1998). *Baseline Survey on Harmful Traditional Practices in Ethiopia.* Addis Ababa.

Nega Haile.(2001). *Case Study on Female Circumcision.* An unpublished paper for ETC, Addis Ababa.

Nieman, Sandy (Ed). (1997). *Where Woman Have No Doctor.* California: Hesperian Foundation.

Rahman, A. & Toubia, N. (2000). *Female Genital Mutilation: A Guide to Laws and Policies Worldwide*. London: Zed Books Ltd.

Robert, Dana L. (1966). *American Women in Mission: A Social History of Their Thought and Practice*. Georgia: Mercer University Press.

Robinson, Simon.(2001, 3 Dec). The Last Rites. *Time*.

Rushwan, H. (2000). Female Genital Mutilation Management. *International Journal of Gynaecology & Obstetrics ,70,* 99–104.

Shack, William A. (1966). *The Gurage:* London: Oxford University Press.

Shaw, Evelyn. (1985). Female Circumcision: What Kind of Nursing Care Do Circumcised Women Need? *American Journal of Nursing*. 685–687.

Shell-Duncan, Bettina & Hernlund,Ylva (Eds.). (2001). *Female "Circumcision" in Africa: Culture, Controversy and Change.* London: Lynne Rienner Publishers, Inc.

Terrefe Rus-Work. (1957, Dec). *University College of Addis Ababa, Ethnological Society, Bulletin No 7.*University Press.

W H O : < *h t t p : / / w w w . w h o . i n t / d o c s t o r e / f r h - hd/FGM/infopack/English/fgminfopack. >*

Worsely, A. Infibulation and Female Circumcision. *British Journal of Obstetrics and Gynaecology* (45) 686–91.